አዲስ ልሳን

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

ቅጽ 32 ቁጥር 3599 | ቅዳሜ ህዳር 5 ቀን 2019 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር



በአንታሊያ ያበራው የዲፕሎማሲ ከፍታ

- በአንታሊያ እየተካሄደ ባለው ኮፕ- 31 ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ በታዳሽ ኃይልና በዘላቂ የከተማ ልማት ያስመዘገበቻቸውን ውጤቶች አስተዋውቃለች


3

ፎቶ- ከገፀ ድር

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ፣ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የቱርክዬ ፕሬዝዳንት ረጀብ ጠይፕ ኤርዶጋን በኮፕ 31 ጉባኤ

አዲስ አበባ ላይ የተገለጠው የጉባ ብስራት

- በከተማዋ በ21 ሳይቶች 100 ሺህ ቤቶች እየተገነቡ መሆኑ ተገልጿል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ከንቲባ አዳነች አቤቤ በቱሉ ዲምቱና በቅጠል ተራ እየተገነቡ ያሉ ቤቶችን በትናንትናው ዕለት ጎብኝተዋል

በመለሰ ተሰጋ

የሰው ልጅ ከፍጥረቱ ጀምሮ ደኅንነቱ የተጠበቀ መኖሪያ ማግኘት ከቀዳሚ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ መካከል አንዱና ዋናው ነው። ይሁን እንጂ አሁን ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአዳጊ ሀገራት ከተሞች እየታየ ባለው ፈጣን ዕድገት፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር እና የኢኮኖሚ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመኖሪያ ቤት እጥረት የበርካታ ዜጎች አንገብጋቢ ችግር ሆኗል። በኢትዮጵያም በተለይም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ታላላቅ ከተሞች ውስጥ የሚታየው የቤት እጥረት እና ከደረጃ በታች የሆኑ መኖሪያ ቤቶች መስፋፋት የዜጎችን ኑሮ በቀጥታ የሚፈታተን ከባድ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ሆኖ ቆይቷል።

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

ቀድሞ የመገኘት ማሳያ

- አዲስ አበባ እያከናወነቻቸው ያሉት ሥራዎች ከኮፕ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተሳሰሩ መሆናቸው ተመላክቷል

በቶለሳ መብራቴ

የዓለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ አጀንዳ ከዲፕሎማሲያዊ ውይይትና ከስምምነት ባለፈ በከተሞች የልማት አቅጣጫ፣ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴና በነዋሪዎች የኑሮ ጥራት ላይ የሚያተኩር የዘመናችን ዋነኛ ጉዳይ ሆኗል። በተለይም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (ኮፕ) የሚያስቀምጣቸው የተበከለ አየር ልቀት ቅነሳ፣ የታዳሽ ኃይል ማስፋፋት፣ የደን

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ከህዳር ሲታጠን ወደ ዘላቂ ፅዳት


9

ፎቶ- ከገፀ ድር

ነዋሪዎችን በማሳተፍ የፅዳት ሥራ ሲከናወን

ምናብና ቀመር ሲሰናኙ


11

ፎቶ:- ከገፀ ድር


በሳይንስ የላቁ የጥበብ አፍቃሪያን

የአትሌቲክሱ ተስፋዎች


20

ፎቶ:- ከገፀ ድር

በዳካር ከተማ ሲከናወን በቆየው የወጣቶች ኦሎምፒክ ውድድር ላይ ተሳትፈው ውጤታማ ከሆኑ አትሌቶች መካከል ጥቂቶቹ



አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

ርዕሰ አንቀፅ



የአዲስ አበባ ዕድገት ከተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ ለመሆኑ ሥራዎቿ የተግባር ምስክር ናቸው!

አዲስ አበባ ዕድገቷን ከተፈጥሮ ጋር አስማምታ በለውጥ ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ከተማዋ ከአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት ተላቅቃ ለዘላቂ ልማትና ለሥነ-ምህዳር ጥበቃ ስራ እየተጋች ነው፡፡ ይህ ጉዞዋ ዛሬ ላይ ተጨባጭ ፍሬ እያፈራ ይገኛል።

ከተማዋ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር፣ በታዳሽ ኃይል ልማት እንዲሁም የተፈጥሮ ጋዝን በጥቅም ላይ በማዋል እያከናወነቻቸው ያሉ ዘርፈ ብዙ ጥረቶች ከዓለም አቀፉ የአየር ንብረት ጉባኤ (COP) መርሆዎች ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ይህ የከተማዋ ቁርጠኛ አካሄድ የካርቦን ልቀትን ከመቀነስ ባለፈ የነዋሪዎችን የአኗኗር ዘይቤ እያስተካከለው፣ ወደ ንጹሕና ጤናማ ምዕራፍም እያሸጋገረው መጥቷል። በተለይ የከተማዋን የትራንስፖርት ሥርዓት ከነዳጅ ጥገኝነት በማላቀቅ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ዘመናዊ አውቶብሶችን ወደ ሥራ ማስገባትና በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ የባቡር ትራንስፖርት አውታሮችን ማስፋፋት የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታው ዋነኛ ምሰሶዎች ሆነዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን ለዘመናት የቆሻሻ መጣያ ሆነው የቆዩ ወንዞችን በማጽዳት ወደ ውብ መናፈሻነት የመቀየር እንዲሁም ሰፋፊ የእግረኛና የሳይክል መንቀሳቀሻ መንገዶችን የመገንባት ተግባራት አዲስ አበባን ለሰው ልጅ ምቹና ተስማሚ ከተማ እንድትሆን አድርገዋታል። እነዚህ የተቀናጁ ሥራዎች የከተማዋን ውበት ከማድመቅ ባሻገር የአካባቢ ብክለትን በመግታት ረገድም አስደናቂ ውጤት አስመዝግበዋል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ 31ኛውን የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (COP31) አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት ኢትዮጵያና መዲናዋ አዲስ አበባ በተግባር የተረጋገጠ የአረንጓዴ ልማት አብዮት እያካሄዱ መሆናቸውን ለዓለም አስገንዝበዋል።

መሪዎቹ የአረንጓዴ ዐሻራና የንጹሕ ኃይል ሽግግር ጥረቶች ለአየር ንብረት ለውጥ መከላከል ያላቸውን ፋይዳ በማጉላት፣ የከተማዋ ተሞክሮ በቃል ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ ሥራ የሚገለጽ የዓለም አቀፍ ትብብር ማሳያ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተውበታል። በእነዚህ ዘርፈ ብዙ ስኬቶቿ አዲስ አበባ ለአፍሪካ ከተሞች ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ሕያው ተምሳሌት መሆኗን አስመስክራለች። ከተማዋ በምገባ መርሃ ግብር፣ በስማርት ከተማ አመራር፣ በቆሻሻ አወጋገድና በአካባቢ ጥበቃ ባስመዘገበቻቸው ድንቅ ውጤቶች የሚለን አርባን ፋድ ፖሊሲ ፓከት፣ የሴኡል ስማርት ከተማ፣ የC40 ከተሞች የብሉምበርግ ሽልማት እንዲሁም የአፍሪካ ምርጥ ስማርት ከተማ ሽልማቶችን ጨምሮ በርካታ ዓለም አቀፍ ዕውቅናዎችን መጎናጸፏ የዚሁ ጥረት ቀጥተኛ ውጤት ነው።

አዲስ አበባ በአረንጓዴ ልማት፣ የታዳሽ ኃይልን በሚጠቀሙ ትራንስፖርቶች፣ በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማት ረገድ ያከናወነቻቸው እነዚህ ታላላቅ ሥራዎች፣ መዲናዋ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነቷን እንድታረጋግጥ አስችለዋታል። ይህም ከተማዋ 32ኛውን የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (COP32) ጨምሮ የተለያዩ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉባኤዎችን በላቀ ብቃትና ድምቀት የማስተናገድ አቅሟን ከምንጊዜውም በላይ የሚያሳድግ ጽኑ መሠረት ሆኖ ያገለግላል።

የእኔ አይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

ቸልተኝነት የሚወልደው የዜጎች እንግልት

በኤልያስ ደጉ ከ6 ኪሎ

የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን የዜጎችን እርካታ ለማረጋገጥ መንግስት ዘርፈ ብዙ ሪፎርሞችን አድርጓል፤ በተለይም እንደ መሶብ የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት እና ዲጂታል አሰራሮችን በመዘርጋት ዜጎች ያለ እንግልት እንዲገለገሉ የሚያስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀቶች መፈጠራቸው ይታወቃል። እነዚህ የለውጥ ውጥኖች ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን በመቀነስ ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን እውን ለማድረግ የታለሙ ቢሆንም፣ መሬት ላይ ያለው ተጨባጭ እውነታ ግን የታሰበውን ያህል ፍሬ ሲያፈራ አይስተዋልም።

የዚህ አለመሳካት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ከመሶብ የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ውጭ ባሉ አንዳንድ የመንግስት ሰራተኞችና የስራ ኃላፊዎች ዘንድ የሚታየው ቸልተኝነትና የስነ ምግባር መጓደል ነው ብዬ አምናለሁ። በርካታ ተገልጋዮች ጉዳያቸውን ለማስፈፀም ወደ መንግስት ተቋማት ሲያመሩ፣ "የሻይ ሰዓት ደርሷል፣ ትራንስፖርት ስለሌለ በጊዜ መውጣት አለብን፣ የሚከፈለን ደመወዝና ጥቅማጥቅም አነስተኛ ነው" በሚሉና ሌሎች ሰራተኞች በሚሰነዘሩባቸው መሰረተ ቢስ ሰበቦች ተገቢውን መስተንግዶ ሳያገኙ ይመለሳሉ። ዜጎች ተከብረው ከመስተናገድ ይልቅ ዘለፋና ግልምጫ እየደረሰባቸው፣ ለቀናትና ለሳምንታት ያለበቂ ምክንያት እንዲመላለሱ ይደረጋሉ፤ በዚህም ምክንያት ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን በከንቱ ያባክናሉ።

ከዚህም በከፋ መልኩ አንዳንድ ስነ-ምግባር የጎደላቸው ባለሙያዎችና አመራሮች የህዝብን አደራ ወደ ጎን በመተው፣ ህጋዊ አገልግሎትን እንደ ልዩ ውለታ በመቁጠር ከተገልጋዮች ያልተገባ እጅ መንሻና ጉቦ ይጠይቃሉ። እጅ መንሻ የሰጠ ዜጋ ጉዳዩ በፍጥነት ሲፈፀምለት፣ ህግን አክብሮ የመጣው ንፁህ ዜጋ ግን በተለያዩ ሰበቦች እንዲጉላላና ተስፋ እንዲቆርጥ ይደረጋል። ይህ አሳፋሪ ድርጊት በተቋማት ላይ የተጣለውን የህዝብ አመኔታ ከመሸርሸሩም በላይ፣ የከተማዋን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጉዞ የሚያደናቅፍ አደገኛ ሳንካ ሆኗል ብዬ አምናለሁ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2019 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርቱ በሌብነትና ብልሹ አሠራር ውስጥ እጃቸው አለበት ባላቸው 360 አመራሮችና ሠራተኞች ላይ የዲሲፕሊንና የሥራ ስንብት እርምጃ መውሰዱን እንደማሳያ መጥቀስ ይቻላል፡፡ እርምጃው ከተወሰደባቸው መካከል 301ዱ አመራሮች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 59 ደግሞ ፈጻሚ ሠራተኞች መሆናቸው ይታወሳል፡፡

ይህ ችግር በዋናነት ከደመወዝ ማነስ ወይም ከትራንስፖርት እጥረት ጋር ብቻ የሚያያዝ ሳይሆን፣ ከአገልጋይነት መንፈስ መጥፋት፣ ከሙያዊ ስነ-ምግባር ጉድለትና ከአመለካከት ዝንፈት የመነጨ ነው ብዬ አምናለሁ። የመንግስት ስራ ማለት ህዝብን በቅንነትና በታማኝነት ማገልገያ እንጂ ዜጎችን የማንገላቻ ወይም የግል ጥቅም ማካበቻ መሳሪያ አይደለም። የስራ ኃላፊዎችም በስራቸው ያሉ ሰራተኞችን በአግባቡ መቆጣጠርና ተጠያቂነትን ማስፈን ሲሳናቸው፣ ችግሩ ስር እየሰደደ ሄዶ ተቋማዊ ባህል የመሆን አዝማሚያ ያሳያል።

ስለሆነም የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን በዘላቂነት ለመቀየር፣ የቴክኖሎጂና የአደረጃጀት ሪፎርሞችን ከሰው ኃይል አመለካከት ግንባታ ጋር አቀናጅቶ መምራት የግድ ይላል። የመንግስት አመራሮች በየተቋማቱ ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት፣ በተገልጋይ ላይ በደል የሚፈፅሙና እጅ መንሻ የሚጠይቁ አካላት ላይ የማያዳግም አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል። በተጓዳኝም ታታሪና ቅን አገልጋዮችን የሚያበረታታ የዕውቅና ስርዓት በመዘርጋት፣ የአዲስ አበባ መንግስታዊ ተቋማት በእርግጥም የህዝብ አገልጋይነታቸውን በተግባር የሚያረጋግጡበትን ምህዳር መፍጠር ያስፈልጋል።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

አድራሻ
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት
ስልክ 0111 - 112218

አታሚ
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ግራፊክስ ዲዛይን
እዮብ ተፈራ

ሌይአውትና ዲዛይን
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

የእርምት ባለሙያ
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

የዕለቱ አዘጋጆች
ፋንታነሽ ተፈራ
ሽዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ
ለይላ መሀመድ

ዋና አዘጋጅ
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

ም/ዋና አዘጋጅ
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለሰ ተሰጋ

ከፍተኛ አርታኢያን
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቱ

በአንታሊያ ያበራው የዲፕሎማሲ ከፍታ

- በአንታሊያ እየተካሄደ ባለው ኮፕ- 31 ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ በታዳሽ ኃይልና በዘላቂ የከተማ ልማት ያስመዘገበቻቸውን ውጤቶች አስተዋውቃለች



ፎቶ:- ከገጸ ድር

በቱርክዬ አንታሊያ ከተማ እየተካሄዳ ባለው ኮፕ-31 ጉባኤ እየተሳተፉ ያሉ የተለያዩ ሀገራት መሪዎች በከፊል

በመለሰ ተሰጋ

አፍሪካ አስተማማኝ ድምፅ የሚሆናት በምትፈልግበት በዚህ አንገብጋቢ ወቅት ኢትዮጵያ እንደ ዓድዋ ድል ከፍ ብሎ የሚታይ የልማት ብርሃኗን እየፈነጠቀች በአንታሊያ ሰማይ ሥር በዓለም የዲፕሎማሲ መድረክ ላይ ብቅ ብላለች።።

በቱርክዬ አንታሊያ ከተማ እየተካሄደ ባለው 31ኛው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (ኮፕ-31) ላይ ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እየተመራች፣ የተለመደውን የልመና እና የተጎጂነት ትረካ በመቀየር በመደመር እሳቤ የበለፀገ እና ለዓለም የሚተርፍ ጉልህ የለውጥ ምዕራፍ ላይ መሆኗን አብስራለች።።

ይህ የዓለም አቀፉ አየር ንብረት ጉባኤ ከካርቦን ልቀት መጠን ቅነሳ ውይይት ባሻገር፣ በማደግ ላይ ያሉ እና የበለፀጉ ሀገራት የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ አቅጣጫ የሚወሰንበት የኃይል ሚዛን ማስጠበቂያ የፍልሚያ መድረክም ሆኗል።

ለበርካታ አስርት ዓመታት የበለፀጉ የዓለም ሀገራት በኢንዱስትሪ ብክለት ያከማቹትን ሀብት ተገን በማድረግ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ቀጥተኛ ሰለባ የሆኑትን በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ችላ ብለው ማለፋቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።።

አሁን አሁን የአየር ንብረት ለውጥ ዳፋው እነሱንም እየነካቸው በመሆኑ ስለ አየር ንብረት ለውጥና ተያያዥ ጉዳዮች ደጋግመው መምከር ጀምረዋል።። በሌላ በኩል አፍሪካ ለዓለም አቀፉ የካርቦን ልቀት የምታበረክተው አስተዋፅኦ ከ4 በመቶ በታች ቢሆንም፣ የድርቅ፣ የጎርፍ እና የአካባቢ ብክለት ቀጥተኛ ገፊት ቀማሽ ሆናለች።

በዚህ ሳቢያ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ዘንድ ሲንፀባረቅ የቆየው ዋና አጀንዳ “የአየር ንብረት ፍትሕ” (Climate Justice) እና የበለፀጉ ሀገራት የገቡትን የፋይናንስ ቃል ኪዳን እንዲፈጽሙ መሞገት ነበር። ነገር ግን ይህ ሙግት በተደጋጋሚ በተግባራዊ እርምጃ ከመደገፍ ይልቅ እንደ ተማፅኖ ሲታይ ቆይቷል።

በአንታሊያው ኮፕ-31 ጉባኤ ላይ ግን ኢትዮጵያ ይዛው የወጣችው የዲፕሎማሲ አቋም ከተለመደው የተጎጂነት ንግግር የተሻገረ እንደነበር ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ ያደረጉት የፖለቲካና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አሕመድ ሰይድ ይናገራሉ።።

ኢትዮጵያ በጉባኤው ላይ ያቀረበቻቸው ተጨባጭ ስኬቶቿና በመደመር እሳቤ የተመራው ኢኮኖሚያዊ ከፍታዋ አፍሪካ የአየር ንብረት ሰለባ ብቻ ሳትሆን ለዓለም አቀፉ ቀውስ ተጨባጭና ተግባራዊ መፍትሔዎችን ማቅረብ የምትችል መሪ አህጉር መሆኗን የሚያመላክት ስለመሆኑ የፖለቲካና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው ጠቁመዋል።።

ይህም ብቻ ሳይሆን በኮፕ-31 የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ፓቪሊዮን (የልዩ ኤግዚቢሽን ቦታ) ከማስተዋወቂያና ባህል ማሳያ ማዕከልነት ያለፈ ስትራቴጂያዊ የፖሊሲ አደባባይ ሆኖ እያገለገለ ነው።።

ፓቪሊዮኑ በዲዛይኑ፣ በቀረቡት የመረጃ ሰነዶች እና በተዘጋጁት የንጉሦሽ ውይይቶች ሀገሪቱ በራሷ አቅምና ህዝባዊ ንቅናቄ ያከናወነቻቸውን ከተፈጥሮ የተስማሙና ዘላቂ የልማት ስራዎቿን ለዓለም ማህበረሰብ በማስገንዘብ ረገድ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው።።

የፓቪሊዮኑ መሪ ቃል “ከአንታሊያ እስከ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ዓለምን ለመቀበል ዝግጁ ናት” የሚል ነው። ይህ መሪ ቃል የኢትዮጵያን የወደፊት የዲፕሎማሲ አቅጣጫ ግልጽ በሆነ መንገድ ያሳያል የሚሉት የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ባለሙያው ኢኤአ በ2027 አዲስ አበባ ላይ የሚካሄደውን 32ኛውን የዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (COP 32) ለማስተናገድ ሀገሪቱ ያላትን ቁርጠኝነት እና ዝግጁነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የማብሰሪያ መድረክ እንደሆነም ጠቁመዋል።።

በፓቪሊዮኑ የአረንጓዴ ዐሻራ እና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ የታዳሽ ኃይል እና የኤሌክትሪክ አውታር ማስፋፋት እንዲሁም የከተሞች ኮሪደር እና ተያያዥ ዘርፎች ላይ የተመዘገቡ ልማቶችም በተምሳሌትነት ቀርበውበታል።።

በዚህም ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የተከለቻቸውን ከ56 ቢሊዮን በላይ ችግኞች፣ የደን ሽፋን እድገት እና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎቿን የሚያሳዩ ሳይንሳዊ መረጃዎች እና ተጨባጭ ምስሎች ቀርበዋል። ይህም ሀገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የተከተለችውን አዋጭ የመፍትሔ መንገድ ያሳየ ነው።።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ በውሃ፣ በንፋስ፣ በፀሐይ እና በጂኦተርማል ኃይል የሚመነጩ የኤሌክትሪክ አቅሞችን የሚያሳዩ መረጃዎች ለጎብኚዎች ቀርበዋል። ኢትዮጵያ የካርቦን ልቀት የሌለው ታዳሽ ኃይል በማመንጨት የቀጣናው የንጹህ ኃይል ማዕከል መሆኗንና ይህንኑ አቅም ለጎረቤት ሀገራት በማቅረብ ቀጣናዊ ትስስር እያረጋገጠች እንደሆነ ተብራርቷል።።

በሌላ በኩልም በአዲስ አበባና በሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች የተከናወኑት የኮሪደር ልማት ስራዎች፣ የእግር መንገድና የብስክሌት መስመሮች ማስፋፊያ፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን አጠቃቀም ለማበረታታት የተወሰዱ የፖሊሲ እርምጃዎችም በተንቀሳቃሽ ምስል ታግዘው ቀርበዋል።

ይህ የፓቪሊዮን አቀራረብ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መድረክ ላይ ያላትን የሞራል የበላይነት ከፍ አድርጎታል የሚሉት የፖለቲካና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው፣ ለዚህም ኢትዮጵያ ለዓለም ያቀረበቸው ተሞክሮ በተጨባጭ ሥራዎች የተደገፈ መሆኑን በዋቢነት ጠቅሰዋል።።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ የአየር ንብረት እርምጃ የዜጎችን የዕለት ተዕለት ኑሮ ለማሻሻል፣ የመቋቋም አቅምን ለማጠናከርና የተመዘገቡ የልማት ስኬቶችን ዘላቂ ለማድረግ እጅግ ወሳኝ የሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አካል ስለመሆኑም ጠቅሰዋል።።

በመደመር ፍልስፍና በመመራት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር እስካሁን ከ56 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል ስለመቻሉ የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተመሳሳይ መልኩ የታዳሽ ኃይል ልማትን፣ ዘላቂ የከተማ ግንባታንና የአየር ንብረት ተስማሚ መፍትሔዎችን በስፋት እያሳደግን እንገኛለን ብለዋል።

አሁን ላይ ከቃል ኪዳን ባለፈ ወደ ፈጣን ተግባራዊ እርምጃዎች መሸጋገር ይኖርብናል። ይህም በቀላሉ ሊገኝ በሚችል የአየር ንብረት ፋይናንስ፣ ይበልጥ ጠንካራ በሆኑ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶችና ተጋላጭ ለሆኑ ማህበረሰቦች የመቋቋም አቅም ግንባታ ላይ በሚደረግ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ተግባራዊ መደረግ እንዳለበትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገልፀዋል።።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ታላቅ መድረክ አፅንዖት ከሰጡባቸው ጉዳዮች መካከል በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ እርምጃ ብቻውን ተነጥሎ የሚታይ እንዳልሆነ ነው። በዚህም የአየር ንብረት ለውጥ እርምጃ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አካል መሆኑንም አብራርተዋል።። ለአብነትም የኢትዮጵያ 90 በመቶ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ከውሃ የሚመነጭ መሆኑን እና ይህን ንጹህ ኃይል ለጎረቤት ሀገራትም ጭምር እያቀረበች እንደሆነም አብራርተዋል።።

እስካሁን ከ56 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል፤ ይህም የአፈር መሸርሸርን ከመግታት ባለፈ ለዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል። በከተሞች የጎርፍ መከላከያዎችን ከመገንባት ባሻገር፣ የቆሸሹ ወንዞችን በማጽዳት ዳርቻዎቻቸውን ለቤተሰብና ህፃናት መዝናኛ ወደሆኑ መናፈሻዎች መቀየር እንደተቻለም ጠቅሰዋል።።

በሌላ በኩልም በድርቅ ወቅት በኢኮኖሚው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ከውሃ፣ ከነፋስ፣ ከፀሐይ እና ከጂኦተርማል በተጨማሪ በኒውክሌር ኃይል ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው። የአየር ንብረት አደጋዎችን አስቀድሞ ለመተንበይም የሳተላይት መረጃዎችን እና የሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) በመጠቀም ለአርሶ አደሮች የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ እየቀረበ መሆኑን ጠቅሰዋል።።

በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በየዓመቱ ለዕዳ ወለድ ብቻ ወደ ፣ ትሪሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ይከፍላሉ። ይህም ከፍተኛ የብድር ወጪ የአየር ንብረት መቋቋም አቅማቸውን በመገደቡ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የብድር መመሪያዎቻቸውን ማሻሻል ይኖርባቸዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ የኮፐ 32 ጉባኤን በምታስተናግድበት ወቅት፣ የአየር ንብረት ፋይናንስ ቃል ኪዳኖች ምን ያህል? እስከ መቼ? በምን አሰራር? ለሚሉት ሦስት ጥያቄዎች ግልጽ ምላሽ የሚሰጡበትን እና የቅድመ-አደጋ ዝግጁነት እርምጃዎችን የትኩረቷ ማዕከል አድርጋ እንደምትሰራም ጠቁመዋል።።

በአርግጥም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቱርክዬ አንታሊያ ከተማ እየተካሄደ ባለው 31ኛው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (ኮፐ-31) ላይ ያደረጉት ይህ ታሪካዊ፣ ወቅታዊና ወሳኝ ንግግር ኢትዮጵያ ዛሬም በፍጹም ፅናትና ከፍታ ለአፍሪካ ድምፅ መሆኗን ያስመሰከረችበት፣ ከተፈጥሮ የተስማማና ሁሉን አቀፍ ልማቷን በተግባር ያሳየችበት እና የዲፕሎማሲ ከፍታዋን ዳግም ያበሰረችበት ነው።።

ቀድሞ ... ከገጽ 1 የዞረ

ሀብት መጠበቅ፣ የንጹሕ ትራንስፖርት ማሳደግና የከተሞችን የአየር ንብረት ተጋላጭነት መቀነስ የሚሉ አጀንዳዎች በተግባር እንዲውሉ የከተሞችን ድርሻ ወሳኝ ያደርጉታል።

አዲስ አበባም በተለያዩ የአረንጓዴ ልማት፣ የታዳሽ ኃይል፣ የባቡር ትራንስፖርትና የተፈጥሮ ጋዝ አጠቃቀም ጥረቶች ይህንኑ ዓለም አቀፋዊ አቅጣጫ ከከተማዋ የልማት ግቦች ጋር ለማስተሳሰር እየሠራች ትገኛለች። እነዚህ ጥረቶች ከኮፕ የአየር ንብረት ጉባኤዎች መርሆዎች ጋር የሚጣጣሙ ብቻ ሳይሆኑ፣ ከተማዋ የአካባቢ ጥበቃን ከኢኮኖሚያዊ ልማት ከማኅበራዊ ተጠቃሚነት ጋር ለማቀናጀት የያዘችውን አቅጣጫም ያመላክታሉ።

አዲስ አበባ ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ ያስመዘገበችው የከተማ ዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ጉዞ ተራ የከተማ ልማት ሥራ ብቻ ሳይሆን፣ የዓለም አቀፉ የካርቦን ልቀትን የመቀነስና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን የመቋቋም ንቅናቄ ጋር በቀጥታ የተሳሰረ እውነተኛ የለውጥ ምሳሌ ነው። በተለይም በከተማዋ ተግባራዊ የተደረጉት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሮች፣ የታዳሽ ኃይል አጠቃቀምና የኤሌክትሪክ ትራንስፖርት መስፋፋት እንዲሁም የተፈጥሮ ጋዝን በጥቅም ላይ የማዋል ጥረቶች ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤዎች (ኮፕ) መሠረታዊ ዓላማዎች እና የፓሪስ ስምምነት ግቦች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣሙ ስለመሆናቸው ድርጅቱ ይፋ ባደረጋቸው መረጃዎች ተመላክተዋል።

የዓለም አቀፉ የአየር ንብረት ጉባዔ (ኮፕ) በየዓመቱ ሲካሄድ 31ኛ ላይ ደርሷል። የ2026 ኮፕ31 በቱርክዬ አንታሊያ እየተካሄደ ይገኛል። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና ልዑካናቸው የዚህ ታላቅ ጉባኤ ተሳታፊ ናቸው። ከንቲባዋ ከጉባኤው ጎን ለጎን ከአፍሪካ ልማት ባንክ የአየር ንብረት ለውጥ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር አንቶኒ ኦኮን ንዮንግ እና የግሎባል ኮቨናንት ኦፍ ሜየርስ (Global Covenant of Mayors) አምባሳደር እንዲሁም የፓሪስ ቀድሞ ከንቲባ አን ሂዳልጎ ጋር በአዲስ አበባ የአየር ንብረትና ዘላቂ የከተማ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አድርገዋል።

በውይይቱ ወቅት በተለይም የአየር ንብረት ፋይናንስን በቀጥታ ለከተሞች ማድረስ፣ የፕሮጀክት ዝግጅትና አፈጻጸም አቅምን ማጠናከር በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ ትኩረት ተደርጓል። በተጨማሪም በአረንጓዴ ልማት፣ በወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በከተማ መልሶ ማልማትና በከተማ ግብርና የተገኙ መልካም ልምዶችን ለመማማርና ለመለዋወጥ የሚያስችሉ የትብብር መስኮችን ለማጠናከር ስምምነት ላይ ተደርሷል።


ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከኮፕ31 ጉባኤ ጎን ለጎን ከአፍሪካ ልማት ባንክ የአየር ንብረት ለውጥ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር አንቶኒ ኦኮን ንዮንግ ጋር ተወያይተዋል

አዲስ አበባ የአፍሪካ ከተሞችን የጋራ የአየር ንብረት ለውጥ ስራዎች፣ የፋይናንስ ፍላጎቶችና የልማት አጀንዳ በአንድ ድምፅ ለዓለም ማቅረብ የሚያስችል መድረክ ለመፍጠር ትልቅ እድል እንዳላት ተመላክቷል። በዚህም የጋራ ድምፅን በማጠናከር የአፍሪካ ከተሞችን የልማት ፍላጎት፣ የፋይናንስ ተደራሽነትና የቴክኖሎጂ ትብብርን ለማሳደግ ታቅዶ እየተሰራ እንደሚገኝ ተገልጿል።

ከንቲባ አዳነች ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የከተሞችና የመኖሪያ ቦታዎች ፕሮግራም (UN-Habitat) ዋና ዳይሬክተር አናክላውዲያ ሮስባክ ጋርም ተወያይተዋል። በውይይታቸው ሁለቱ ወገኖች በከተማ ልማትና ፕላን ያላቸውን ትብብር በማጠናከር፣ ቀጣዩን የዓለም የከተሞች ቀን በአዲስ አበባ በስኬት ለማክበር በቅንጅት ለመሥራት ተስማምተዋል። በተጨማሪም በቅርቡ የተፈረመውን የመግባቢያ ስምምነት ወደ ተግባር ለማሸጋገር የሚያስችል የጋራ የትግበራና የክትትል ሥርዓት ለመዘርጋት እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ለመለየት መክረዋል።

የUN-Habitat ስትራቴጂያዊና ቴክኒካዊ አጋርነት የአዲስ አበባን የልማት አጀንዳ ለማፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተጠቅሷል። የዚህ ስምምነትና አጋርነት ዋና ዓላማም የተቀመጡ ውይይቶችንና ተግባራትን ወደ ተጨባጭ ውጤት በመቀየር ለሕዝቡ ዘላቂ ጥቅም ማስገኘት እንደሆነ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂና ቢልት ኢንቫይሮመንት ኮሌጅ የአካባቢ ፕላኒንግ እና ላንድስኬፕ ዲዛይን መምህርና ተመራማሪ ሰለሞን በንቲ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የዓለምን የሙቀት መጠን መጨመር ከ1 ነጥብ 5 ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንዲሆን በሚታገልበት በዚህ ዘመን፣ አዲስ አበባ የከተማ ካርቦን ልቀትን በመቀነስ በኩል በተግባር የተደገፈ ተጨባጭ እርምጃ በመውሰድ ለአፍሪካና ለአዳጊ ሀገራት ከተሞች አርዓያ የሚሆን አዎንታዊ ልምድ ማሳየት ችላለች።

በዚህ ረገድ ከተማዋ ከአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ጋር በማያያዝ ያከናወነቻቸው የችግኝ ተከላና የአካባቢ መልሶ ማልማት ሥራዎች ተጠቃሽ ናቸው። የችግኝ ተከላ የከተማን ውበት ከማሳደግ በላይ ካርቦን ዳይኦክሳይድን (የተቃጠለ አየር) በመምጠጥ፣ የአየር ጥራትን በማሻሻል፣ የሙቀት መጠንን በመቆጣጠርና የከተማ ሥነ-ምህዳርን በማጠናከር የሚኖረው ፋይዳ ከኮፕ ዋነኛ የአየር ንብረት ግቦች ጋር በቀጥታ እንደሚገናኝ ሰለሞን (ዶ/ር) ተናግረዋል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የከተማዋን አረንጓዴ ሽፋን ከ17 በመቶ ወደ 24 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚደረገው ጥረት በዓለም አቀፍ ጉባኤዎች በሚደረጉ ውይይቶች ብቻ ሳይወሰን በየአካባቢው በሚፈጠሩ ተጨባጭ ለውጦች መለካት እንዳለበት የአካባቢ ፕላኒንግ እና ላንድስኬፕ ዲዛይን መምህርና ተመራማሪ አንስተዋል። የከተማ ወንዞችን ዳርቻ ማልማት፣ ፓርኮችን ማስፋፋት፣ የተበከሉ ቦታዎችን ማጽዳትና የተፈጥሮ ሀብትን መመለስ የዚሁ አቅጣጫ አካል ናቸው።

የከተማዋ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት እና በኤሌክትሪክ የሚሰሩ አውቶብሶችም በዚህ ረገድ የሚጠቀስ ተግባራዊ ምሳሌ ነው። በ2015 እ.ኤ.አ አገልግሎት የጀመረው የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር በሁለት መስመሮች 34 ኪሎ ሜትር ርዝመት የሚዘልቅ የኤሌክትሪክ ትራንስፖርት ነው። ይህ የትራንስፖርት አማራጭ የነዳጅ ፍጆታንና የተሽከርካሪዎችን ብዛት በመቀነስ የአየር ብክለትን ለመቆጣጠር ያለው አበርክቶ ጉልህ ነው። በተለይም ኤሌክትሪክ ባቡሩ ኃይሉን ከታዳሽ ኃይል በሚያገኝበት ሁኔታ የካርቦን ልቀትን የመቀነስ አቅሙ የበለጠ ይጎለብታል። በተለይም በየከተሞች የንጹሕ የሕዝብ ትራንስፖርት እንዲስፋፋ ከሚያበረታታው ዓላማ ጋር ይጣጣማል።

ከዚህ በተጨማሪ ከተማዋ የሕዝብ ትራንስፖርትን በተፈጥሮ ጋዝ ለማንቀሳቀስ የጀመረችው ጥረት አዲስ የኃይል አጠቃቀም አቅጣጫን ያመለክታል። በቅርቡ 26 የከተማ አውቶቡሶች ከተለመደው ነዳጅ ወደ ተፈጥሮ ጋዝ ተቀይረው ሥራ መጀመራቸው የሚታወስ ነው። ከንቲባ አዳነች አቤቤ በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት እርምጃው የትራንስፖርት ወጪንና የአካባቢ ብክለትን ከመቀነስ ባለፈ የዜጎችን ጊዜ ለመቆጠብና የሀገር ውስጥ ሀብትን በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያግዝ መሆኑን አመልክተዋል። በተጨማሪም 400 አዳዲስ የተፈጥሮ ጋዝ አውቶቡሶች ወደ ሀገር እንደሚገቡ ተገልጿል።

ታዳሽ ኃይል መጠቀም የአካባቢ ጥበቃን ከኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር የማስተሳሰር ፋይዳ የገለጹት መምህርና ተመራማሪው፤ የሀገር ውስጥ የተፈጥሮ ጋዝን በመጠቀም በነዳጅ ላይ የሚኖረውን ጥገኝነት መቀነስ፣ የውጭ ምንዛሬን መቆጠብና የሕዝብ ትራንስፖርትን ወጪ ማቃለል ያስችላል። ሆኖም ተፈጥሮ ጋዝ እንደ ኤሌክትሪክ ከታዳሽ ምንጮች የሚመነጭ ንጹሕ ኃይል ሳይሆን ቅሪተ አካል ነዳጅ ነው። ስለዚህ ከኮፕ የረጅም ጊዜ የካርቦን ገለልተኝነት ግብ አንጻር እንደ የሽግግር መፍትሔ በመውሰድ ወደ ኤሌክትሪክና ሌሎች ታዳሽ ኃይሎች የሚደረገውን ሽግግር ማፋጠን እንደሚገባም ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በታዳሽ ኃይል፣ በኤሌክትሪክ ባቡርና በተፈጥሮ ጋዝ አጠቃቀም እያከናወነች ያለው ሥራ ከኮፕ የአየር ንብረት ግቦች ጋር የተሳሰረ የከተማ ልማት አቅጣጫ ነው። በአረንጓዴ ልማት ላይ የተሰራው ስራ ከተማዋን ወደ ዘላቂ የከተማ ልማት ምሳሌነት አሸጋግሯታል።

አዲስ... ከገጽ 1 የዞረ

አዎ፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት ከቁሳቁስ እጥረት በላይ ነው፡፡ አንዳንዴም የሰው ልጅ ሰብዓዊ ክብር የሚፈተንበት፣ የጤናና የስነ-ልቦና ስቃይ የሚጸናበት ከባድ አደጋ ሲሆን ይስተዋላል፡፡ ይህንን ሀቅ ከግምት ያስገባው የመደመር መንግሥትም አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የበርካቶችን የዘመሙ ቤቶች ጎጆ አቃንቷል፤ በአዲስ መልክም ቀልሷል፡፡

ባሳለፍነው ዓመት መጨረሻም የታላቁ ህዳሴ ግድብ መመረቅን አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጉባ አደባባይ በኢትዮጵያ ሰማይ ሥር እንደ ጸሐይ የሚያበሩ ሰባት የልማት ከዋክብትን ይፋ አድርገዋል፡፡

እነዚህም የኒውክሌር ማበልጸጊያ፣ የጋዝ ፋብሪካ ማስመረቅ፣ የነዳጅ ማጣሪያ እውን ማድረግ፣ በአፍሪካ ግዙፉ አየር ማረፊያ፣ 2ኛውን የጋዝ ፋብሪካ ግንባታ ማስጀመር፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ ማስጀመር እና ፣ ነጥብ 5 ሚሊዮን ቤቶች በመላው ሀገሪቱ ማስጀመር መሆናቸው ይታወሳል፡፡

ሁሉም በሚባል ደረጃ ከቃል ወደ ተግባር ተለውጠዋል፡፡ በእርግጥም ይህ ከመደመር መንግሥት የተሰማው ሀገራዊ ብስራት ወደ ተግባር ስለመቀየሩ መንግሥት ውስብስብ ችግሮቹን ፈትቶ እውን ያደረገው የህዳሴው ግድብ በራሱ ምስክር ነው፡፡

የሌሎቹ ታላላቅ ብስራቶች እውን መሆን እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ከ7 ታላላቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች መካከል ያካተተው የቤት ልማት በተለይም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ትልቅ ዋጋ ያለው መሆኑን እና የቤት እጦት በተለይም ለሰው ልጆች መኖሪያ ምቹ ያልሆኑ ቤቶችና አካባቢዎች በነዋሪዎች ሕይወት ላይ የሚያደርሱት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ከፍተኛ እንደሆነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂና ቢዩልት ኢንቫይሮመንት ኮሌጅ የከተማ ፕላኒንግ መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ብርሃኑ ግርማ (ዶ/ር) ይናገራሉ፡፡

በመሆኑም በዘመናዊ የከተማ ፕላን አስተሳሰብ ውስጥ ነዋሪዎችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብራቸው ሳይበታተን በቦታቸው ላይ ማልማት ወይም ማሻሻገር ቀዳሚው ተግባር ነው። ይህንንም ተከትሎ በአዲስ አበባም ሆነ እንደ ሀገር ዜጎች በተሻሉና በዘመናዊ መኖሪያ ቤቶችና አካባቢዎች እንዲኖሩ ለማድረግ የተሠሩ ተግባራት ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጣቸው እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

የፕላኒንግ ባለሙያው ብርሃኑ ግርማ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ የዜጎችን አንገብጋቢ ችግሮች በተለይም ዘመናዊ ቤቶችን በስፋት በመገንባትና ምቹ የመኖሪያ አካባቢዎችን በመፍጠር የልማት ማዕከል ሰው መሆኑን አስመስክሮ መጓዝ መቻሉ ለሌሎች ሀገራትም ትልቅ አርአያ የሚሆን የዕድገት ምዕራፍ ነው።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በተለምዶ ቅጠል ተራ በሚባል መንደር እየተገነቡ ካሉ ቤቶች መካከል ከፊሎቹ

በትናንትናው ዕለትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በቱሉ ዲምቱ 33 ብሎኮችን እና በአዲስ ከተማ ቅጠል ተራ 9 ብሎኮችን ጎብኝተዋል፡፡ በዚሁ ወቅት የጉባ ብስራትን መነሻ አድርገው ንግግር ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በአምስት ዓመታት ውስጥ ፣ ነጥብ 5 ሚሊዮን ቤቶችን ገንብተን ለማስረከብ ለሕዝባችን ቃል ገብተናል፤ ይህንንም ቃላችንን በተግባር ለማረጋገጥ ቀን ከሌት ያለ እረፍት እየተጋን ነው ብለዋል፡፡

አከለውም፣ ሕዝባችን በመኖሪያ ቤት እጥረት ምክንያት የሚገጥመውን ፈተናና ስጋት በሚገባ እንረዳለን፣ ደረጃቸውን የጠበቁና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶችን ማመቻቸት የልማት ግብ ብቻ ሳይሆን፣ ለዜጎቻችን ያለብን አደራና ኃላፊነት መሆኑንም ጠንቅቀን እንገነዘባለን ካሉ በኋላ ዋነኛ ትኩረታቸውም ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ፣ የሕዝቡን የመኖሪያ ቤት ጫና ማቃለል እና በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ቤተሰቦች የተሻለ የኑሮ ምዕራፍ መክፈት እንደሆነም አስምረውበታል፡፡

የሕዝባችንን የቤት ጫና ማቃለል ለእኛ የልማት ግብ ብቻ ሳይሆን አደራና ኃላፊነት በመሆኑ 24/7 (ሳምንቱን በሙሉ ለ24 ሰዓታት) ተግተን እንሠራለን ያሉት ደግሞ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ናቸው፡፡ ከንቲባ አዳነች “ቃልን በተግባር!” በሚል ርዕስ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ከጉባ ብስራቶች አንዱ እንደ ሀገር በአምስት ዓመታት ውስጥ ፣ ነጥብ 5 ሚሊዮን ቤቶችን ለዜጎች ለማስረከብ የተገባ ቃል ስለመሆኑም አውስተዋል፡፡

በዚህም እንደ አዲስ አበባ በ2ነ ሳይቶች ነዐ ሺህ ቤቶች እየተገነቡ መሆኑን ጠቅሰው፣ እነዚህም 50 ሺህ በከተማው በጀት፣ 50 ሺህ ደግሞ በመንግሥት የግል አጋርነትና በማኅበራት እየተገነቡ ስለመሆኑም አብራርተዋል፡፡

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ አዲስ አበባ ለበርካቶች ምቹ የመኖሪያ ቤቶችና አካባቢዎችን መፍጠር ችላለች። ለአብነትም ወይዘሮ ዙፋን ስጦታው በልደታ ክፍለ ከተማ በአሁኑ ስያሜ የበንነት መኖሪያ መንድር፣ ለ65 ዓመታት ያህል በኖሩበት አሮጌ የቀበሌ ቤት ውስጥ ያላለፉት ሕይወት በስጋትና በጭንቀት የተሞላ ነበር።

በዚያ ደካማ የጭቃ ቤት ውስጥ እያንዳንዱ የከረምት ወራት ሲመጣ ደስታን ሳይሆን ፍርሃትን ይዞ ይመጣ ነበር። የቤቱ አፈር እየረገፈ፣ ጣሪያው እያፈሰሰ እና ከቤታቸው ሥር ያለው ገደል የመናድ አደጋ እያንዣበበባቸው ልጆቻቸውን ሰብስበው እንቅልፍ አጥተው የሚያደሩበት ጊዜ የሚረሳ አይደለም። በተጨማሪም በርካታ ነዋሪዎች የሚጠቀሙበት አንድ የጋራ ሽንት ቤትና የበዛ የኑሮ እንግልት፣ የጤና እክል ተጨምሮበት እኚህን እናት ለአካልና ለሥነ-ልቦና ስቃይ ዳርጓቸው እንደነበረ የዛሬውን የልደታ በንነት መንደር በስስት እየተመለከቱ እንዲሁም የትናቱን ጭንቅ እያስታወሱ ኃዘንና ደስታ በተቀላቀለበት ስሜት አጫውተውናል፡፡

የወይዘሮ አበባ ካሳ ሕይወትም የዚሁ ከባድ መከራ አካል ነበር። የዝናብ ውሃ ከጣሪያ ሲንጠባጠብ፣ የቆሻሻ ፈሳሽ ደግሞ በደጃፍ በኩል ሲፈስ፣ አሥር ነፍሳት በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ተጨናንቀው ሌሊቱን የሚያድሩበት ሕይወት ለብዙዎች የቆየ መራራ እውነት ነበር። ልጆቻቸውን በጠባቧ ክፍል ማሳደር አቅቷቸው ደጅ የሚያደሩበት ሁኔታ ከቤት ማጣት በላይ የእናትነት ልብን የሚሰብቅ ጥልቅ ቁስል ሆኖ ቆይቷል።

ይህ ሁኔታ መኖሪያ ቤት የጥላ ማረፊያ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ክብርና ደኅንነት መሠረት መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በአሁኑ ወቅት የወይዘሮ አበባ ሕይወት ሙሉ በሙሉ አዲስ ምዕራፍ ይዟል። ከአንድ ጠባብና ከተበላሸች ክፍል ወጥተው ሙሉ ቁሳቁስ የተሟላለት የሁለት መኝታ ቤት ባለቤት መሆናቸው፣ በሥነ-ልቦናቸውና በጤናቸው ላይ ትልቅ እፎይታን ፈጥሯል። እንደ አልጋ፣ ሶፋና ፍራሽ ያሉ መሠረታዊ የቤት ቁሳቁሶች መሟላታቸውም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩ ዜጎችን በቀጥታ ወደተሻለ የሕይወት ማዕረግ ያሸጋገረ ተግባር ነው። “አሁን እንደ ልቤ ነው የምኖረው” የሚሉት እኚህ እናት ንግግር፣ የሰው ልጅ ክብሩና መብቱ ሲጠበቅለት የሚሰማውን የውስጥ ሰላም ያንጸባርቃል።

የእነዚህ እናቶች እና ቤተሰቦቻቸው ሕይወት በዘላቂነት መለወጥ የመንግሥት የልማት ቃል-ኪዳን ከወረቀት ወደ ተግባር ሲቀየር በዜጎች ሕይወት ላይ የሚያመጣውን እውነተኛ ደስታ፣ ሥነ-ልቦናዊ እፎይታ እና ቃል በተግባር መለወጥ እንደሚችል በግልጽ ያሳያል።

የማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ልማት ጥናት መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር መሳይ ሙሉጌታ፣ የከተማዋ ቦታዎች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው በመሆናቸውና በርካታ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከሰብዓዊ ደረጃ በታች በሆኑ ደካማ ቤቶች ውስጥ በጠበበ ሁኔታ በመኖራቸው ይህንን ታሳቢ በማድረግ መንግሥት ለዜጎች በአምስት ዓመታት ውስጥ ፣ ነጥብ 5 ሚሊዮን ቤቶችን ለመገንባት ቃል በገባው መሠረት እያከናወነ ያለው ልማት ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና በጣም አስፈላጊ ስለመሆኑም ገልጸዋል፡፡

ሰብዓዊ ክብርንና ማኅበራዊ ትስስርን ማዕከል ያደረገ የከተማ መልሶ ማልማት አሠራር፣ የከተሞችን መልክ ከመቀየር ባለፈ የማኅበረሰብ አብሮነትንና ዘላቂነት የሚያረጋግጥ ወሳኝ እርምጃ ነው። ነዋሪዎችን ከለመዱት አካባቢና ከገነቡት ማኅበራዊ ትስስር ሳይበታተኑ በዘመናዊ ቤቶችና አካባቢዎች እንዲኖሩ ማድረጉ የቆየውን የጉርብትና እሴትና አብሮ የመኖር ባህል ሳይደፈርስ እንዲቀጥል ያስችላል። በመሆኑም መንግሥት የዜጎችን ቤትና ተያያዥ ችግሮች ለመቅረፍ በገባው ቃል መሠረት እያከናወናቸው ያሉ ልማቶች የሚበረታቱ ናቸው ይላሉ የከተማ ፕላኒንግ መምህርና ተመራማሪ ብርሃኑ (ዶ/ር)፡፡

“የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የቀጣናው ሀገራት ሊተባበሩበት የሚገባ ጉዳይ ነው”

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ መምህር አበራ ሄብሶ

በስንታየሁ ምትኩ

የኢትዮጵያን ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፤ በአክሱም ዘመነ መንግሥትና ከዚያ በኋላ የተነሱ ስልጣኔዎች መነሻቸው ከባህር ጋር የተቆራኘ ነው። ባህር ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ምንጭ፣ የህልውና መጠበቂያ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ሚዛን ማስጠበቂያና ከውጭ ዓለም ጋር ለሚደረግ ንግድ ማሳለጫ ሆኖ አገልግሏል።

ከባህሩ እየራቀች በመጣች ቁጥር ደግሞ የኢኮኖሚ፣ የዲፕሎማሲና ራስን የመከላከል አቅሟ እየተዳከመ መምጣቱን በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የታተመው “የሁለት ውኃዎች ዐቢይ ስትራቴጂ” ሰነድ ያሳያል።

የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያውና በናይል ጂኦፖለቲካ ላይ ሁለት መጽሐፍት የጻፉት ስለአባት ማናዬ፣ “ቶፕ አፍሪካ ኒውስ” በተባለው የዲጂታል ሚዲያ ላይ፣ “የኢትዮጵያ የባህር መልሶ ማግኘት ቀጣናዊ እና ዓለምአቀፋዊ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞች” (Regional and Global Strategic Benefits of Ethiopia’s Quest to Regain Sea Access) በሚል ርዕስ ያሰፈሩት ጽሑፍ ይህንኑ ሀሳብ ያጠናክራል። በማብራሪያቸው፣ “የባህር በር ለኢትዮጵያ የህልውናና የልማት መሠረት ነው። ኢትዮጵያ ከባህር ጋር ስትገናኝ ብልጽግናን አግኝታለች፤ ከባህር ስትቆረጥ ደግሞ ተዳክማለች። ካላት ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር፣ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ረጅም ታሪክና የተፈጥሮ ሀብት አኳያ ኢትዮጵያ ለቀይ ባህርና ለአፍሪካ ቀንድ ደህንነትና መረጋጋት ወሳኝ ሀገር ናት። ስለዚህ የባህር በር ጥያቄዋ ለከርከር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም” ይላሉ።

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ መምህር አበራ ሄብሶም የባህር በር ለአንድ ሀገር ህልውና ወሳኝ መሆኑን ያሰምሩበታል። ሀገራት የባህር በርን ኢኮኖሚያዊ ነጻነታቸውን፣ ሀገራዊ ደህንነታቸውንና ሉዓላዊነታቸውን ለማስጠበቅ ይጠቀሙበታል። ኢትዮጵያ ኤርትራ ራሷን ችላ ሀገር እስከሆነችበት እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ከውጭው ዓለም ጋር የምትገናኝበት የራሷ የባህር በር ነበራት፤ የራሷንና የአካባቢውን ደህንነት የሚጠብቅ ጠንካራ የባህር ኃይልም ገንብታ ነበር። የባህር በሯን ስታጣ የባህር ኃይሏም አብሮ ፈርሷል፤ የኢኮኖሚና የደህንነት ስጋትም ተጋርጦባታል ይላሉ።

የደህንነት ስጋቱን ብናነሳ፤ የአፍሪካ ቀንድ በዓለም አቀፍ ንግድ ካለው ስልታዊ ጠቀሜታ የተነሳ ፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ጃፓንና ቻይናን ጨምሮ በርካታ ኃያላን ሀገራት የጦር ሰፈር አቋቁመውበታል። “ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ” በ2014 ዓ.ም ባሳተመው ጥናት ላይ “የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፤ ከጎረቤትና ከአረብ ባህረ ሰላጤ ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት” በሚል ርዕስ መጣጥፍ ያቀረቡት የአዲስ አበባ



ፎቶ፦ ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ ባህር በር ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ሁሉም ሊረባረብ ይገባል

ዩኒቨርሲቲ መምህር አስናቀ ከፋለ (ዶ/ር) ይህንን በግልፅ አስቀምጠውታል።

“ቀጣናውንና የኢትዮጵያን የፀጥታ ሁኔታ ስንመለከት በጅቡቲ የውጭ ሀይሎች የጦር ሰፈር መስፋፋት ነጂ አንድምታ እንደሚኖረው መገንዘብ ይገባል። በአንድ በኩል የወታደራዊ የጦር ሰፈሮች መበራከት ተቀናቃኝ ሀይሎች ግጭታቸውን ወደ አካባቢው ሊያመጡ የሚችሉበትን እድል ስለሚፈጥር ለቀጣናው የስጋት ምንጭ ነው። በሌላ በኩል በቀጣናው የሰፈሩ የውጭ ሀይሎች በግጭቶች ውስጥ የሚሳተፉበት እድል ከተፈጠረ ግጭቶቹ ይበልጥ እንዲወሳሰቡ ያደርጋሉ።”

የባህር በር አለመኖር ምን ያህል በደህንነት ላይ ስጋት እንደሚደቅን አሁንም የኢትዮጵያን ታሪክ ወደኋላ በማየት መረዳት ይቻላል። በ1928 ዓ.ም ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን ለማስከበር ስትዋጋ ጅቡቲን ይዝዙ የነበሩት የፈረንሳይ ባለሥልጣናት ኢትዮጵያ የገዛቻቸውን ወሳኝ የጦር መሣሪያ ጭነቶች አግደዋል። የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው ስለአባት በጽሑፋቸው እንደሚያትቱት፣ የባህር በር ተደራሽነት በሌላ ኃይል እጅ መሆኑ በወሳኝ ጊዜ የሀገርን ደህንነት ሊጎዳ እንደሚችል ይህ ክስተት ያሳያል።

ከኢኮኖሚ አንጻርም አስተማማኝ የባህር በር ለኢትዮጵያ እድገት አስፈላጊ መሆኑን የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ ያነሳሉ። ዛሬ በዓለም ላይ እስከ 75 በመቶ የሚደርሰው ንግድ የሚከናወነው በባህር ነው። የባህር በር የሌላት ኢትዮጵያ ግን የወጪና ገቢ ንግዷን በባህር በር ባላቸው ጎረቤቶቿ ላይ ጥገኛ ሆና ታከናውናለች። የንግዱ አብዛኛው ከፍል በጂቡቲ በኩል ስለሚያልፍ ለወደብ አገልግሎት የምትከፍለው ገንዘብ እጅግ ከፍተኛ ነው። ለወደብ ኪራይ አገልግሎት በቢሊዮን ዶላር የሚገመት ወጪ በዓመት ታወጣለች። ይህ ቀላል ገንዘብ አይደለም። የኢኮኖሚ ነጻነትንና የሀገርን የመቋቋም አቅም አደጋ ላይ የሚጥል ሸክም ነው።

ለሌሎች ሀገራት ምን ጥቅም ያስገኛል?

የባህር በር ጥያቄ የኢኮኖሚ ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ የሀገር አንድነትንና የረጅም ጊዜ ሉዓላዊነትንም ይነካል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ብዝሃነት ያላቸው ሀገራትን አስተሳስረው የሚይዙት የጋራ ጥቅሞች፣ የጋራ እጣ ፈንታና የጋራ ሀብቶች ናቸው። የባህር በር ተደራሽነት ከእነዚህ ሀብቶች አንዱ ነው። ሀገራት ወሳኝ መሠረተ ልማት ወይም የኢኮኖሚ መሠረት ሲኖራቸው አንድነታቸውን ለመጠበቅ ጠንካራ ተነሳሽነት አላቸው። እነዚህ ሀብቶች በሌሉበት ወይም በውጭ ኃይል ቁጥጥር ሥር በሆኑ ጊዜ ደግሞ የመበታተን አደጋ ይሰፋል ይላሉ የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው ስለአባት።

የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው እንደሚሉት፣ የቀይ ባህር አካባቢ ለረጅም ጊዜ ዘርፈ ብዙ የፀጥታ ተግዳሮቶች የሚታዩበት ነው። ከአልሸባብ እና የመሳሰሉ ቡድኖች የሚመጣ ሽብርተኝነት፣ በኤደን ባህረ ሰላጤ የሚፈጸም የባህር ላይ ውንብድና፣ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ እንዲሁም የጦር መሣሪያና የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር የአካባቢው ስጋቶች ናቸው። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ትልቋ ሀገር እንደመሆኗ በሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች እንዲሁም አሜሪካንን ጨምሮ ከታላላቅና መካከለኛ ሀይል ያላቸው ሀገራት ጋር ሽብርተኝነትን ለመከላከል በምታደርገው ጥረት ለቀጣናው መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገች ነው።

ሆኖም ኤርትራ ነጻነቷን ካወጀች በኋላ ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ በመሆኗ ከሦስት አሥርት ዓመታት በላይ የደህንነት አስተዋጽዖ በየብስና በአየር ላይ ብቻ የተገደበ ሆኗል። አስተማማኝ የባህር በር ማግኘት በቀይ ባህር ላይ የሚነሱ ስጋቶችን የመከታተልና ምላሽ የመስጠት አቅሟን ያሳድጋል። የባህር ላይ ውንብድናን እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል የሚደረገውን ዓለም አቀፍ ጥረትንም ያጠናክራል። ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት፣ በአፍሪካ በሕዝብ ብዛት ሁለተኛ ለሆነችው ሀገር የኢኮኖሚ እድገትን ያፋጥናል፤ ቀጣናዊ ውህደትንም ያነቃቃል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የፖለቲካ ማዕከል ናት። አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ ከመታገል ጀምሮ ወደ አንድነት እንዲመጡ በማስተባበር የመሪነት ሚና ተጫውታለች። በአሁኑ ወቅትም በከተማ ልማት፣ በግብርና ምርታማነትና በኃይል አቅርቦት ተመሳሳሉት እየሆኑ ነው። ከሕዝብ ብዛቷና ከእምቅ ሀብቷ አንጻር የባህር በር ማግኘቷ ጥቅሙ ለጎረቤት ሀገራትም የሚተርፍ መሆኑን የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ፣ “የኢትዮጵያን የባህር በር ጥያቄ የቀጣናው ሀገራት ለራሳቸው ብሔራዊ ደህንነትና የኢኮኖሚ እድገት መረጋገጥ ምላሽ የሚሰጡበትና ሊተባበሩበት የሚገባ ጉዳይ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም” ሲሉ ገልጸውታል።

ኢትዮጵያ የባህር በር ቢኖራት ጎረቤት ሀገራት የሚፈልጉትን ከሀገራቱ በማግኘት ገቢያቸውን ማረጋጋትና የሕዝባቸውን ኑሮ ማሻሻል ይችላሉ። የአሸባሪዎች እንቅስቃሴና ውስብስብ ዓለም አቀፍ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ አሰላለፎችን መቋቋም የሚቻለው በጋራ ሲሰሩ ብቻ እንደሆነ ያሰምሩበታል።

ኢትዮጵያ ከኤርትራ፣ ሶማሊያ፣ ጂቡቲ፣ ኬንያ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ጋር ድንበር ብቻ ሳይሆን ታሪክ፣ ቋንቋና ባህል እንዲሁም ተመሳሳይ ማንነት ያላቸውን ሕዝቦች ትጋራለች። ስለዚህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የጎረቤቶቿም ብሔራዊ ጥቅም መሆኑን እንዲገነዘቡ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን በማጠናከር መስራት እንደሚገባ የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ ያነሳሉ። ኢትዮጵያ በሱዳን፣ በደቡብ ሱዳንና በሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍላለች፤ አሁንም እየከፈለች ነው። የባህር በር ቢኖራት የእነዚህ ሀገራት ብሔራዊ ህልውና የበለጠ ይጠበቃል፤ የንግድ ልውውጥና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውም ያድጋል።

የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው ስለአባት እንደሚሉት ኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፈንታዋን ለማረጋገጥ የቀይ ባህር መስመርን ስትራቴጂካዊ ክብደት፣ የመካከለኛው ምሥራቅና የዓባይ ተፋሰስ ጂኦፖለቲካዊ ጫናዎችን፣ ከባህር በር አልባነት የሚመነጩ ተጋላጭነቶችንና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ከተመሠረተ ትብብር የሚገኙ ዕድሎችን ያገናዘበ ስትራቴጂ መንደፍ አለባት። ስትራቴጂው የባህር በር ለህልውናዋ ወሳኝ መሆኑን፣ እንዲሁም ለዓለም አቀፍ የባህር ደህንነት፣ ለቀጣናዊ ሰላምና ለኢኮኖሚያዊ ውህደት የሚጫወተውን ሚና ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ የማሳመን አስፈላጊነት ያካተተ መሆን አለበት። ቀይ ባህር ለኢትዮጵያ ተራ የውሃ አካል አይደለም፤ የኢኮኖሚ እስትንፋሷን፣ የብሔራዊ አንድነቷንና የረጅም ጊዜ ደህንነቷን የሚመለከት ነው።

“በመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ በታሪክና በተጽዕኖ ከኢትዮጵያ ያነሱ ቢሆኑም በጋራ ብሔራዊ ፍላጎታቸው ዙሪያ በመሰለፍ ሀገራቸውን ያሻገሩ ሀገራት አሉ” የሚሉት የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ፣ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ሕዝቡም ነገን አሻግሮ ማየት ይጠበቅበታል። ጉዳዩን የፖሹው ፓርቲ ወይም የመንግሥት አጀንዳ ብቻ አድርጎ ማየት አይገባም። ቀደም ባሉት ዓመታት የባህር በርን አስፈላጊነት በትክክል ሳንረዳ፣ ወደፊት አሻግረን ሳንመለከት በመቅረታችን ዛሬ መስዋዕትነት እየከፈልን ነው። ጠንካራና ሉዓላዊ ሀገር ለመገንባት ጉዳዩ ወሳኝ መሆኑን በመረዳት መንግስትና ህዝብ ተባብረው መስራት፣ ጥያቄውም በዲፕሎማሲ፣ በጋራ ተጠቃሚነትና በትብብር መፍትሄ እንዲያገኝ መረባረብ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ አስተማማኝ የባህር በር ብታገኝ ጥቅሙ ለእሷ ብቻ ሳይሆን ለመላው ቀጣናም የሚዳረስ ነው፤ ገቢያ ይረጋጋል፣ ንግድ ይስፋፋል፣ ሽብርተኞችንና የባህር ላይ ወንበዴዎችን የመከላከል አቅም ይጠናከራል። ለዚህም በአንድ በኩል መንግሥት ጥበብ የተሞላበት ዲፕሎማሲያዊ ስትራቴጂ ሊነድፍ ይገባል፤ በሌላ በኩል ምሁራን፣ ሚዲያዎችና መላው ሕዝብ የጉዳዩን ክብደት ተገንዝበው በአንድነት ሊቆሙ ይገባል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

የአዲስ አበባ ከተማ ተማሪዎች የዲሲፒሊን መመሪያ ምን ይላል?

(ክፍል አንድ)

አብርሃም ንጉሴ (ዐቃቤ ህግ)

ተማሪዎች በትምህርት ቤት በጥሩ ሥነ-ምግባር በመታነጽ ለራሳቸው ለማህበረሰባቸው እና ለሀገራቸው ጠቃሚ ዜጋ ሆነው እንዲቀረጹ እና አሁን እየታየ ያለው የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ችግር በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ የመጣ እና ይህንን ችግር ከወዲሁ ማስተካከል አስፈላጊ በመሆኑ የተማሪዎች የዲሲፒሊን መመሪያ ቁጥር 150/2016 ወጥቷል።

በተጨማሪም ተማሪዎች መልካም ምግባርን በመላበስ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ተቆርቋሪ፣ ችግር ፈችና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ዜጎች ሆነው እንዲቀረጹ ለማስቻል፣ የትምህርት ቤታቸውን ህግና ደንብ በማክበር በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻልም መመሪያው ፋይዳው የጎላ ነው።

በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደቱ ሳይታወክ እና የትምህርት ቤቱ ሠላምና ደህንነት ተጠብቆ እውቀት የሚቀስሙበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ሊያወጣ ችሏል።

የተማሪዎች መብት እና ግዴታዎች

በሌላ መልኩ የተማሪዎች መብትና ግዴታ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሰረት ተማሪዎች በርካታ መብቶች እንዳሏቸው ተደንግጎ እናገኛዋለን። ከእነዚህ በጥቂቱ ተማሪዎች የመማር፣ ጠይቆ የመረዳትና የማወቅ፣ ከማንኛውም ዓይነት የአካልና ሥነ ልቦና ጥቃቶች የመጠበቅ፣ በትምህርት ቤቱ የትምህርት ግብዓቶች የመጠቀም ወይም አገልግሎት የማግኘት፣ የትምህርት ውጤትና የምስክር ወረቀት በወቅቱ የማግኘት መብት አላቸው።

ስርአትና ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል እና ትምህርት ቤት የመማር፤ ሃሳባቸውን የመግለጽና የመደመጥ መብት፤ የግል ምስጢራዊ ጉዳዮቻቸውን የመጠበቅ፣ ፆታን መሰረት ካደረገ ጥቃት የመጠበቅ፣ የትምህርት ቤቱን ደንብና መመሪያ የማወቅና የማግኘት፣ ከመምህራን ድጋፍና እርዳታ የማግኘት፣ የሚደርስባቸውን በደልና ቅሬታ ማቅረብ የተማሪዎች ሌላው መብታቸው ነው።

ስለመምህራን የማስተማር ክህሎት



በሚዛናዊነት የመገምገም፤ አስተያየት ሲጠየቁ የመስጠት፣ ከመማሪያ ክፍል ውጭ የሚከናወኑ የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ የመሳተፍ፣ ለተማሪዎች ከሚሰጠው ልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች የመምረጥና የመመረጥ፣ የጤና ዕርዳታ የማገኘት፣ ልዩ ፍላጎታቸውን መሰረት ያዳረገ አገልግሎት የማግኘት እና ከጥቃት የመጠበቅ መብት፣ በትምህርት ቤት የዕቅድ ዝግጅትና የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ በተወካዮቻቸው አማካኝነት የመሳተፍ መብቶች እንዳሏቸው በግልጽ ተደንግጓል።

የተማሪዎች ግዴታዎች

ይህ እንዳለ ሆኖ ተማሪዎች መብት ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቤት ጊቢ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ተማሪ የሚከተሉትን ግዴታዎች እንዳሉበት በአንቀጽ 6 ስር ተደንግጎ ይገኛል።

ከእነዚህ በጥቂቱ በሰንደቅ ዓላማ ሥነ ስርአት ላይ የመገኘትና የመዘመር፤ በመማሪያ ክፍል የመገኘት፣ ያለበቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት አለመቅረት፣ በክበባት የመሳተፍ፣ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በጥሞና የመከታተል መብት (ግዴታ) አለባቸው።

የክፍል ሥራ፣ የቤት ሥራ፣ የቡድን ሥራ፣ ሠርቶ አጠናቅቆ በጊዜው የማቅረብ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎችና መምህራን በአግባቡ የሚሰጡትን ድጋፍ ምክርና መመሪያ የመፈፀም፣ ሴት ወይም ወንድ ተማሪዎችን ከመተንኮስ፣ ከማስፈራራት ከመድፈር ከመደባደብና ሰብአዊ መብታቸውን ከመጋፋት የመቆጠብ፣ ከማንኛውም የቡድን ጸብ አምባጓሮና ጉልበተኝነት ተግባር ራስን ማቀብ የሚጠቀሱ መብቶቻቸው ናቸው።

ለመምህራን፣ ለሠራተኞች፣ ለትምህርት አመራሮችና ለጓደኞቻቸው ተገቢውን ክብር የመስጠት፣ አለመዘለፍ፣ አለማንጓጠጥ፣ አለመስደብ፣ አለመዛት፣ አለማንቋሸሽ እና የመሳሳሉት፣ የመማሪያ መጽሐፍትን ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎችን በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም አለማበላሸት፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት የመጠበቅ/መቀመጫ ወንበሮችን፣ የመማሪያ ክፍሎችን፣ መስኮቶችን፣ ምድረ ግቢውን በንፅህና የመያዝና የመንከባከብ/፣ ማንኛውንም በአካልና በጤና ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሣሪያ ይዞ አለመገኘት ግዴታ አለባቸው።

ማንኛውንም አይነት የኃይማኖትና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች አለማካሄድ፣ በትምህርት ቤቱ ያልተፈቀደ ስብሰባዎች ላይ ያለመሳተፍ፣ የግልና የጋራ ንፅህናን የመጠበቅ፣ የደንብ ልብስ አለባበስና የፀጉር አያያዝ ማስተካከል፣ የትምህርት ቤቱን ዩኒፎርም/የደንብ ልብስ አዘውትሮ መልበስ፣ አካል ጉዳት ያለበት ተማሪን ጉዳቱን መሰረት ያደረገ አድልዎ አለመፈጸም በመመሪያው የተቀመጡ የተማሪዎች ግዴታዎች ናቸው።

መንግስት ከሚያወጣው እና ህጋዊ በዓላት ውጭ አለማክበር/ዋተር ዴይ፤ ከሬዚ ዴይ የመሳሳለት በትምህርት ሰዓት ያለበቂ ምክንያት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ አለመዟዟር፣ የትምህርት ቤቱን አጥር ዘሎ አለመውጣት ወይም አለመግባት ወይም ዕቃ በአጥር አለመቀበልና አለማቀበል፣ ሲጋራ አለማጨስ መጠጥ ጠጥቶ አለመገኘት ጫትና ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን አለመጠቀም፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብና አራሱን ከኤች አይ ቪ ኤድስ የመከላከል፤ የስርቆት ወንጀል አለመፈፀም፣ ፆታና መኮረጅ ቁማር መጫወት ከመሳሰሉ ሕገ ወጥ ድርጊቶችና ከሌሎች ጥፋቶች መራቅ እና መታወቂያ ይዞ የመገኘት፤ ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ እንዳለበት ልብ ማለት ያስፈልጋል።

የተማሪዎች ዩኒፎርም ወይም የደንብ ልብስ አጠቃቀም

በተመሳሳይ መልኩ የተማሪዎች ዩኒፎርም ወይም የደንብ ልብስ አጠቃቀም በተመለከተ በአንቀጽ 7 ላይ ተመላክቷል። የመንግስት ትምህርት ቤቶችን በተመለከተ ትምህርት ቢሮ በሚወስነው የጨርቅ ዓይነት፣ ጥራት እና ቀለም እና ስፋት ዲዛይን መሆን ይኖርበታል። መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ዩኒፎርም ወይም የደንብ ልብስ የጨርቅ ዓይነት፤ ጥራት እና ቀለም በትምህርት ቤቱ አስተዳደር፤ ተማሪዎችና ወላጆች የጋራ ስምምነት ይወሰናል።

የወንድ ተማሪዎች የደንብ ልብስ የሱሪ ቬል ስፌት ኖርማል ወይም ከ8 ኢንች ያላነሰ መሆን አለበት። የሴት ተማሪዎች የደንብ ልብስ አዘገጃጀት በተመለከተ ደግሞ የቀሚስ መጠን ከጉልበት በታች ያለውን 2/3ኛ የእግር ክፍል የሚሸፍን መሆን እንዳለበት በመመሪያው ተደንግጓል። ከተወሰነው የደንብ ልብስ ዓይነት፤ ጥራትና ቀለም ውጪ መጠቀም፣ ማንኛውንም ዓይነት ጽሑፍ ማሳተም፤ ሌላ የጨርቅ ዓይነት ቀጥሎ ማሰፋት እና ያልተፈቀደ የደንብ ልብስ ዓይነት፣ ቅርፅና ይዘት መጠቀም የተከለከለ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ የማታ እና የርቀት ተማሪዎችን ግን አይመለከትም።

የፀጉር አቆራረጥ፣ አያያዝ እና የጆሮ ጌጥ አጠቃቀምን አስመልክቶ በአንቀጽ 8 ተመላክቶ እናገኛለን። በመሆኑም ማንኛውም ተማሪ የፀጉርን ንፅህና መጠበቅ አለበት። ማንኛውንም አይነት የፀጉር ቀለም መቀባት የለበትም። ወንድ ተማሪ ፀጉሩን ከ3 ቁጥር የበለጠ ወይም ከ1 ሴ.ሜትር የበለጠ ማሳደግ የለበትም። ሴት ተማሪ ፀጉሯን ከማበጠርና ከማስያዝ ወይም ሹሩባ ከመሰራት ውጪ ሌሎች ማናቸውንም አይነት የፀጉር አሰራሮችን መሰራት የለባትም። ወንድ ተማሪ የአንገት፣ የእጅ ሀብል ቀለበት ጉትቻ ማድረግ እንዲሁም ጥፍር ማሳደግ የለበትም። ሴት ተማሪ የአንገት ሀብል፣ የእጅ ጌጥ፣ የእግር ጌጥ፣ ከጋብቻና ከቃል ኪዳን ውጪ የሆነ ቀለበት፣ ከጆሮ ውጭ የትኛውም የሰውነት አካል ላይ ለማጌጥ ተብሎ ማስበሳትና ጌጦችን ማድረግ የለባትም።

የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

ሌላው በዚህ መመሪያ የምናገኘው ነጥብ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ነው። በዚህ መሰረት የዲሲፕሊን ቅጣት መሰረታዊ ዓላማ የትምህርት ቤቱን የመማር ማስተማር ሥራ ውጤታማ ለማድረግ ሲሆን ተማሪው በፈጸመው ጥፋት ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት ተጸጽቶ ወደፊት ብቁ እና ታማኝ ዜጋ ለመሆን እንዲችል ለመርዳት፣ ለማረምና ለማስተማር እንዲሁም የማይታረም በሚሆንበት ጊዜ መማር ማስተማሩ እንዳይስተጓጎል ከትምህርት ቤት ለማሰናበት እንደሆነ በአንቀጽ 9 ላይ ተደንግጓል።

ቀጣዩን ክፍል ሳምንት ይዘንላችሁ እንቀርባለን።

የቱሪዝሙ ተደማሪ አቅም

• የወንዝ ዳርቻ ልማቱ አዲስ አበባን ከቱሪስት መሸጋገሪያነት ወደ መዳረሻነት እየቀየረ እንደሚገኝ ተገልጿል

በስንታየሁ ምትኩ

አቶ ወርቁ ተሾመ በአዲስ አበባ ቦሌ ቡልቡላ አካባቢ ነዋሪ ናቸው። በፒያሳና አራት ኪሎ አካባቢ ለበርካታ ዓመታት የሚሰሩ በመሆናቸው አካባቢውን በደንብ ያውቁታል። አቶ ወርቁን ያገኘናቸው ሰሞኑን በተመረቀው ከቀጨኔ፣ ባምቢስ እስከ ሰላም መንገድ በሚዘልቀው የወንዝ ዳርቻ ልማት በአፍንጮ በር አካባቢ የተሰራውን እየተመለከቱ፤ በደስታና በተመስጦ ተውጠው ለማስታወሻ ፎቶ ሲነሱ ነበር።

ከጥቂት ዓመታት በፊት የነበረው የወንዙ ዳርቻ ሁኔታ ከአሁኑ ጋር ፈፅሞ ለንፅፅር የሚቀርብ አይደለም። ጣሪያና ግድግዳቸው የፈራረሱ፣ ያረጁ፣ በፕላስቲክ የተወታተፉና የተጨናነቁ ቤቶች የሚገኙበት፣ ወንዞቹም የቆሻሻ መጣያ በመሆናቸው ተፈጥሯዊ ይዘታቸውን አጥተው በከፍተኛ ደረጃ ተብከለው የሚታዩበት፤ አካባቢውም በጥሻ ተሸፍኖ ለደህንነት ስጋት ነበር። አሁን ግን ይህ ሁሉ ታሪክ ሆኗል፤ የወንዝ ዳርቻው ፀድቶ ገለጥ ብሎ እንዲታይ ተደርጓል፤ ከአካባቢው የኮሪያ ዘማቾች መታሰቢያ ፓርክ ጋር ተሰናስሎም ለምታል ይላሉ።

“የወንዝ ዳርቻው በጣም የሚያስገርም ነው፤ የነበረው ቆሻሻ ተወግዶ ውብና ማራኪ ሆኖ ሰዎች የሚዝናኑበት ሆኗል። በአካባቢው ጊዜ ማሳለፍና ማለፍ መንፈስን ያድሳል” ይላሉ አቶ ወርቁ። በአካባቢው በሚገኘው አላቅሷ መስጂድ ለመስገድ በመጡበት አጋጣሚ የወንዝ ዳርቻውን እየነበኙ እንደሆነ የነገሩን ግለሰቡ፣ ልማቱ ለአካባቢው ብቻ ሳይሆን ለመስጂዱም ግርማ ሞገስ እንዳጎናፀፈው ይናገራሉ። “ከቤተሰብ ጋር መጥቼ አውቃለሁ፤ አይተነዋል። ድሮ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ የውጭ እንግዶች ሽራተን ሆቴልን ‘በቆሻሻ መሀል የበቀለ ፅጌረዳ’ ይሉት እንደነበረ አውቃለሁ። አሁን ግን ፅጌረዳ በሁሉም አካባቢ ነው የሚታየው። የወንዝ ዳርቻዎች ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባ እንደ ፅጌረዳ ውብና ማራኪ ሆኗለች” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

በወንዝ ዳርቻ የተሰሩ መሰረተ ልማቶች ጥራትና ውበት ከቃላት በላይ መሆናቸውን የሚገልጹት አቶ ወርቁ፣ በውስጡ ምቹ የመኪና ማቆሚያዎች፣ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶች እንዲሁም የመሮጫ ትራኮች ተካትተው መሰራታቸውን ያደንቃሉ። ቀደም ሲል የውጭ ዜጎች ወደ ከተማዋ ሲመጡ መዚየሞችን ካልሆነ በቀር በቀጥታ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች ይጓዙ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ግን ነዋሪዎች በእግራቸው እየተንቀሳቀሱ፣



ፎቶ፦ በዳዊት ቦጋለ
ነዋሪዎች በአፍንጮ በር አካባቢ ባለው የወንዝ ዳርቻ ሲዝናኑ

በተዘጋጁ ማረፊያዎች አረፍ እያሉ ንፁህ አየር የሚወስዱበት ውብ የመዝናኛ ስፍራ ማግኘታቸውን ይናገራሉ። ይህ ሁኔታ ለውጭ ቱሪስቶችም ሀገራችንን በተሻለ ሁኔታ የሚያውቁበትና ለከተማዋ ገቢ የሚገኝበት በመሆኑ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው አስረድተዋል።

በአፍንጮ በር በሚገኘው የወንዝ ዳርቻ ድልድይ ስር ባለ መተላለፊያ ላይ የተዘጋጁ ወንበሮች ላይ አረፍ ብሎ ሲዝናና ያገኘነው ወጣት ደርበው ሀይሉ በበኩሉ፣ ነዋሪነቱ በሸገር ከተማ ለገጣፎ አካባቢ ቢሆንም፣ የእረፍት ጊዜውን ለማሳለፍ በአካባቢው መገኘቱን ይናገራል። ወጣት ደርበው በወንዝ ዳርቻ ልማት ስራ በግንበኛነት በመሳተፍ የራሱን አሻራ አኑሯል። የድልድዩ ስር በሥነ ጥበባዊ ስዕሎች አምሮና ተውቦ ይታያል። ግራና ቀኝ የሚታየውም ፅዱና ውብ የሆነ ነገር ብቻ ነው። ለምለም ሳር፣ የተለያዩ አበቦች፣ ምቹ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶች፣ መሮጫ ትራክ እንዲሁም ከታች የወንዙ ውሃ ለስለስ ያለ ድምፅ ይሰማል።

“አካባቢውን ከመልማቱ በፊት አውቀዋለሁ። እንኳን ሰዎች ቁጭ ብለው ሊዝናኑበት ለማለፍ የሚቀፍ ስፍራ ነበር። በወቅቱ ወደ ስራው ስንገባ ለዘመናት መጸዳጃ እና የቆሻሻ መጣያ ሆኖ በመቆየቱ ለሳምንታት ታመን ነበር” የሚለው ወጣቱ፣ የአሁኑን ውበትና ፅዳት በማየቱ ከለገጣፎ ድረስ መምጣቱን ይናገራል። “የሚያረካ ስራ ነው የተሰራው፤ የዚህ አካል በመሆኔ እድለኛ ነኝ። ከቤተሰብና ከጓደኞቻችን ጋር በመሆን የምንዝናናበት ስፍራ ሆኗል” በማለት የተሰማውን ስሜት በደስታ ገልጿል።

ወ/ሮ ኤደን ወንድሙ የተወለዱትና ወልደው ከብደው የሚኖሩት በአፍንጮ በር አካባቢ ነው። ውብና ማራኪ ሆኖ በተሰራው የወንዝ ዳርቻ ሁለት ልጆቻቸውን ይዘው ሲያጫውቱና ሲዝናኑ ነበር ያገኘናቸው። አካባቢው ከዚህ በፊት የሚያስፈራ እንደነበርም ያነሳሉ።

“ወንዙ በጣም ቆሻሻ በመሆኑ ለምንም አገልግሎት አይውልም ነበር። ዝናብ በጣለ ቁጥር ስለሚሞላ ነዋሪዎች በስጋት ነበር የሚኖሩት፤ በንብረት ላይም ጉዳት ይደርስ ነበር። አካባቢው ጫካ ስለነበር ሌቦች ስለሚደበቁበት ያስፈራም ነበር። አሁን ግን ፅዱ ሆኗል፤ አየሩ ንፁህ ነው። እኛ ብቻ ሳንሆን ልጆቻችን እየበረቁ የሚውሉበትና የሚያድጉበት አካባቢ ተፈጥሯል፤ በጣም ደስ ይላል።” ሲሉ የተሰማቸውን ስሜት ይናገራሉ።

ከዚህ በፊት በአካባቢው ካፌዎች እንዳልነበሩና ለመዝናናት ረጅም ርቀት እየሄዱ እንደነበር የሚናገሩት ወ/ሮ ኤደን፣ አሁን በአቅራቢያቸው ካፌዎች መከፈታቸውና ከምንም በላይ በጥሻ ተከብቦ የነበረው አካባቢ ግልጥልጥ ብሎ ንጹህና ሰላማዊ አካባቢ መፈጠሩ እንደሚያስደስታቸው ነው የገለፁልን።

አዲስ አበባ ከተማ የብዙዎች ታሪክና ትዝታ የተከተበባቸው በርካታ ወንዞች አሏት። እነዚህ ወንዞች የህዝብ ቁጥር ሳይጨመርና የመኖሪያ አካባቢ ሳይስፋፋ ለመጠጥ ውሃ፣ ለግብርና ስራ እና ለተለያዩ የመዝናኛ አገልግሎቶች ይውሉ ነበር።

ከጊዜ በኋላ በወንዙ ዳርቻ ሰዎች መኖሪያ ቤቶችን በብዛት እየሰሩ መኖር ሲጀምሩ፣ የሸንት ቤት ፍሳሽን ጨምሮ የተለያዩ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት ስፍራ እየሆነና እየተበከሉ መጥተዋል። መኖሪያ ቤቶች ከወንዙ ዳርቻ ተጠግተው የተገነቡ በመሆናቸው በክረምት ወቅት ወንዞች ሲሞሉ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳቶችን ያስከትሉ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት ወንዞችን ወደ ተፈጥሯዊ ይዘትና መልካቸው ለመመለስ፣ የከተማዋን የአረንጓዴ ሽፋን ለመጨመር፣ ነዋሪዎች ንፁህ አየር የሚያገኙበት፣ የሚያርፉበት፣ የስራ ዕድልና ገቢ የሚያገኙበት ሁኔታ ለመፍጠር የወንዝ ዳርቻ ልማት እየተከናወነ ይገኛል። በርካታ የከተማዋ ወንዞችም ፅዱ፣ አረንጓዴና ለዓይን ማራኪ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

አሁን ላይ የተፈጥሮና የሰው ልጅ ጥበብ የተዋሃዱባቸው የመዝናኛ፣ የስራና ንግድ፣ የቱሪዝም ስፍራዎች ሆነዋል።

ሰሞኑን በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተመረቀው የእንጦጦ ፒኮክ የወንዝ ዳርቻ ልማት አካል የሆነው፤ ከቀጨኔ፣ አምባሳደር፣ ኢሬቻ፣ ባምቢስ እስከ ሰላም መንገድ በሚዘልቀው የወንዝ ዳርቻ ልማት የተሰሩ ስራዎች ሀያው ምስክር ናቸው።

በእነዚህ የወንዝ ዳርቻዎች በእግር ሲንቀሳቀሱ የሚያስደንቀው ነገር የአካባቢው ንፅህና እና የተፈጥሮ ውበት ነው። በአበቦች መዓዛ የተሞላው አየር፣ ዘመናዊና ምቹ የሆኑት የእግረኛ መንገዶች፣ የሩጫና የብስክሌት መስመሮች የዕለት ተዕለት ውጥረትን በቅጽበት ያስረሳሉ። በወንዙ ዳርቻ የሚገኙት ካፌዎችና ማረፊያዎች በዘመናዊ መልኩ የተደራጁ፣ ልዩ ገፅታን የተላበሱና ቀልብን የሚገዙ ናቸው። የዝግጅት ክፍላችን ቅኝት ባደረገበት ወቅት በወንዙ ዳርቻ ባሉ ምቹ የእግረኛ መንገዶች በእርጋታ እየተንሸራሸሩ ውብ ነገሮችን እያዩ ብቻቸውን፣ ከቤተሰባቸው፣ ከጓደኞቸው፣ ከፍቅር አጋሪቸው በሳቅና በጨዋታ የታጀበ ጊዜ የሚያሳልፉ፣ ፎቶ ግራፎችን እየተነሱ ያንን ውብ አጋጣሚ ለትውስታ የሚያስቀሩ በርካታ ሰዎችን

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከህዳር ሲታጠን ወደ ዘላቂ ፅዳት

- **ህዳር ሲታጠን ያስተላለፈው የአካባቢን ንጽህና የመጠበቅ መልዕክት በዘመኑ እውቀት ታግዞ መቀጠል እንዳለበት ተጠቁሟል**

በለይላ መሀመድ

በሀገራችን "ህዳር ሲታጠን" ሲባል መስማት የተለመደ ነው። መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ጉዳዩ በሀገራችን ከተከሰተው የጤና ቀውስ ጋር የተያያዘ ነው። በ1911 ዓ.ም ተከስቶ የበርካቶችን ሕይወት ለነጠቀው "የእስፓኒሽ ፍሉ" ወረርሽኝ የተሰጠውን ማህበራዊ ምላሽ መሠረት ያደረገ ነው።

ይህ ባህላዊ ተግባር በየአካባቢው ያለውን ቆሻሻ ሰብስቦ በማቃጠል በሽታን ከአካባቢው የማስወገድ እምነትን ይዞ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል።

በአዲስ አበባ ጃንሜዳ አካባቢ ተወልደው ያደጉት አቶ መስፍን ተስፋዬ በህዳር ሲታጠን የቆሻሻ አወጋገድ ልምድን ከልጅነት ትዝታቸው ጋር በማያያዝ ያስታውሳሉ። በልጅነታቸው ህዳር ሲታጠን ሲመጣ ወላጆቻቸውን ተከትለው በየአካባቢው ያለውን ቆሻሻ ሰብስበው ማቃጠላቸውን አቶ መስፍን፣ በትውልዱ ዘንድ የተለመደው ይህ ቆሻሻ የማቃጠል ልማድ መነሻው የበሽታ ወረርሽኝን ከመከላከል ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የአካባቢውን ቆሻሻ ሰብስቦ ማቃጠል ህብረተሰቡ እንደ ባህል እየተቀባበለው መጣ። ድርጊቱ በሚከናወንበት ጊዜ አካባቢው በጭስ እንደሚታፈንና እሳቸውም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይህንን ተግባር ያከናውኑ እንደነበር አልሸሸጉም።

ወይዘሮ እየሩሳሌም ንጉስም በተመሳሳይ ይህ ባህል ከቀደምት ወላጆች የተላለፈ መሆኑን በመግለጽ በየዓመቱ በህዳር ወር ቆሻሻን የመሰብሰብና የማቃጠል ልማዱ አሁንም እንደሚስተዋል ገልጸዋል።

ይሁን እንጂ ይላሉ ወይዘሮ እየሩሳሌም፣ በአንድ ቀን ብቻ ቆሻሻን ሰብስቦ ማቃጠል የጽዳት ችግርን ሙሉ በሙሉ አይፈታም። በእሳቸው እምነት ይህ ባህላዊ ልማድ ወደ ዘወትራዊ እና አካባቢን በማይበክል መልኩ መተግበር እንዳለበት ጠቁመዋል።



ፎቶ፦ ከገፀ ድር
ነዋሪዎችን በማሳተፍ የፅዳት ሥራ ሲከናወን

ቆሻሻ ወደ ሀብትነት

የአዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሙላት ተገኘ እንደሚያብራሩት፤ በቀደሙት ዘመናት የተከናወነው "የህዳር ሲታጠን" ተግባር ከወረርሽኝ በሽታዎችን የመከላከል ጥረት ጋር የተያያዘ ታሪካዊ መነሻ አለው። በወቅቱ ቆሻሻ ከበሽታ ጋር ተያያዥነት እንዳለው በመገንዘብ አካባቢን ለማጽዳት የተደረገው ጥረት ተገቢ ቢሆንም በማቃጠል የማስወገድ ዘዴው መቀየር እንዳለበት ያስገነዝባል።

በህዳር ሲታጠን ቆሻሻ እንደሚጎዳና መወገድ እንዳለበት የሄዱበት መንገድ ትክክል ነው። አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ ቆሻሻ ሀብት እየሆነ፣ የብዙዎችን ህይወት እየቀየረና ከፍተኛ ገቢ እያስገኘ ከመሆኑ የተነሳ ያን ጊዜ ባለው አስተሳሰብ መሄድ እንደማያስፈልግ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፤ በዚህም ለውጥ እየመጣ መሆኑን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የኤጀንሲው ዋነኛ ተልዕኮ ከተማዋን ጽዱ ከማድረግ ባለፈ ከቆሻሻ የሚገኘውን ሀብት በተገቢው መንገድ መጠቀምና ለነዋሪዎች ምቹ የአኗኗር አካባቢ መፍጠር ነው። ለዚህም በህዳር ሲታጠን ብቻ ሳይወሰን የጽዳት ባህልን በማስረጽ ረገድ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች በተለያዩ መንገዶች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በተሰሩት ግንዛቤ የመፍጠርና የክትትል ስራዎች የከተማዋ ጽዳት እየተሻሻለ መምጣቱን የጠቆሙት አቶ ሙላት፣ ይህንን ዓላማ ለማሳካት ቤት ለቤት የግንዛቤ ስራዎች፣ በሚዲያ፣ በቶክሾዎችና በሌሎች የማህበረሰብ ተሳትፎ መድረኮች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ሙላት አክለውም፤ አካባቢን ለማጽዳት የሚደረገው ጥረት በአንድ ተቋም ወይም በአንድ ዘመቻ ብቻ የሚፈታ አይደለም። የነዋሪዎችን ተሳትፎ፣ የተቋማትን ቅንጅትና የቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎቶችን በተገቢው ሁኔታ ማደራጀት የሚጠይቅ ነው። ከዚህ አንጻር ከሁለት ሺህ በላይ ባለሙያዎች በየአካባቢው በመንቀሳቀስ የቤት ለቤት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ያከናውናሉ። እንዲሁም ከኤጀንሲው ጀምሮ እስከታች የወረዳ መዋቅሮች ጭምር በቅንጅት በመስራት የነዋሪዎችን ተሳትፎ ለማጠናከር ጥረት እያደረጉ ነው።

በተለይም በትምህርት ቤቶችና በማህበረሰቡ የሚካሄዱ የጽዳትና የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎች ተጨባጭ ለውጥ እያመጡ መሆኑን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ይሁንና በተደራጀ መልኩ የቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት እየተሰጠ ቢሆንም አንዳንድ ነዋሪዎች አሁንም በተገቢው መንገድ የማያስወግዱበት ሁኔታ አለ። በተለይ ከከተማዋ ዳርቻዎች ባሉ አንዳንድ አካባቢዎች ቤት ለቤት ቆሻሻ የሚሰበስብ አካል እያለ ቆሻሻን አሁንም ተገቢ ባልሆነ መንገድ የማስወገድ ልማድ እንዳልተወገደ በክትትል መለየቱን ያስረዳሉ።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ በከተማዋ ቆሻሻን የሚሰበስቡ ከ129 በላይ የሽርክና ማህበራት በየቤቱ በመድረስ ቆሻሻን የማንሳት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። እነዚህ አካላት በሳምንት ሦስት ቀናት በመንቀሳቀስ የነዋሪዎችን ቆሻሻ ያነሳሉ። ከዚህ በተጨማሪም በመንገዶችና በሕዝብ መገልገያ ስፍራዎች ቆሻሻ የሚጣልባቸውን ማጠራቀሚያዎች የማስቀመጥና የማደራጀት ስራ እየተከናወነ ነው።

እነዚህ አገልግሎቶች ቢኖሩም በሌሊት ወይም በጨለማ ቆሻሻን በዘፈቀደ የሚጥሉ አካላት መኖራቸው በጽዳት ስራው ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። ይህንን ለመቀየር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ከክትትልና ከተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ ስርዓት ጋር የበለጠ ማስተሳሰር ያስፈልጋል።

በዚህም ቆሻሻን በዓይነቱ መለየትና በተለያየ ማጠራቀሚያ ማስቀመጥ እንዲቻል እየተሠራ ነው። የሚበሰብስ ቆሻሻ፣ እንደ ፕላስቲክ ያሉ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቆሻሻዎችና ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ አደገኛ ቆሻሻዎች በተለያየ መንገድ እንዲያዙ (ቀለም ባላቸው ከረጢቶች እንዲያስቀምጡ) የማስተማር ስራ እየተከናወነ ነው።

በተለይም ከሚበሰብሰው ቆሻሻ የቤት ውስጥ ማዳበሪያ የማዘጋጀት ልምድን በማስፋፋት በቤት ውስጥ የሚመነጨውን ቆሻሻ መጠን መቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች እየተበረታቱ መሆኑን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ የቤት ውስጥ የምግብ ተረፈ ምርቶችንና ሌሎች በቀላሉ የሚበሰብሱ ቆሻሻዎችን በመለየት ወደ ማዳበሪያ መቀየር በአንድ በኩል የሚወገደውን ቆሻሻ መጠን ይቀንሳል። በሌላ በኩል ለአትክልትና ለእርሻ የሚያገለግል ግብዓት እንደሚያስገኝ ያስረዳሉ።

> **አካባቢን ማጽዳት በዓመት አንድ ቀን የሚከናወን ዘመቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ሊሆን ይገባዋል። ቆሻሻን በአግባቡ መለየት፣ በተመደበለት ስፍራ ማስቀመጥ፣ የሌሎችንም ንጽህና መጠበቅ የእያንዳንዱ ነዋሪ ድርሻ ነው**

ጽዳትን ከዘመቻ ወደ ዕለት ተዕለት ተግባር

የህዳር ሲታጠን ታሪካዊ መነሻ የሚያሳየው ማህበረሰቡ በጋራ ተሰባስቦ አካባቢውን ለማጽዳት ያለውን ፈቃደኝነትና ተሳትፎ ነው። ይህንን አዎንታዊ እሴት በመጠበቅ የማቃጠል ልማዱን ወደ ዘመናዊ የቆሻሻ አያያዝ መቀየር አስፈላጊ ነው። አካባቢን ማጽዳት በዓመት አንድ ቀን የሚከናወን ዘመቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ሊሆን ይገባዋል። ቆሻሻን በአግባቡ መለየት፣ በተመደበለት ስፍራ ማስቀመጥ፣ የሌሎችንም ንጽህና መጠበቅ የእያንዳንዱ ነዋሪ ድርሻ ነው።

ህዳር ሲታጠን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፈው የአካባቢ ንጽህናን የመጠበቅ መልካም መልዕክት በዘመኑ እውቀት ታግዞ መቀጠል አለበት። የቀደሙት ትውልዶች ቆሻሻን በማቃጠል በሽታን ለማስወገድ ቢጥሩም የዛሬው ትውልድ ግን ቆሻሻን በመለየት፣ ወደ ሀብት በመቀየርና አካባቢን በዘላቂነት በመጠበቅ የተሻለ መፍትሔ ማምጣት ይችላል። በተለይም ዜጎች የሚቀረጹባቸው ትምህርት ቤቶች በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ። በትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ የአካባቢ ጥበቃ ክበባት ስለጽዳት ያስተምራሉ። ግንዛቤ ከመፍጠር ባለፈም በሳምንቱ መጨረሻ አርብ ቀን በተግባር ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ያጸዳሉ። ይህም ትውልዱ ስለጽዳት ያለውን አረዳድና ግንዛቤ ያሳድጋል።

በመሆኑም የህዳር ሲታጠን ትልቁ ትርጉም በአንድ ቀን ቆሻሻን በማቃጠል ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ ጽዱ አካባቢን የመፍጠር ኃላፊነትን በሁሉም ልብ ውስጥ ማስረጽ ላይ መሆን እንዳለበት አቶ ሙላት መልዕክት አስተላልፈዋል። በቅርቡም የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲሁም እንደ ከተማ በሁሉም ወረዳዎች ኤጀንሲው ካሰለጠናቸው 12 ሺህ የሚሆኑ የኃይማኖት አባቶች፣ የእድር አመራሮች እና የብሎክ አመራሮች ጋር ጽዳትን ባህል የማድረግ ስራ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ መሆኑንም አቶ ሙላት አመላክተዋል።

የኪነ ጥበብ ጥቁምታ

በአብርሃም ገብሬ

ባሳለፍነው ሳምንት በመዲናችን አዲስ አበባ የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል ዝግጅቶች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የአዳዲስ መጻሕፍት ህትመት እና ምርቃት፣ የሙዚቃ ዝግጅት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

መጻሕፍት

የብርጋዴር ጄነራል ንጉሤ አዱኛን የሕይወት ታሪክና የጦር ሜዳ ጀብዱ የሚያወሳው “የዝምታ ጀብዱ” የተሰኘው አዲስ መጽሐፍ ዛሬ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 5፡30 ሰዓት ባለው ጊዜ ይመረቃል። መጽሐፉ በጋዜጠኛ ወንድወሰን መኮንን እና በጀነራሉ የበኩር ልጅ ትዕግስት ንጉሤ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከፍተኛ የወታደራዊ አመራሮች፣ የሥራዊት አባላትና ቤተሰቦች በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ይመረቃል። ዝግጅቱ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሕዳሴ አዳራሽ ይካሄዳል።

በሌላ መረጃ የህይወት እምሻው 7ኛ ስራ የሆነው “ቀብርና ማስካራ” የተሰኘው መጽሐፍ ዛሬ በይፋ ለንባብ ይበቃል። በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ “የመጀመሪያ” የተባለውና 90 ታሪኮችን በአንድ ጥራዝ ያካተተው ይህ መጽሐፍ ከ8፡00 እስከ 10፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ በይፋ ለንባብ ይበቃል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ደራሲ ህይወት እምሻው በተገኙበት የመጽሐፍ ማስፈረምና የፎቶ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡ ዝግጅቱን ያሰናዳው ጃዕፈር መጻሕፍት ሲሆን፣ ከፊርማና የፎቶ ፕሮግራም በተጨማሪ ሌሎች የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ይደረጋሉ ተብሏል፡፡

መጽሐፉ በአንድ ጥራዝ ውስጥ 90 ታሪኮችን ያካተተ ሲሆን፣ ደራሲዋ “ይህ መጽሐፌ ከአማርኛ ቋንቋ እና ስነ ፅሑፍ ጋር ደጋግሜ በፍቅር እንድወድቅ ላደረገኝ ደራሲ አዳም ረታ የተበረከተ ነው” ብላለች። ሕይወት እምሻው ከዚህ በፊት ለአንባቢያን ስድስት መጻሕፍት ያደረሰች ሲሆን፣ እነዚህም ባርቾ፣ ፍቅፋቂ፣ ማታ ማታ፣ ለእርቃን ሩብ ጉዳይ፣ የቡና ቁርስና ዥዋዥዌ ናቸው። ሁነቱ ለገሃር፣ ተወልደ ሕንጻ ስር በሚገኘው ጃዕፈር መጻሕፍት መደብር ስለተሰናዳ ሁላችሁም ተጋብዛችኋል፡፡

ሙዚቃ

የጃዝ ባንድ የሆነው “ካየን-ላብ” ሙዚቀኞች የፊታችን ሰኞ ህዳር 7 ቀን 2019 ዓ.ም የሙዚቃ ስራቸውን ያቀርባሉ። ሀያት ረጀንሲ ሆቴል ውስጥ በፈንድቃ ባህል ማዕከል ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ የካየን-ባንድ አባላት የሙዚቃ ስራቸውን ማቅረብ ይጀምራሉ። የካየን -ላብ የጃዝ የሙዚቃ ባንድ ለየት ባለ የጃዝ ሙዚቃ አጨዋወት የሚታወቁ ሙዚቀኞችን ያጣመረ ሲሆን፣ በቀጣይ ጊዜያትም ሰኞ ቀን በቋሚነት በፈንድቃ ባህል ማዕከል ላልተወሰነ ጊዜ የሙዚቃ ስራቸውን ያቀርባሉ ተብሏል፡፡

ስዕል

ባለፈው ሳምንት ጥቅምት 26 ቀን 2019 ዓ.ም በይፋ መታየት የጀመረው “ከትናንት እስከ ዛሬ” (ቾንቤ) የተሰኘው አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ይገኛል። 22 ሰዓሊያን በአንድ ላይ የስዕል ስራዎቻቸውን ያቀረቡበት ይህ አውደ ርዕይ፣ በጎበረ ከርስቶስ ደስታ ዘመናዊ የስነ ጥበብ ማዕከል ውስጥ በመታየት ላይ ነው፡፡ የስዕል አውደ ርዕዩ እስከ መጪው ህዳር 17 ቀን 2019 ዓ.ም ለጥበብ አፍቃሪያን ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡

በሌላ መረጃ “አዲስ ቅኝት” የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ በሰዓሊ ፍቅረአዲስ ላመስግን የተሳሉ የተለያዩ ስዕሎች የቀረቡበት አውደ ርዕይ፣ ጥቅምት 11 ቀን፣ 2019 ዓ.ም መስቀል አደባባይ በሚገኘው በፈንድቃ ባህል ማዕከል ሀያት ረጀንሲ ሆቴል ውስጥ በይፋ የተከፈተ ሲሆን እስከ ፊታችን ሰኞ ህዳር 07 ቀን፣ 2019 ዓ.ም ድረስ ይቆያል። መላው የጥበብ አፍቃሪያንም በስፍራው ተገኝታችሁ የስዕል አውደ ርዕዩን እንድትታደሙ ተጋብዛችኋል፡፡



በመዲናዋ አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7፡30 ሰዓት “12ቱ እንግዶች” እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት “በር የሌለው ቤት” ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ እሁድ ደግሞ በ7፡30 ሰዓት “ንጉስ አርማሕ” እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት “እምዬ ብረቷ” ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ“ሁሉ በጇ” መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ “እሳት ወይ አበባ” ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 ሰዓት እንዲሁም "ባልቻ አባነፍሶ“ ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በአንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጐ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት “የንባብ ከተማ” የተሰኘው የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8:00 ሰዓት “ወህኒ አምባ”፣ በ11፡30 ሰዓት ደግሞ “አትጥሪኝ” ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረዕቡ በ11፡00 ሰዓት “እሉ”፣ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት “ነገሩ አይቆምም”፣ እሑድ በ8:00 ሰዓት “ሰዶታ” (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12:00 ሰዓት “የመጨረሻው ፍርድ” ቴአትሮች ለጥበብ አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7፡30 ሰዓት “12ቱ እንግዶች” እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት “በር የሌለው ቤት” ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ እሁድ ደግሞ በ7፡30 ሰዓት “ንጉስ አርማሕ” እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት “እምዬ ብረቷ” ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ“ሁሉ በጇ” መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።


በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ “እሳት ወይ አበባ” ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 ሰዓት እንዲሁም "ባልቻ አባነፍሶ“ ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በአንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጐ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት “የንባብ ከተማ” የተሰኘው የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8:00 ሰዓት “ወህኒ አምባ”፣ በ11፡30 ሰዓት ደግሞ “አትጥሪኝ” ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረዕቡ በ11፡00 ሰዓት “እሉ”፣ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት “ነገሩ አይቆምም”፣ እሑድ በ8:00 ሰዓት “ሰዶታ” (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12:00 ሰዓት “የመጨረሻው ፍርድ” ቴአትሮች ለጥበብ አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

የቁጥር ጨዋታ


የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ



ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በሦስት ማዕዘን ውስጥ የተቀመጡትን ቁጥሮች በመደመርና በማባዛት ነው የጥያቄውን መልስ ማግኘት የምንችለው፡፡ በዚህ መሰረት በሦስት ማዕዘኑ አናት ላይ የተቀመጠውን ቁጥር በግራ በኩል በታችኛው ማዕዘን ላይ ከተቀመጠው ቁጥር ጋር እንደምራለን። ደምረን ያገኘነውን ውጤት በስተቀኝ በታችኛው መስመር በኩል በሚገኘው ቁጥር እናባዛለን፡፡ አባዝተን ያገኘነውን ውጤት የመሃሉን ቁጥር ማምጣት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት ነው የጥያቄውን ትክክለኛ መልስ የምናገኘው፡፡ ለአብነትም የመጀመሪያውን ሶስት ማዕዘን አብረን እንስራው፤ 9 + 8 = 17 ከዚያ በኋላ 17 × 1 = 17 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ እንደሚከተለው ይሆናል። 3 + 11 = 14 ከዚያ በኋላ 14 × 2 = 28 ይሆናል፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ መልስ **28** ይሆናል፡፡

የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



ምናብና ቀመር ሲሰናኙ

በአብርሃም ገብሬ

ኪነጥበባዊየፈጠራሥራዎችናሳይንሳዊ እሳቤዎች አንዳንድ ሰዎች የተራራቁ ዘርፎች አድርገው ይመለከቷቸዋል። ኪነ ጥበብን ከስሜት፣ ሳይንስን ደግሞ ከምክንያታዊነት ጋር በማያያዝ ድንበር ለማበጀትም ይሞክራሉ። ይሁን እንጂ ሁለቱም ከሰው ልጆች አስተሳሰብ የሚመነጩ፣ ህይወትን በጥራት እንኖራት ዘንድ የሚተጉ ናቸው። ከምንም በላይ ግን ኪነ ጥበብና ሳይንስ ተደጋጋፊ እንጂ ተጻራሪ የፈጠራ ውጤቶች አይደሉም።

በዚህ ሰዓት ዓለም ላይ ካሉ ስመጥር ኒውሮሳይንቲስቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ሰው አንቶኒዮ ዳማሲዮ ነው። ኒውሮሳይንቲስቱ “Descartes’ Error: Emotion, Reason, and the Human Brain” በተሰኘው መጽሐፉ ያረጋገጠው አንዱ ጉዳይ፣ ምክንያታዊነትና ስሜት ተደጋጋፊ እንጂ ተጻራሪ እንዳልሆኑ ነው። አንቶኒዮ ዳማሲዮ በመጽሐፉ እንዳሰፈረው፣ አእምሯችን ምክንያታዊ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ በዋናነት ከስሜታዊ ልምምዶችና ተሞክሮዎች መነሳት አለበት። ምክንያቱም አንድ ጉዳይ እውነት ሆኖ እንዲሰማንና ተቀባይነት እንዲያገኝ ስሜት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የአንጎላቸው ስሜታዊ ማዕከሎቻቸው ውስንነት ያለባቸው ሰዎች ምንም እንኳን በምክንያት የማሰብ አቅማቸው ባይቀንስም፣ ቀላል ውሳኔዎችን ለማድረግ ግን ይቸገራሉ። የዚህ ዋነኛ ምክንያት አእምሮ አንድን ነገር መርጦ ለመወሰን፣ የቀድሞ ልምዶቹን በስሜት መነጽር መመልከት ስለሚያሻው ነው።

የአንቶኒዮ ዳማሲዮ ጥናቶች የሚያስተምሩን አንዱ ፍሬ ነገር፣ የኪነ ጥበብ ሥራዎችን መውደድ የአእምሮ ስሜታዊ ብልህነትን በማዳበር ረገድ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ነው። ስሜትን የሚያነቃቁና የሚሞርዱ የጥበብ ስራዎች ለአእምሮ ማስተዋልን ይሰጡታል። በዚህም ሳይንሳዊ ፈጠራዎችን እና ምክንያታዊ አስተሳሰቦችን ለማዳበር የኪነ-ጥበብ ፈጠራዎች የማይተካ ሚና አላቸው።

ባሳለፍነው ህዳር አንድ ቀን (በፈረንጆቹ ኖቬምበር 10) በዓለም አቀፍ ደረጃ “ሳይንስ ለሰላምና ለልማት” በሚል መነሻነት ተከብሯል። ይህ የሆነው በዩኔስኮ በዋናነት ሳይንስ በሰዎች ዘወትራዊ ህይወትና በህብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ያለውን ገንቢ አስተዋጽኦ ለማስታወስ ነው። የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል፣ ቀኑን መነሻ በማድረግ የጥበብ ስራዎችን መውደድ ሳይንሳዊ ዕውቀቶችን ለማዳበርና የአዕምሮ የመፍጠር አቅሙን በማነልበት ረገድ የሚሰጠውን ፋይዳ በተመለከተ ኤጭር ዳሰሳ እንደሚከተለው አድርጓል።

የአእምሮ ድርብ ክንፎች


ዶክተር ነጋ ፍቅሬ በአማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሥነ-አእምሮ ሐኪም ናቸው። “የመረሳት ፍርሃት” የተሰኘ የግጥም መጽሐፍ ደራሲም ናቸው። የሳይንሳዊ ዕውቀትና የኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ትስስርን በተመለከት





ፎቶ፦ ከገፀ ድር

በሳይንስ የላቁ የጥበብ አፍቃሪያን



ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በሰጡት ሙያዊ አስተያየት፣ ኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ስራዎችን ማድነቅና መከየን የአእምሯችን ሴሎች እርስ በእርሳቸው አዳዲስ ግንኙነቶችን እንዲፈጥሩ ያነሳሳል። ይህ ክስተት በሳይንሱ ‘ኒውሮፕላስቲስታቲቲ’ በመባል ይታወቃል። አእምሮ በኪነ ጥበብ ስራዎች አማካኝነት ውስብስብ ከሆኑ ቅርጾች፣ ቀለሞች፣ ዜማዎች፣ ትረካዎች... ጋር መስተጋብር ሲፈጥር የማሰብ እና የማስታወስ አቅሙ እየዳበረ እንደሚሄድ አጫውተውናል።

እንደ ዶ/ር ነጋ ገለጻ፣ አንድ ሳይንሳዊ ግኝት ከመገኘቱ በፊት ሁልጊዜም በምናብ ይረቀቃል፣ ምስሉም ይቀረጻል። የኪነ ጥበብ ስራዎች የሰውን ልጅ ከነባራዊው ዓለም ከሚታሰቡ ጉዳዮች ባሻገር ያሉ ሀሳቦችን በምናቡ እንዲያስብና ምስል እንዲቀርጽ በማድረግ የፈጠራ አቅምን ያነሳሳሉ። አልበርት አንስታይን “ምናብ ከዕውቀት የበለጠ ጠቃሚ ነው፤ ዕውቀት ወሰን አለውና” ሲል የገለጻው ይህንን የፈጠራ ሥነ-ልቦናዊ አስፈላጊነት አጽንኦት ለመስጠት መሆኑንም ተናግረዋል።

ሳይንስ ቀመሮችንና ስልቶችን የሚከተል ቢሆንም፣ ታላላቅ ግኝቶች የሚገኙት ከተለመደው አስተሳሰብ ውጭ በሆኑ አዳዲስ አቀራረቦች ነው ይላሉ፤ ዶ/ር ነጋ ፍቅሬ። ኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎችም ሆኑ ከያኒያን ደግሞ መደበኛ ያልሆኑ ትረካዎችን፣ አሻሚ ፍቺዎችንና ያልተለመዱ ምስሎችን በማስተዋወቅ አእምሮን ከተለመደው የዕለት ተዕለት የኑሮ ክብ ውስጥ የማስወጣት አቅም አላቸው። ይህ ልማድ ሳይንቲስቶችና አዳዲስ ግኝት አፍላቂዎች ውስብስብ ችግሮችን ከተለያየ ማዕዘን እንዲያዩ እንደሚረዳቸው ተናግረዋል።

ሌላው ግን አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን ትልልቅ ፈጠራዎች የሚመነጩት የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች በሚፈጥሩት መስተጋብር ነው። አርቲስቶች የተለያዩ ሐሳቦችን በማቀናጀት አዲስ ትርጉም እንደሚፈጥሩ ሁሉ፣ የፈጠራ ባለሙያዎችም ከተለያዩ የሳይንስና የቴክኖሎጂ መስኮች መረጃዎችን በማዋሃድ አዳዲስ ውጤቶችን ያስገኛሉ። ኪነ ጥበብ ለአእምሮ ይህንን የሐሳብ ውህደት በብቃት የማከናወን ልምምድ በመስጠት ገንቢ ድርሻ እንደሚወጣ መረጃዎች ያሳያሉ።

ሳይንስን ከኪነ ጥበብ ጋር አጣምረው የላቁ ሳይንቲስቶች

ከላይ በጨረፍታ ዳሰሳ የተደረገበት አንዱ ጉዳይ፣ የሰዎች አዕምሮ ከፍ ያለ የፈጠራ አቅም የሚገለጸው ሳይንስንና ኪነ ጥበብን ሲያዋህድ ነው። በታሪክ ውስጥ የዕውቀት አድማሳቸው ሰፋ ያለ ታላላቅ ሳይንቲስቶች በጥበብ ስራዎች ላይ የነበራቸው ተሳልሎና መውደድ፣ አዕምሯቸው ከተለመደው አስተሳሰብ ባሻገር እንዲያስብ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህ ረገድ ቀዳሚ ተጠቃሹ ጣሊያናዊው ሊዮናርዶ ዳቪንቺ ነው። የጥበብና የሳይንስ ሊቁ ዳቪንቺ፣ ዝነኛ የሆኑ ስዕሎች (ለምሳሌ የሰው አካል አወቃቀር ጥናቶች) ሥነ-ጥበብን ከሳይንሳዊ ምርምሮች ጋር በማጣመር የተሰሩ ናቸው። ዳቪንቺ እያንዳንዱን የተፈጥሮ ውበት በጥልቀት መመልከቱ የሰውነት አካል አሰራርንና ፊዚክስን በወቅቱ ለመረዳት መንገድ ከፍቶለታል።

ስክሪብድ ገጸ ድር እ.ኤ.አ. በየካቲት 2026 ባስነበበው “The Art and Science of Leonardo Da Vinci” በተሰኘው ጥናታዊ ጽሑፍ፣ ዳቪንቺ የፈጠራ ባለቤት የሆነባቸው እንደ በረራ ማሽኖች እና የጦር መሳሪያዎች ያሉ ንድፎች መሠረታቸው፣ በኪነ ጥበብ ስራዎች ውስጥ በነበረው ጥልቅ ምናባዊ እይታ ላይ ይመሰረታል። ኪነ ጥበብ አዕምሮ እንዲያስብ በሚሰጠው ነጻነት አማካኝነት፣ በዘመኑ ያልነበሩ ቴክኖሎጂዎችን አስቀድሞ በወረቀት ላይ እንዲስል አስችሎታል። ይህ የጥበብ ፍቅር በአዕምሮ ውስጥ አዳዲስ ንድፎችን የመፍጠር አቅምን በከፍተኛ ደረጃ አጎልብቶታል።

ሌላው ታዋቂው ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን ለረቀቁ የሳይንሳዊ ግኝቶቹ አንዱ ምንጭ ሙዚቃ እንደሆነ ነው። የአንፃራዊነት ንድፈ-ሃሳብ (Theory of Relativity) አባት የሚባለው ታላቁ የፊዚክስ ሊቅ አልበርት አንስታይን፣ ለሙዚቃ (በተለይም ለቫዮሊን የሙዚቃ መሳሪያ) የነበረው ፍቅር ከሳይንሳዊ ስራዎቹ ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነበር። አንስታይን ውስብስብ የፊዚክስ እውቀቶችን በሚያጠናበት ጊዜ አእምሮውን ለማሳረፍና አዳዲስ ሃሳቦችን ለማሰላሰል ሙዚቃን ይጠቀም ነበር። ለሳይንቲስቱ የሙዚቃ ቅኝት ህጎች ለአዕምሮው የሂሳብ እና የውበት ስምምነትን ይሰጡት ነበር።

እንዲያውም አንስታይን አንድ የሚጠቀስለት ዝነኛ አባባል አለው፤ “ያለ ሙዚቃ ህይወት ለእኔ ከቶም ሊታሰብ የማይችል ነው” (Life without playing music is inconceivable for me.) ይላል አባባሉ። ለአንስታይን እንደ ሙዚቃ ያለ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለመቀመር ብቻ ሳይሆን በህይወት ለመኖር ቁልፍ አስተዋጽኦ አለው። የዓለም የኖቤል ድርጅት በገጸ-ድሩ በአንድ ወቅት የኖቤል ሽልማት ለሸለመው ስለ አልበርት አንስታይን በፈረንጆቹ 2019 እንዲህ አስፍሯል፤ አንስታይን ኪነ ጥበብና ውበትን በማድነቅ ተፈጥሮን በሌላ ማዕዘን እንዲመለከት አድርጎታል። የአንስታይን ሳይንሳዊ ግኝቶቹን በሂሳብ ቀመሮች ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ በአዕምሮው ውስጥ በሚስላቸው ምስሎች አማካይነት ይረዳቸው ነበር። ለአብነትም የብርሃን ጨረርን ተከትሎ እየተጓዙ መገመት የአንፃራዊነት ንድፈ ሃሳብን እንዲያገኝ አድርጎታል።

ኪነ ጥበብና ሳይንስ ሲጣመሩ የተሻለ የማሰብ ብሎም የመፍጠር አቅም እንደሚያሳድግ አንዷ ማሳያ ኢትዮጵያዊቷ የኮምፒዩተር ሳይንቲስትና የሰው ሰራሽ አስተውሎት (ኤአይ) ተመራማሪ ትዕምኒት ገብሩ ነች። አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገችው ትዕምኒት፣ አሁን ላይ ዓለም ላይ ስመጥር የኮምፒዩተር ሳይንቲስትና የኤአይ ሊቅ ነች። አብዝታ የምትወዳቸው ሶስት ነገሮች ሙዚቃ፣ ሂሳብና ፊዚክስ ናቸው። በአንድ ቃለ መጠይቋ እንደገለጸችው፣ አሜሪካ ውስጥ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግና ሙዚቃ ነበር ጎን ለጎን ለመማር ያሰበችው። የኋላ ኋላ ግን ትዕምኒት የታወቀች የኮምፒዩተር ሳይንቲስትና የኤአይ ተመራማሪ መሆን ችላለች። ከዕለት ተዕለት የጥናት እና የምርምር ስራዎቿ ጎን ለጎን ሙዚቃ ታዳምጣለች። በምርምር ላብራቶሪዎቿ ውስጥ ረቀቅ ያሉ ስልተ-ቀመሮችን (Algorithms) ስትቀምርና ትላልቅ የመረጃ ቋቶችን ስትመረምር፣ የተለያዩ የሙዚቃ ዘውጎችን እንደምታዳምጥ መረጃዎች ያሳያሉ።

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ቅዳሜ የሚቀርብ

ህይወትን የሚያድን እርምጃ

• የጡት ካንሰር ሥር ሳይሰድ በምርመራ ከታወቀ የመዳን ዕድሉ ከ90 በመቶ በላይ መሆኑ ተጠቁሟል

በሸዋርካብሽ ቦጋለ

በሀገራችን የጡት ካንሰርን ለመከላከል፣ ቀደም ብሎ ለመመርመር እና ሕክምና ለመስጠት የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች መሥራት ከተጀመሩ ዋል አደር ብለዋል። የጡት ካንሰር በሀገሪቱ በስፋት ከሚከሰቱ የካንሰር ዓይነቶች አንዱ በመሆኑ መንግሥት፣ የጤና ባለሙያዎችና የተለያዩ አጋር ድርጅቶች ትኩረት ሰጥተው እየሠሩበት እንደሆነም በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል።

ችግሩን ለመከላከል ከሚሠሩ ሥራዎች አንዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የቅስቀሳ ሥራ ሲሆን፣ በየዓመቱ ጥቅምት ወር የጡት ካንሰር ንቃተ ሕሊና ማሳደጊያ ወር አድርጎ በመወሰድ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ የንቅናቄ መድረኮች፣ የሩጫ ውድድሮች እና የትምህርት መርሃ ግብሮች ይካሄዳሉ።

እንደዚሁም የቅድመ ምርመራ አገልግሎቶች መስፋፋት፣ የሕክምና እና የመሠረተ ልማት ማሻሻያዎች፣ የባለሙያዎች ሥልጠና እና አቅም ግንባታ ሥራዎች መሠራታቸው ብቻ ሳይሆን የጤና ሚኒስቴር ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከያ እና መቆጣጠሪያ የሚሆን ብሔራዊ ስትራቴጂክ ዕቅድ ነድፎ ተግባራዊ አድርጓል።

በዚህም የጡት እና የማኅፀን በር ካንሰር ቅድመ መከላከል ዋነኛው ትኩረት መሆኑ ለጉዳዩ የተሰጠውን ክብደት የሚያመላክት ነው። የጡት ካንሰርን በተመለከተ በየዓመቱ የሚከናወነውን የግንዛቤ ማሻሻያ ወር ምክንያት በማድረግም በየአካባቢው የጡት ካንሰር የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራዎች ይደረጋሉ። የኮተቤ 02 ወረዳ 9 ጤና ጣቢያም የምርመራ አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ተቋማት አንዱ ሲሆን፣ በጤና ጣቢያው ተገኝተን የቅድመ ምርመራ ሂደቱን ተመልክተናል።

የጤና ጣቢያው ዋና ሥራ አስኪያጅ አብርሐም ፀጋው ጤና ጣቢያው ለአገልግሎት ፈላጊው ማኅበረሰብ በርካታ አገልግሎቶችን እንደሚሰጥ አስታውሰው፣ ከሚሰጧቸው አገልግሎቶችም የማኅፀን ጫፍ እና የጡት ካንሰር ቅድመ ምርመራ አገልግሎት አንዱ ነው ብለዋል።

በየካ ክፍለ ከተማ የኮተቤ 02 ወረዳ 9 ጤና ጣቢያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አብርሐም ፀጋው፣ የእናቶችን ጫና ለማቃለል ብሎም እንዳይንገላቱ የተቀናጀ አንድ ማዕከል አገልግሎት ላይ የጡት ካንሰር እና የማኅፀን ጫፍ ካንሰር የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራዎች ይሰጣሉ። እነዚህ አገልግሎቶች በሰለጠኑ ባለሙያዎች እንደሚሰጡ የጠቆሙት ሥራ አስኪያጁ፣ ይህም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጥምረት የሚሰጥበት አግባብ መኖሩንም አንስተዋል። ከተቋሙ ባሻገር በማኅበረሰቡ ውስጥ በቤተሰብ ጤና ቡድን አማካኝነት የጡት ካንሰር ምልክት ያለባቸው ሰዎች የልየታ ሥራ ከተሠራ በኋላ ሕክምና ወደሚሰጥበት ተቋም ይላካሉ።



ፎቶ፦ ከገፀ ድር

የጡት ካንሰር በሀገሪቱ ከሚከሰቱ የካንሰር ዓይነቶች አንዱ ነው

> **“የጡት ካንሰር ዋና ዋና ምልክቶች በጡት ወይም በብብት ሥር የሚወጣ ሕመም የሌለው እብጠት፣ የጡት ቅርጽ ወይም መጠን መለወጥ፣ እና ከጡት ጫፍ ያልተለመደ ፈሳሽ ወይም ደም መውጣት ናቸው”**

በተለይ የጡት ካንሰር ዋና ዋና ምልክቶች በጡት ወይም በብብት ሥር የሚወጣ ሕመም ሌለው እብጠት፣ የጡት ቅርጽ ወይም መጠን መለወጥ፣ እና ከጡት ጫፍ ያልተለመደ ፈሳሽ ወይም ደም መውጣት ናቸው ያሉት ባለሙያዋ፣ የጡት ካንሰር ሥር ሳይሰድ ቀድሞ በምርመራ ከታወቀ የመዳን ዕድሉ ከ90 በመቶ በላይ በመሆኑ፣ ሴቶች በየወሩ ራሳቸውን እንዲመረምሩ እና ምልክት ሳይታይባቸው በየጊዜው ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ ምርመራ እንዲያደርጉም መክረዋል።

መንግሥት በሁሉም የመንግሥት የጤና ተቋማት በነፃ የቅድመ ምርመራ አገልግሎት ማስጀመሩን አንስተው፣ በጤና ጣቢያው ለዚሁ ምርመራም ይሁን ለተለያዩ አገልግሎቶች ለሚመጡ እናቶች በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምርመራ አገልግሎት እየተሰጠ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ወይዘሮ ሐረግ ገዛኝ ወደ ጤና ጣቢያው ልጃቸውን ለማስከተብ አምርተው እግረ መንገዳቸውን የጡት ካንሰር ምርመራ ማድረጋቸውን የነገሩን አስተያየት ሰጪ ናቸው። ቅድመ ምርመራ ማድረጋቸው አንዲት እናት ወይም ሴት የጡት ካንሰር ሕመም እንዳለባት ሕመሙ ሥር ሳይሰድ ቀደም ብላ ምርመራ ብታደርግና ሕክምና ብትጀምር የመዳን ዕድሏ ሰፊ መሆኑን ከጤና ባለሙያዎች ተረድቻለሁ የሚሉት እኚሁ እናት፣ ወደ ጤና ተቋም ሳይመጣ ቤት ውስጥ ጡትና የጡት አካባቢን በመዳበስ እንዲሁም በመስታወት የጡት መጠንን በመመልከት ያለውን ሁኔታ መረዳት እንደሚቻልም ግንዛቤ ማግኘታቸውን ጠቅሰዋል።

ወይዘሮ ራውዳ ሰይድ የተባሉ ሌላዋ አስተያየት ሰጪም የጡት ካንሰር በጊዜ ሕክምና ካልተደረገ አደገኛ በሽታ መሆኑን በቅርበት በሚያውቋቸው አንዲት እናት ላይ ደርሶ መመልከታቸውን አስታውሰው፣ በሽታው ሥር በመስደዱ ሳቢያ ሁለቱንም ጡቶቻቸውን እስከመቆረጥ መድረሳቸውን፣ እንዲያም ሆኖ ከበሽታው ሙሉ በሙሉ ባለመፈወሳቸው የጨረር ሕክምና እያደረጉ እንደሆነ ነው የተናገሩት።

ማናችንም ብንሆን ሕመም ሳይከሰት አስቀድሞ ክትትልና የጤና ምርመራ ማድረግ ጠቃሚ መሆኑን ተገንዝቢያለሁ ብለው፣ እሳቸውም በቤታቸው ሰውነታቸውን ሲታጠቡ ጡቶቻቸውን በመዳበስ ብሎም ለልጆቻቸው ከማሳወቅና ከማስተማር ሌላ በጤና ጣቢያው የጡት ካንሰር ቅድመ ምርመራ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቡድን የማኅፀን በር ካንሰርና የጡት ካንሰር ተጠሪ ብሩክታይት አበበ፣ “የየትኛውም ዓይነት ካንሰር በሰውነት ውስጥ ያሉ ሴሎች የሚያደርጉት ያልተለመደ ወይም አግባብ ያልሆነ ብዜት ማለት ነው” ብለው፤ ሰውነታችን በተፈጥሮ የራሱ የሆነ የሴሎች እድገት እንዳለው ሁልጊዜም ሴሎች እየተከፋፈሉ እያደጉና እየሞቱ እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

ባልተለመደ ሁኔታ ግን በተለያዩ ምክንያቶች በራሳቸው ዝም ብለው ከመጠን ባለፈ ከተፈጥሮ ውጪ ሊባዙ እንደሚችሉና ይህ ሁኔታ ሲከሰትም ወደ ካንሰር ሊቀየር እንደሚችል ገልጸው፣ የጡት ካንሰርም የጡት ሴሎች ባልተለመደ ሁኔታ እየተከፋፈሉ በጣም በፍጥነት ወይም በብዛት እየተራቡ ሲሄዱ የሚመጣ የጤና እክል መሆኑን ጠቅሰዋል።

የጡት ካንሰር የሚከሰተው በጡት ውስጥ የሚገኙ ሕዋሳት ከተፈጥሯዊ የሰውነት ቁጥጥር ውጪ በሆነ መንገድ ከመጠን በላይ ሲራቡ እና ሲያድጉ ነው። እነዚህ ሕዋሳት ቅርጻቸውን እና ባህሪያቸውን በመቀየር በጡት ውስጥ እብጠት የሚፈጥሩ ሲሆን፣ በጊዜ ካልታከሙ በደም ዝውውር አማካኝነት ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ሊሰራጩ ይችላሉ።

የጡት ካንሰር በዓለም አቀፍ ደረጃ 99 በመቶ በሴቶች ላይ የሚከሰት ቢሆንም፣ ፣ በመቶ ያህሉ ግን በወንዶች ላይ ይከሰታል። የጡት ካንሰርን ጨምሮ በአብዛኛው ካንሰር የሚመጣበት ምክንያት በውል ባይታወቅም፣ ለካንሰር አጋላጭ ተብለው የተቀመጡ ሁኔታዎች መኖራቸውን ግን ሳይጠቅሱ አላለፉም።

በጡት ወይም በብብት ሥር የሚወጣ እብጠት፣ የጡት ጫፍ ወደ ውስጥ መሰርጎድ ወይም ከጡት ጫፍ ያልተለመደ ፈሳሽ መውጣት፣ በጡት ቆዳ ላይ የሚታይ የቆዳ ቀለም ወይም ቅርጽ ለውጥ፣ የቆዳ መሸብሸብ ወይም ቁስለት የበሽታው ዋና ዋና ምልክቶች መሆናቸውንና በሽታውን ለመለየት የመጀመሪያው የሕክምና እርምጃ አካላዊ ምርመራ ማድረግ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም የአልትራሳውንድ እና የማሞግራፊ ምርመራዎች፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የሕብረ ሕዋሳት ናሙና ምርመራ የሚደረግ ሲሆን፣ በሽታው ከተከሰተ በኋላ እብጠቱን ወይም ሙሉ የጡትን ክፍል በቀዶ ሕክምና ማስወገድ፣ እንዲሁም በኬሞቴራፒ እና በራዲዮቴራፒ የካንሰር ሕዋሳትን ለማጥፋት የሚያስችሉ ሕክምናዎች ይሰጣሉ።

በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቡድን የማኅፀን በር ካንሰርና የጡት ካንሰር ተጠሪ ብሩክታይት አበበ እንደገለፁት በአብዛኛው ዕድሜ እየገፋ ሲሄድ ከሚመጣ የሆርሞን ለውጥ ጋር ተያይዞ ሊመጣ እንደሚችል ገልጸው፣ በተለይ ዕድሜዋ ከ40 ዓመት በላይ የሆነች ሴት በየጊዜው ምርመራ እንድታደርግ ይመከራል።

ልጆች፤ አዲሱን የመጫወቻ ስፍራ እንዴት አገኛችሁት?

በፋንታነሽ ተፈራ

ልጆች እንዴት ናችሁ? ዛሬ ልንዳስሰው የወደድነው ርዕሰ ጉዳይ፤ ከቀጨኔ እስከ ባምቢስ ተገንብቶ ለአገልግለት የበቃው የወንዝ ዳርቻ ለእናንተ ስላካተተው የመዝናኛና መጫወቻ ቦታዎች ነው።

እኛም ወደ ስፍራው በማቅናት በእነዚህ መጫወቻ ቦታዎች ሲጫወቱ ያገኘናቸው ጓደኞቻችሁ አዲስ የመጫወቻና የመዝናኛ አማራጭ በመሰራቱ የተሰማቸውን ስሜት እና ስለሚሰጣቸው ጠቀሜታ ጠይቀናቸው ሃሳባቸውን አካፍለውናል። እናንተም ይሄን ጽሑፍ ካነበባችሁ በኋላ መረጃውን ይዛችሁ እንደምትነበኙ እና እንደምትዝናኑ በማመን፣ ያነጋገርናቸውን ልጆች ሃሳብ እንደሚከተለው አቀረብንላችሁ። መልካም ንባብ።

ተማሪ ሙሴ ባህሩ እባላለሁ። የመዝናኛ ቦታዎች በብዛት ከመሰራታቸው በፊት፣ በእረፍት ጊዜዬ ሰፈር ከጓደኞቼ ጋር ኳስ እጫወት ነበር። የምንጫወተው አስፋልት መንገድ ላይ ስለነበር በጨዋታ መሀል የመኪና አደጋ እንዳይደርስብኝ እፈራ ነበር። የወዳጅነት ፓርክ ከተሠራ በኋላ ቤተሰቦቼ አልፎ አልፎ ይወስዱኛል። አሁን ላይ ደግሞ በሠፈሬ የመጫወቻ እና የመዝናኛ ስፍራ በመሰራቱ፣ ሩቅ ሳልሄድ እዚሁ የመጫወት እድል አግኝቻለሁ። የቅርጫት ኳስ እንዲሁም ዥዋዥዌ እጫወታለሁ። በዚህም ደስተኛ ሆኛለሁ። ጉዳት ይደርስብኛል የሚል ስጋትም የለብኝም። የተለያዩ ጨዋታዎች ያለስጋት መጫወቴ ሰውነቴ ንቁና ጠንካራ እንዲሆን ይጠቅመኛል። አዕምሮዬ ዘና ይላል፣ ጤናማና ደስተኛም እሆናለሁ።

ተማሪ ሳሙኤል አብርሃም እባላለሁ። አራዳ እና ቀበና ፓርክ ተዝናንቼ አውቃለሁ። አሁን ደግሞ በቀጨኔ የወንዝ ዳርቻ በተሰራልን የመጫወቻ ቦታ ላይ ዋኝቼ ስጨርስ ነው ያገኘችሁኝ። ውሃ ዋና በጣም ያስደስተኛል። ይህን እድል በቅርቡ በማግኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። አሁን ላይ አዲስ አበባ ከተማ የትኛውም ቦታ ብንሄድ መጫዎቻዎች አሉ። በተለይ ይህ የመዝናኛ ቦታ ከትምህርት ቤት ስመለስ ለመጫወት በጣም ምቹና ቅርብ ነው።

ቅዳሜ እና እሁድ በዚህ ቦታ መጥቼ ስጫወት አዕምሮዬ ዘና ይላል። በፓርኮቹ ያሉትን አረንጓዴ ተክሎች፣ የተለያዩ ሰው ሰራሽ ቅርፃ ቅርፆችን ስመለከት አዳዲስ ነገሮችን ለመስራት ውስጤ እንዲነሳሳ ያደርገዋል። በመጫወቻ ቦታዎች ላይ ስጫወት ከማላውቃቸው አዳዲስ ልጆች ጋር ተዋውቄያለሁ። አብረን ለመጫወት መግባባትን፣ ተራ መጠበቅን እና መጫወቻዎችን በጋራ መጠቀምን ተምሬበታለሁ።

ተማሪ አሜን ይስሐቅ እባላለሁ። መዝናናት በጣም ያስደስተኛል። ከዚህ በፊት ለእኛ ለልጆች በነፃነት ለመጫወትና ለመዝናናት የተዘጋጀ ምቹ ቦታ አልነበረም። ሰፈር ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር እጫወት፣ አልፎ አልፎም አምባሳደር መናፈሻ ከቤተሰቦቼ ጋር እየሄድኩ እዝናና ነበር።

በአሁኑ ወቅት ደግሞ በምኖርበት ቀጨኔ በለማው የወንዝ ዳርቻ ፓርክ የተለያዩ እና የሚመቹ የመጫወቻ ቦታዎች ተሠርተውልናል። የትራንስፖርት ሳላወጣ እንድዝናና አድርጎኛል። በዥዋዥዌው ላይ እየተወዛወዝኩ፣ መንሸራተቻዎች ላይ እየተንሸራተትኩ ጊዜዬን በደስታ በማሳለፍ ላይ እገኛለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ፏፏቴዎች አሉ። ባህር የሚመስል የውሃ አካል የመመልከት እድል ፈጥሮልኛል። መዝናኛ ቦታው በጣም ደስ ስለሚል በቀጣይ ከቤተሰቦቼ ጋር በመምጣት ፎቶ የመነሳት ሃሳብ አለኝ።

ተማሪ አቡበከር ኑርሰፋ እባላለሁ። ከዚህ በፊት የምጫወተው በመንገድ ዳር፣ በኩብልስቶን ወይም ለመጫወት ምቹ ባልሆኑ ስፍራዎች ነበር። በምጫወትበት ጊዜም የመኪና አደጋ እንዳያጋጥመኝ እፈራ ነበር። በአሁኑ ሰዓት የተሰሩት የመዝናኛ ስፍራዎች፣ የእግር ኳስ ሜዳ ከጓደኞቼ ጋር እንድጫወት፣ ዛፎች፣ አበቦችና አረንጓዴ ቦታዎች እያየሁ እንድዝናና እድል ሰጥቶኛል። በመርከብ ቅርፅ የተሰራውንም ካፌ ስመለከት ተደስቻለሁ።

ከዚህ በተጨማሪም ንጹህ፣ ውብና ሰፊ በሆኑ የእግረኛ መንገዶች በነፃነት እንድንቀሳቀስ፣ አደጋ ይደርስብናል ብለን ሳንሰጋ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እንድናደርግ እድል ፈጥረውልናል። ይህም አካላችን እንዲጠነክር፤ የአዕምሮ ሰላም እንድናገኝ ጠቅሞናል።



ፎቶ፦ በዳዊት ቦጋለ

ልጆች በቀጨኔ የወንዝ ዳርቻ ልማት በተሰራው የልጆች መጫወቻ ሲጫወቱ

የአምባሳደር ፓርክ



የአምባሳደር ፓርክ በአዲስ አበባ ከዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል እና ከአምባሳደር ሲኒማ አጠገብ ይገኛል። ፓርኩ ከተማ የሚገኝ ታሪካዊና በቅርቡ የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት አማካኝነት በአዲስ እና በዘመናዊ መልክ ታድሶ ለነዋሪው መናፈሻና መዝናኛነት ክፍት ሆኗል።

ፓርኩ በአዲስ መልክ ከታደሰ በኋላ ለህፃናት ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ዘመናዊ የመጫወቻ ስፍራዎች ተዘጋጅተውለታል። ከእነዚህ መካከል አንዱ የህፃናት መጫወቻ ስፍራ ነው። በፓርኩ ውስጥ ለተለያዩ የእድሜ ክፍሎች የሚሆኑ ዘመናዊ ሽርተቴዎች፣ ዥዋዥዌዎች እና መውጫ መጫዎቻዎች ይገኛሉ።

ሰፊ አረንጓዴ ሜዳ ያለው ፓርኩ ልጆች በነጻነት የሚሮጡበት እንዲሁም አረፍ ሲሉ ለአይናቸው ማራኪ የሆነ ንጹህ እና አረንጓዴ ሳር የተነጠፈበት ቦታ አለው።

በፓርኩ የውሃ ፏፏቴዎች እና ሰው ሰራሽ ወንዝ ይገኛል። በቅርቡ በተደረገው እድሳት የውሃ ፏፏቴዎች እና የተስተካከለ የወንዝ ዳርቻ ስለተካተተበት ለልጆች ማራኪ እይታ ይሰጣል።

ልጆች በደህንነት የሚንቀሳቀሱባቸው ንጹህ የእግረኛ መንገዶች እና የብስክሌት መንገ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል።

የመረጃ ምንጭ፦ ገጸ ድር

10 ልዩነቶችን ፈልጉ



አንቆቅልሽ

ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

ምን ቢወዱት ብብት ስር አይሸጉጡት

መልስ፦ ሀ. እሳት

የዚህ ሳምንት ጥያቄ

ካባቷ ትበልጣለች ከእናቷ ታንሳለች

ሀ. ዶሮ

ለ. ግመል

ሐ. በቅሎ

ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ቅዳሜ የሚቀርብ

የስማርት ኢኮኖሚ ጉዞ በአዲስ አበባ

በደረጀ ታደሰ

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዓለም ከተሞች ዕድገትና የመልካም አስተዳደር መለኪያ የሚሰላው በሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ብዛት የተለመዱ ግዙፍ መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት ብቻ አይደለም። ከዚህ ይልቅ "ከተሞች ምን ያህል ዘመናዊውን የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከአስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎቻቸው ጋር አዋህደው ተጠቃሚ መሆን ችለዋል?" የሚለው ነጥብ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፋት እየተተገበረ የሚገኘው የስኡጥ ከተማ (ስማርት ሲቲ) ጽንሰ ሃሳብ፣ ከተሞችን ለነዋሪዎቻቸውና ለንብረቶቻቸው ምቹ፣ ቀልጣፋ፣ ጽዱ፣ ተወዳዳሪ እና ተመራጭ የማድረግ አላማን አንግቦ የሚንቀሳቀስ ነው። በዚህ ዘመናዊ የከተሞች የለውጥ እና ዕድገት ጉዞ ውስጥ ወሳኝ ምሰሶዎች ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል ስማርት ኢኮኖሚ አንዱ ነው።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በመዲናዋ ያሉ የመንግስት ተቋማት አገልግሎታቸውን የማዘመን ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል

አፍሪካዊቷ የዲፕሎማሲ ማዕከል እና የፈጣን ዕድገት ባለቤት የሆነችውን አዲስ አበባ፣ ይህንን ዘመናዊ የከተሞች ልማት ማዕቀፍ በመከተል ወደ ስኡጥ ከተማነት (ስማርት ሲቲነት) ለመቀየር የ8 ዓመት ስትራቴጂካዊ እቅድ ተቀርጾ ወደ ተግባር ከገባች ሦስት ዓመታትን አስቆጥራለች። በከተማ አስተዳደሩ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የስማርት ሲቲ ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ቡድን መሪ አቶ ይድነቃቸው ተስፋዬ እንደሚገልጹት፤ የመዲናዋን ስኡጥ ከተማነት እውን ለማድረግ ከተቀመጡት ስድስት ዋና ዋና ምሰሶዎች መካከል የስማርት ኢኮኖሚ ግንባታ የመጀመሪያውንና ዋናውን ድርሻ ይይዛል። በዚሁ መነሻነት የስማርት ኢኮኖሚን በተጠና አሠራር እና በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት አማካኝነት በከተማዋ ተግባራዊ አድርጎ ምን ውጤት ማምጣት እንደተቻለ፣ የቀጣይ አቅጣጫ ምን እንደሆነ እንዲሁም በዚህ የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ሚና ምን እንደሚመስል ለጋዜጣችን ዝግጅት ክፍል ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የስማርት ሲቲ ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ቡድን መሪ አቶ ይድነቃቸው እንዳብራሩት፤ የስማርት ኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሳብ ከባህላዊው በጥሬ ገንዘብ ወይም በአካላዊ ንክኪ ላይ ከተመሰረተ ኢኮኖሚ ወደ እውቀት፣ ፈጠራ፣ ዲጂታላይዜሽን እና ቴክኖሎጂ መር አሠራር መሸጋገርን ያመለክታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) እና የተለያዩ የዓለም አቀፍ ከተሞች ልማት ጥናቶች፤ "ስማርት ኢኮኖሚ:- የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን (ICT) በመጠቀም የንግድ፣ የፋይናንስ፣ የግብር አሰባሰብ፣ የምርታማነትና የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶችን ማዘመንና ግልጽ ማድረግ ነው።" በማለት ይበይኑታል።

እንደ ጊፊንገር ያሉ ታዋቂ የከተማ ልማት ተመራማሪዎች በጥናታቸው ያረጋገጡትና የሚስማሙበት ሀቅ፤ አንድ ከተማ የስማርት ኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሳብን አሳካች የሚባለው የፈጠራ አቅሟ፣ ሥራ ዕድል ፈጣሪነቷ፣ የገበያ ተወዳዳሪነቷ እና የአሠራር ቅልጥፍናዋ በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ሲደገፍና ምርታማነቷ ሲጨምር ነው። በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ ስማርት ኢኮኖሚ አሠራርን ዕውን ያደረጉ ከተሞች ከተለምዷዊ አሠራር ካልተላቀቁ ከተሞች የተሻለ እና ፈጣን የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት (ጂዲፒ-GDP) እንደሚያስመዘግቡ፣ ህገ-ወጥ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን የመቆጣጠር እንዲሁም የመንግሥት ገቢን በከፍተኛ መጠን የማሳደግ አቅምን እንደሚፈጥሩ መስክረዋል።

አዲስ አበባ የስኡጥ ከተማነትን ውጥን ለማሳካት ያስችሉኛል ብላ ከለየቻቸው ወሳኝ ምሰሶዎች መካከል አንዱ የሆነውን የስማርት ኢኮኖሚ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ባለፉት ሦስት ዓመታት ወሳኝ የሚባል ውጤት የተመዘገበባቸው ተግባራትን ስለማከናወኗ አቶ ይድነቃቸው አረጋግጠዋል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በዋናነት በሚመራው እና በርካታ ባለድርሻ አካላት በሚሳተፉበት የስማርት ሲቲ ዕውን የማድረግ ሂደት ውስጥ በተሠሩ ሥራዎች ከተመዘገቡ በርካታ ውጤቶች መካከል፡- ከተማዋ የምትሰበስባቸውን የግብር እና የአገልግሎት ክፍያዎችን ከካሽ ወደ ዲጂታል የክፍያ ስርዓት ማሸጋገር፣ የመንግሥት አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ዲጂታላይዝድ ማድረግ፣ ተበታትነው የነበሩ የመንግስት አገልግሎቶችን በማሰባሰብ በ"መሶብ" የአንድ ማዕከል አገልግሎት አማካኝነት ለዜጎች ማቅረብ፣ የግዢ (e-GP) እና የንብረት አስተዳደር (የአሴት ማኔጅመንት) ስርዓቱ ቡቴክኖሎጂ ማከናወን መቻሉን በማሳያነት ዘርዝረዋል።

"ከጥቂት ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ የነበረው የግብርና የአገልግሎት ክፍያ አሰባሰብ ስርዓት በጥሬ ገንዘብ ላይ የተመሰረተ ነበር። ይህ አሰራር ለሙስና፣ ለተለያዩ አሰራር መጓተቶችና ለአገልግሎት አሰጣጥ ቅሬታዎች መንገድ የከፈተ ነበር።" የሚሉት አቶ ይድነቃቸው፤ በአሁኑ ወቅት ግን ይህ የካሽ አሰባሰብ ስርዓት በዲጂታል ተተክቷል። በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ ተቋማት ማንኛውንም የፋይናንስ እንቅስቃሴ ዘመኑ ባፈራው ቴክኖሎጂ አማካኝነት እንዲፈጽሙ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ከንኪ ባንክ፣ ከቴሌብር እና ከሌሎች የክፍያ አማራጮች ጋር በሲስተም እንዲገናኙ ተደርጓል። ይህም ተገልጋዩ ማህበረሰብ የሚከፍለውን የትኛውንም ክፍያ በዲጂታል መንገድ ሲፈጽም፣ ገንዘቡ በቀጥታ ወደ ተቋማቱ ባንክ አካውንት እንዲገባ ማስቻሉን፣ ግልጽነትን ማስፈኑን፣ ተገልጋዩ የከፈለው ገንዘብ የት እንደደረሰና ለምን እንደዋለ በትክክል የሚያውቅበትን አስተማማኝ አሰራር መዘርጋቱን አስረድተዋል።

በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ አብዛኞቹ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ አገልግሎታቸውን በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አማካኝነት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ከእጅ ንክኪ የጸዳና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እየሰጡ ይገኛሉ። ተቋማት ላቀረቡት አገልግሎት የሚጠይቁትን ክፍያም በዲጂታል የክፍያ አማራጮች ይቀበላሉ። ከዚህ ቀደም በተለምዷዊ አሠራር ጊዜው፣ ገንዘቡ ለብክነት ይዳረግበት የነበረው ተገልጋይ፤ በቴክኖሎጂ በዘመነና በተቀላጠፈ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ረክቶ፣ የአገልግሎት ክፍያውን በእጅ ስልኩ ከፍሎ የሚያጠናቅቅበት ሁኔታ ተፈጥሮለታል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተገልጋይን የሚያስተናግዱ እንደ መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ፣ የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ ትራንስፖርት ቢሮ ያሉ ተቋማት ወደ ዘመናዊና ዲጂታል የአሠራር ሂደት መግባታቸው በብዙ መልኩ ሊገለጽ የሚችል ውጤት አምጥቷል።

ቡድን መሪው አቶ ይድነቃቸው አክለው እንዳስረዱት፤ የመንግስት የንብረት ግዢ እንዲሁም የአስተዳደር ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዘመነ መምጣቱ፣ የስማርት ኢኮኖሚ ግንባታው በስኬታማ ጉዞ ላይ መሆኑን አመላካች ነው። ምክንያቱም፤ ከተማ አስተዳደሩ ለልማት ስራዎች የሚያወጣውን በጀት ግልጽና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ስርዓት (e-GP) ተግባራዊ አድርጓል። በዚህም ማንኛውም የጨረታና የግዢ ሂደት በአንላይን በመመራቱ የተሻለ ተወዳዳሪነትንና ግልጽነትን አስፍኗል። በተጨማሪም "የአሴት ማኔጅመንት" ሲስተም ተዘርግቷል። ይህም የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ስርዓት እና የንብረት አስተዳደር ሲስተሞች ከተሞች ባላቸው ውስን ሀብት ከፍተኛ ውጤት እንዲያስመዘግቡና ያለአግባብ የሚባክኑ ንብረቶችን እንዲታደጉ ይረዳል፤ ለከተማዋ ኢኮኖሚም ትልቅ ካፒታል ይሆናል።

የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ያከናወነው ሌላው ትልቅ ስኬት የተለያዩ የመንግስት ተቋማትን አገልግሎት በአንድ ማዕከል ማገናኘት ነው። "መሶብ" በተሰኘው የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣ ከተለያዩ ተቋማት የመጡ ባለሙያዎች፣ የአይቲና የቢዝነስ ሰዎች በአንድ ላይ ተቀምጠው የሲስተም ውህደት (System Integration) በመስራት፣ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ቀላልና ቀልጣፋ፣ ምቾትና አክብሮት በሞላው ተቋማዊ ከባቢ ውስጥ በአንድ ቦታ ሁሉንም አገልግሎቶች የሚያገኝበትን ሁኔታ ፈጥረዋል። ስለማዕከላቱ የተሠሩ ጥናታዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት አገልግሎት የሚያገኙ ተገልጋዮች የእርካታ ደረጃ ከ99 ከመቶ በላይ ደርሷል። እንደዚህ ያሉ ለውጦች በመንግስት መስሪያ ቤቶች የነበረውን ረጅም ሰልፍ፣ የቢሮክራሲ ማነቆ እና ወረቀት ላይ የተመሰረተውን አሠራር በዲጂታል ሲስተሞች በመተካት ተገልጋዩ ህብረተሰብ ባለበት ቦታ ሆኖ እንዲገለገል ያደርጋል። ያባክን የነበረውን ጊዜና ወጪ በመቀነስ፣ ወደ ምርታማ ስራ እንዲሰማራ ሰፊ እድል ይፈጥራል።

የስኡጥ ከተማነትን (ስማርት ሲቲነትን) ጽንሰ ሃሳብ ወደ ዕውናዊ ውጤት ለመቀየር፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የገባችው አዲስ አበባ ገና ከማለዳው ለሌሎች ምሳሌ ሆናለች። ለዚህም በኢኮኖሚው መስክ የዘመነውና የሰመረው የስኬት ጉዞ ይጠቀሳል። ከተማዋ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ስማርት ኢኮኖሚን ተፈጻሚ ማድረጓ፤ ከዚህ ቀደም በጥሬ ገንዘብ (Cash-based) በሚከናወን የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ በጉልህ የሚታየውን ሙስና፣ የገንዘብ ምዝበራ፣ የግብር ስወራ እና የአሰራር ብክነት በማስቀረት፣ አሁን ላይ በፋይናንስ ስርዓቱ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሠራር ተፈጥሯል። የከተማዋ የገቢ መጠን በየዓመቱ እንዲጨምር አስችሎታል።

አዲስ አበባ ወደ ስማርት ኢኮኖሚ የምታደርገው ጉዞ ሙሉ በሙሉ አልጋ በአልጋ አይደለም። በሂደቱ በርካታ ሰው ሰራሽና የቴክኖሎጂ ተግዳሮት እንዳለ ቡድን መሪው አንስተዋል። በመንግስት ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች አዲሱን ዲጂታል አሰራር ለመቀበል ፍቃደኝነትና ፍላጎት ማነስ፣ በተወሰኑ አገልጋዮችና ተገልጋዮች ዘንድ የዲጂታል እውቀትና የአቅም ውስንነት መኖር፣ የመሰረተ ልማት አለመሟላትና የበጀት ውስንነት ከቀዳሚ ተግዳሮቶች መካከል ናቸው። ቢሮው በተግዳሮቶቹ ሳይታጠር መፍትሄ እየሰጠ ውጤታማ ጉዞውን ይቀጥላል። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታትም አዲስ አበባ በሁሉም መመዘኛ ዓለም አቀፋዊ ደረጃን የተቆናጠጠች ስኡጥ ከተማ (ስማርት ሲቲ) ለማድረግ ይሠራል ብለዋል።

ገበያዎቹ የኑሮ ውድነቱን ምን ያህል እያረጋጉ ነው?

በይግለጡ ጓዴ

ባሳለፍነው ቅዳሜ ረፋድ 4 ሰዓት ግድም በአዲስ አበባ ስድስት ኪሎ ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት አካባቢ ነበርኩ። ከፊት ለፊቴ በውስጣቸው በግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶች የተሞሉ አነስ አነስ ያሉ ድንኳኖች ይታያሉ። የምርቶቹ ልዩ ልዩ መጠንና ቀለማት ስፍራውን አድምቀውታል። “አምስት ኪሎ ስጠኝ፣ ስንት ነው፣ መዝንልኝ፣ ሽንኩርት በቅናሽ ገባ ገባ በሉ...” የሚሉ ድምፆች ከፍ ብለው ይሰማሉ። በእርግጥ ይህ ሁሌም በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት በአዲስ አበባ የተለያዩ ስፍራዎች የተለመደ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ድባብ ነው። እነዚህ ገበያዎች ደግሞ የኑሮ ውድነትን ማርገቢያ ፍቱን መላ ናቸው።

በእርግጥም በአሁኑ ወቅት በፍጥነት በማደግ ላይ በሚገኙ የሦስተኛው ዓለም ሀገራት ከተሞች ውስጥ ከሚታዩት ዋነኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች መካከል የኑሮ ውድነት እና የዋጋ ንረት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የምግብ ምርቶች ፍላጎት ማደግ፣ የትራንስፖርትና የሎጅስቲክስ ወጪዎች መጨመር እንዲሁም በምርት አቅራቢውና በሸማቹ መካከል ያሉ በርካታ ደላሎች እና መሰል ሰንሰለቶች መኖር የምርቶችን ዋጋ ያለአግባብ በመስቀል በዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና ያሳድራሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም በመዲናዋ የሚስተዋለውን ኢኮኖሚያዊ ጫና ለማቃለል፣ የሸማቹን የመግዛት አቅም ለመጠበቅ እና አምራችና ሸማችን በቀጥታ የሚያገናኙ አማራጭ የገበያ መስመሮችን ለመዘርጋት ከተገበራቸው ስትራቴጂያዊ ዘዴዎች መካከል እነዚህ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ቀደም ባሉት ዓመታት በመደበኛ የንግድ መስመር ውስጥ አንድ የኢንዱስትሪ ወይም የግብርና ምርት ከአምራቹ ተነስቶ ለሸማቹ እስኪደርስ ድረስ በአምራች፣ በአካባቢ ደላላ፣ በጅምላ ነጋዴ፣ በከተማ ደላላ እና በቸርቻሮ ነጋዴ በበርካታ ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል። በዚህ ረጅም ሰንሰለት ውስጥ እያንዳንዱ አካል የራሱን ትርፍ እና የትራንስፖርት ወጪ ስለሚጨምር፣ የቸርቻሮ ዋጋው ከአምራቹ ሽያጭ ዋጋ በላይ እጅግ ከፍ ብሎ ይደርሳል። የቅዳሜና እሁድ ገበያ ዓላማ ግን አምራቹን ወይም ቀጥታ አቅራቢውን ከሸማቹ ጋር ማገናኘት ነው።

ከአቅርቦት ሰንሰለት ችግሮች በተጨማሪ፣ የደላሎችና የመካከለኛ ነጋዴዎች አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪ፣ የምርት ብክነት፣ የትራንስፖርት መዘባየትና የማከማቻ ተቋማት እጥረት ችግሩን ይበልጥ ያወሳስቡታል። በእንደዚህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የመንግሥት ጣልቃ ገብነትና አማራጭ የገበያ መዋቅሮችን መዘርጋት በቀጥታ የህብረተሰቡን የዕለት ተዕለት ህይወት የሚታደግ እርምጃ መሆኑን የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ መኩብብ ተስፋሁን ይናገራሉ።



ፎቶ:- ከገጸ ድር

የየካ ክፍለ ከተማ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ከፊል ገፅታ

ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ስንመለከት፣ ህንድ በአግሮ-ኢኮኖሚዋ የምትታወቅ ሀገር ስትሆን፣ የደላሎችን አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ለማስወገድ ራይቱ ባዛር በመባል የሚታወቁ የአርሶ አደሮች ገበያዎችን አቋቁማለች። በእነዚህ ገበያዎች አርሶአደሮች ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለከተማ ነዋሪዎች ይሸጣሉ። ይህ ሥርዓት ከተማ ነዋሪዎች ምርትን በመደበኛ ገበያ ከሚሸጠው በአስራ አምስት እስከ ሀያ በመቶ ቅናሽ እንዲያገኙ ያደረገ ሲሆን፣ ለአርሶ አደሮች ደግሞ የተሻለ የገቢ ድርሻ አትርፎላቸዋል ይላል የህንድ የኤሌክትሮኒክስ እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይፋ ያደረገው የቅርብ ጊዜ መረጃ።

የህንድና መሰል ዓለም አቀፍ ልምዶች እንደሚያሳዩት፣ አምራችና ሸማችን በቀጥታ የሚያገናኙ ገበያዎች የዋጋ ንረትን ለመቀነስ ብቻ ሳይሆን፣ የአካባቢው አርሶ አደሮችና ህብረት ሥራ ማህበራት ተገቢውን የልፋታቸውን ዋጋ እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና እንዳላቸው የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ መኩብብ ጠቅሰዋል።

እንደ ባለሙያው ገለጻ የንግድ ሰንሰለቱ ሲያጥር፣ በምርት ማጓጓዝ ሂደት ውስጥ የሚባክነው ምርት መጠን የሚቀነስ ሲሆን፣ የሸማቹ የመግዛት ፍላጎትና የአቅራቢው የማቅረብ አቅም በተመጣጣኝ ሁኔታ ይገናኛሉ። ይህም በከተማና በገጠር መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ትስስር አጠናክሮ ዘላቂ የገበያ መረጋጋት ለመፍጠር ያስችላል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮም በከተማዋ ባሉ ሁሉም ክፍለ ከተሞች የቅዳሜና እሁድ ገበያን በስፋት በመተግበር በየክፍለ ከተማው እና በወረዳዎች ደረጃ የተወሰኑ ቦታዎችን በመለየት አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል። በቅዳሜና እሁድ ገበያዎች የሚቀርቡ መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች፣ በተለይም ሽንኩርት፣ ድንች፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ዘይት፣ ዱቄት፣ ጤፍ እና እንቁላል፣ በመደበኛ ሰፈር ሱቆችና

“የከተማ አስተዳደሩ ለ282 የቅዳሜና የእሁድ ገበያዎች የግብይት ቦታዎችን በነፃ ከመፍቀድ ጀምሮ የምርት ትስስር እንዲፈጥርላቸው ያደረገው የኑሮ ውድነት ጫናን ለመከላከል ነው”

የቸርቻሮ ገበያዎች ከሚሸጡበት ዋጋ ከ15 እስከ 20 በመቶ የሚደርስ ቅናሽ አላቸው። ይህም አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች የወርሃዊና የሳምንታዊ ምግብ ወጪያቸውን እንዲቀንሱ ረድቷቸዋል።

ወይዘሮ ቀነኒ ፋንታዬ በስድስት ኪሎ አካባቢ ባለው የቅዳሜና እሁድ ገበያ ላይ ሽንኩርት እና ድንች ሲሸምቱ ያገኘናቸው እናት ናቸው። ገበያዎቹ የተለያዩ የፍጆታ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የነዋሪዎችን የኑሮ ሁኔታ እያቀለሉ መሆኑን ወይዘሮ ቀነኒ ይናገራሉ።

በቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ሁሉንም ዓይነት ምርቶች በአንድ ቦታ እንደሚያገኙ ወይዘሮ ቀነኒ ገልጸው፣ ከውጭ ካለው ገበያ አኳያ ሲታይ የተሻለ የዋጋ እና የምርት አቅርቦት ያለው መሆኑን ጠቁመዋል። ለነዋሪዎች የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት አኳያ ገበያዎቹ የሚይተካ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል።

ወይዘሮ ብርቱካን ደሳለኝ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል አካባቢ በሚገኝ የቅዳሜና እሁድ ገበያ ላይ ግብይት ሲፈጽሙ ያገኘናቸው እናት ናቸው። የቅዳሜና እሁድ ገበያ ከሌላው አንጻር የዋጋ ሁኔታ እና የምርት አቅርቦቱ የተሻለ መሆኑን ተናግረዋል። በቀላሉ የተለያዩ የፍጆታ ምርቶችን በአንድ ላይ ማግኘት እንደሚችሉ ወይዘሮ ብርቱካን ተናግረው፤ ይህም ብዙ ሳይደክሙ በቀላሉ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚፈልጉትን ምርት መሸመት እንደሚያስችላቸው ገልጸዋል።

ከዘግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት አቶ መለሰ ካሳው በአካባቢው በሚገኙ የቅዳሜና እሁድ ገበያ የተለያዩ የፍራፍሬ ምርቶችን ለሸማቹ ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ። የቅዳሜና እሁድ ገበያ ከመደበኛው ገበያ ዋጋ ከፍ ያለ ልዩነት እንዳለው አቶ መለሰ ይገልጻሉ። ይህም ከአንድ ምርት በኪሎ ከ40 ብር እስከ 60 ብር ድረስ የዋጋ ልዩነት እንዳለው ተናግረዋል። ለምሳሌ፦ የ50 ብር የዋጋ ልዩነት ማለት አምስት ኪሎ የፍጆታ ምርት ለሚገዛ አንድ ሸማች የ250 ብር ተጨማሪ ወጪን እንደሚያስቀርለት ጠቅሰዋል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አሸናፊ ብርሃኑ የከተማ አስተዳደሩ 282 ለሚሆኑ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች የግብይት ቦታዎችን በነፃ ከመፍቀድ ጀምሮ የምርት ትስስር እንዲፈጥርላቸው ያደረገው የኑሮ ውድነት ጫናን ለመከላከል መሆኑን አውስተዋል።

እንደ አቶ አሸናፊ ገለጻ በመዲናዋ በሚገኙ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች አንዳንድ ነጋዴዎች ገበያዎቹ ከታሰበላቸው ዓላማ በተቃራኒ ምርቶችን ሲሸጡ በመገኘታቸው እርምጃዎች እየተወሰዱ ይገኛሉ። በቅዳሜና እሁድ ገበያዎችም ሆነ በገበያ ማዕከላት የሚገኙ ነጋዴዎች ጥራቱን የጠበቀ ምርት በተተመነው ዋጋ መሠረት ለመሸጥ ግዴታ የገቡ እንደመሆናቸው መጠን፣ ማንኛውም ህገ-ወጥ የግብይት ሂደት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን አሳውቀዋል።

በየደረጃው የሚገኙ የንግድ ቁጥጥር አመራሮችና ባለሙያዎች በቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎችም ሆነ በገበያ ማዕከላት የሚፈጸሙ ህገ-ወጥ የግብይት ሂደቶችን በመከታተል መፍትሄ የመስጠትና አስተማሪ እርምጃ እየወሰዱ የመሄድ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የመወጣት ግዴታ እንዳለባቸው ጠቁመዋል። ህብረተሰቡም ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በመከላከል ረገድ ጥቆማ ከመስጠት ጀምሮ ሙቡቱን ለማስከበር እያደረገ ያለውን አዎንታዊ ተሳትፎ አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አቶ አሸናፊ አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ የ2019 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት የሥራ አፈጻጸሙን በገመገመበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሐቢባ ሲራጅ፤ ቢሮው በሦስቱ ወራት አገልግሎት በመስጠት፣ አቅርቦትን በማሳለጥ እና ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ረገድ ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸውን ገልጸዋል።

ከአቅርቦት አንፃር ያለፉት ጊዜያት በርከት ያሉ ህዝባዊና ኃይማኖታዊ በዓላት የነበሩበት መሆኑን ገልጸው፣ ከመደበኛ አቅርቦት ባሻገር ለበዓላቱ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በማቅረብ ረገድ ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል። ይህን ለማሳለጥ የሚያግዙ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎችን ቁጥር ማሳደግና ደረጃቸውን የማሻሻል ሥራ መከናወኑን ነው የጠቀሱት። የገቢያ ማዕከላትን ቁጥር ከማሳደግ አንፃር ሁለት ተጨማሪ የገቢያ ማዕከላትን በለሚ እና በየካ ጉራራ ላይ ወደ አገልግሎት ማስገባት እንደተቻለም ተናግረዋል።

የዕውቀት ቤቶቹ ማዕድ

በለይላ መሀመድ

ወደ አቡነ ባሲሊዮስ ቅድመ መጀመሪያ፣ መጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግቢ ሲዘልቁ ቀድሞ የሚቀበልዎት የተለመደው የትምህርት ቤት ጫጫታና የደወል ድምፅ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም በልምላሜ ያጌጠውና የዓይን ማረፊያ የሆነው አረንጓዴው ምድረ ግቢም ጭምር እንጂ። ትምህርት ቤቱ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ይገኛል፡፡

በትምህርት ቤቱ እየተከናወነ ያለው የከተማ ግብርና የአካባቢ ውበትን ከማስጠበቅ ባለፈ ለተማሪዎች የተግባር ማስተማሪያ፣ ለመምህራንና ለመጋቢ እናቶች ተጨማሪ ገቢ፣ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ደግሞ የምግብ አቅርቦት ምንጭ ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝ በስፍራው ተገኝተን ባደረግነው ቅኝት ለመረዳት ችለናል።

በተለይም ተማሪዎች ከመጽሐፍ ያገኙትን እውቀት በተግባር እንዲያውሉ በማድረግየስራ ባህላቸውንእንዲያዳብሩና ከሸማችነት ወደ አምራችነት የሚያደርስ ልምድ እንዲያገኙ እድል የሚፈጥር ስለመሆኑም አያጠራጥርም።

የስምንተኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ሙሉ አሸናፊ ከሁለት ዓመት ወዲህ በትምህርት ቤቱ በሚካሄደው የከተማ ግብርና ስራ ውስጥ ተሳታፊ ነው። በተሰጠው የማምረቻ ቦታ የእርፍት ጊዜውን ተጠቅሞ ከክፍል ጓደኞቹ ጋር በመሆን የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን ያለማል፡፡ በክፍል ውስጥ በንድፈ ሐሳብ የሚማረውን ትምህርት በእርሻ ማሳው ላይ በተግባር ማየቱ የመረዳት አቅሙን አጎልብቶለታል። በዚህም የትምህርቱን ይዘት በቀላሉ ከመረዳት ባለፈ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንደረዳው ነግሮናል።

የከተማ ግብርናው በትምህርት ቤቱ ግቢ ብቻ እንዲቀር አልፈለገም። በመኖሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ዕቃዎችን ተጠቅሞ ካሮት፣ ዝኩኒና ሰላጣ በማምረት የቤተሰቡን የምግብ ፍጆታ ለመደገፍ ችሏል። በትምህርት ቤቱና በቤቱ የተለማመደው የከተማ ግብርና ተሞክሮ በቀጣይ ህይወቱ ላይ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወትም ተረድቷል።

ተማሪ ነቢል ኑረዲንም በተመሳሳይ ተሞክሮውን በመውሰድ በቤተሰቡ ጓሮ ውስጥ ጎመን፣ ቆስጣና ዝኩኒ በማልማት ላይ ነው። ነቢል የከተማ ግብርና የአርሶ አደር ሙያ ያላቸው ሰዎች ብቻ የሚሳተፉበት ሥራ እንዳልሆነ ከተሞክሮው ተምሯል። በትንሽ ቦታና በተለያዩ ዕቃዎች ላይ እንኳን አትክልት ማምረት እንደሚቻል ተረድቷል። ከዚህ ልምዱ ወደፊት በትልቅ የእርሻ መሬት ላይ የከተማ ግብርናን በስፋት ለመሥራት እንደሚፈልግ ይገልጻል።

በከተማ ግብርና ስራው የሚሳተፉት ተማሪዎች ብቻ አይደሉም፤ መጋቢ እናቶች፣ መምህራንን ጨምሮ የትምህርት ማህበረሰቡ ነው፡፡ ወይዘሮ እመቤት መሰለ በትምህርት ቤቱ መጋቢ እናት ናቸው፡፡





ፎቶ- በገነት ወንድሙ
በአቡነ ባሲሊዮስ ቅድመ መጀመሪያ፣ መጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የከተማ ግብርና ስራዎች በከፊል

“የከተማ ግብርና የትምህርት ቤቱን አካባቢ ከማሳመር ባለፈ የተማሪዎችን የማሰብ፣ የመመራመርና ችግርን በተግባር የመፍታት አቅም ለማጎልበት ያግዛል። ተማሪዎች በተግባር ያገኙትን እውቀት ወደ ቤታቸው በመውሰድ ለቤተሰቦቻቸው ማስተላለፍ መቻላቸውም የዚህ ስራ አንዱ ውጤት ነው”

በየዕለቱ ከሚሰጡት የምገባ አገልግሎት በተጨማሪ ትምህርት ቤቱ በሰጣቸው የእርሻ ቦታ በመጠቀም የጓሮ አትክልትና ቅመማ ቅመሞችን ያመርታሉ። ትርፍ ጊዜያቸውን ተጠቅመው በሚያለሙት ማሳ ዝኩኒ፣ ኮባ፣ ጎመን፣ ድንች፣ ካሮት፣ ቀይ ሥርና አብሽ የሚያመርቱ ሲሆን፤ ምርቱ ሲደርስ ለቤታቸው ፍጆታ፣ ለትምህርት ቤቱ ምገባ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ለሚገኘው የአካባቢው ማህበረሰብ ለሽያጭ በማቅረብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን እያሳደጉ ይገኛሉ። ሽጠው የሚያገኙትን ገንዘብ ለትራንስፖርት ይጠቀማሉ። በተለይም በክረምት ወራት ድንች ገዝተው እንደማያውቁ ሲገልጹ የውስጣቸውን ደስታ ፊታቸው ላይ የሚታየው ፈገግታ ይናገራል።

በትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርና መምህራንም ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ከእነዚህም አንዱ መምህር ይልቃል ስመኝ ይገኙበታል። መምህር ይልቃልን ያገኘናቸው ትምህርት ቤቱ በሰጣቸው የእርሻ ማሳ ውስጥ ያለሙትን አትክልት ሲንከባከቡ ነበር፡፡ የተለያዩ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን በማልማት የቤተሰባቸውን ፍጆታ ከመደገፍ ባለፈ ተጨማሪ ገቢ ማግኘት መቻላቸውን ይገልጻሉ፡፡ በተለይ የሸንኩርት ምርታቸው የሚያስገኘው ጥቅም ቀላል አለመሆኑን ጠቅሰው፣ አሁን ላይ እየኮተኮቱት ያለው የሸንኩርት ማሳ በቅርቡ ለምግብነት እንደሚደርስና ይህም ቤታቸውን እንደሚደጉመው ያምናሉ።

ባለፈው ዓመት ከሁለት ኩንታል በላይ ሽንኩርት በማምረት ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን ያስታውሳሉ። የመምህሩ ተሳትፎ በግል የአትክልት ምርት ብቻ አልተወሰነም። ከሌሎች መምህራን ጋር በመሆን በማህበር ተደራጅተው የከብት ማድለብ ስራም ያከናውናሉ። በ100 ሺህ ብር ካፒታል የተጀመረው የከብት ማድለብ ስራ አሁን ላይ ወደ 300 ሺህ ብር አድጓል።

የከተማ ግብርና ለመማር ማስተማር ሂደቱ

የትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርና ለተማሪዎች የሚያስገኘው ጥቅም ከምርት ተጠቃሚነት በላይ ነው። በክፍል ውስጥ በሳይንስና በሌሎች ትምህርቶች የሚማሩትን በእጽዋት እድገት፣ በአፈር ዝግጅት፣ በውኃ አጠቃቀምና በምርት ሂደት ላይ በቀጥታ የሚመለከቱበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

መምህር ወንደሰን ብርሃኑ ተማሪዎች በንድፈ ሐሳብ የተማሩትን በተግባር እንዲያረጋግጡ ከሚያግዙ መምህራን መካከል ናቸው። ሳይንስን በተግባር ማስደገፍ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል። ድንች፣ አቮካዶ፣ ዘይቱን እና ዝኩኒ ከመሳሰሉ አትክልቶች ጋር ተማሪዎችን ማስተዋወቅና አመራረታቸውን ማሳየት ዕውቀታቸውን ያበለፅጋል።

በቤት ውስጥ አትክልቶችን ማየት፣ በምግብ ላይ መጠቀም እና ከዘር ጀምሮ እስከ ምርት ድረስ ያለውን ሂደት ማወቅ ልዩነት አለው፡፡ ተማሪዎች ቆስጣ፣ ካሮት፣ ድንች፣ አቮካዶ፣ ዘይቱና እና ዝኩኒ የመሳሰሉ እጽዋትን በማሳው ላይ በማየት የአመራረት ሂደታቸውን ይማራሉ። አንዳንድ አትክልቶችን ከዚህ በፊት በምግብነት ቢያውቋቸውም አመራረታቸውን በተግባር ማወቃቸው ለተማሪዎቹ የመረዳት አቅማቸውን ለማጎልበትም ሆነ አጠቃላይ ለመማር ማስተማር ሂደቱ እገዛ እንደሚያደርግ መምህሩ ያብራራሉ።

በዚህ መንገድ የከተማ ግብርና የትምህርት ቤቱን አካባቢ ከማሳመር ባለፈ የተማሪዎችን የማሰብ፣ የመመርመርና ችግርን በተግባር የመፍታት አቅም ለማጎልበት ያግዛል። ተማሪዎች በተግባር ያገኙትን እውቀት ወደ ቤታቸው በመውሰድ ለቤተሰቦቻቸው ማስተላለፍ መቻላቸውም የዚህ ስራ አንዱ ውጤት እንደሆነ መምህር ወንደሰን አብራርተዋል።

የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር አቶ ለገሰ ማሞ እንደሚገልጹት፤ ትምህርት ቤቱ 7 ሺህ 738 ተማሪዎች እና 350 መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች አሉት። በትምህርት ቤቱ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ በሰፊው በተጀመረው የከተማ ግብርና 19 ያህል የአትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶች፣ ቡና፣ የሰብል ምርቶች (እንደ በቆሎና ሽምብራ)፤ የወተት ላም እርባታና የከብት ማድለብ ስራዎች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም የትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ሰራተኞች በማህበር ተደራጅተው ኮምፖስት ወይም ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ በማምረት ለገበያ እያቀረቡና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን እያሳደጉ ይገኛሉ።

እንደ ርዕሰ መምህር አቶ ለገሰ ገለጻ፤ በመምህራንና በመጋቢ እናቶች የሚመረቱ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች ከራሳቸው የምግብ ፍጆታና ለገበያ እያቀረቡ ገንዘብ ከማግኘት በተጨማሪ ለትምህርት ቤቱ ምገባ በማቅረብ የምግብ ወጪን ይደግፋሉ። የከተማ ግብርናው ለአካባቢው ማህበረሰብ ጥቅም እየሰጠ ይገኛል፡፡ በክረምት ወቅት የትምህርት ቤቱ ምገባ በማይኖርበት ወቅት ስጋና ወተትን ጨምሮ በትምህርት ቤቱ የሚመረቱ የግብርና ምርቶችን የአካባቢው ማህበረሰብ በተጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የገበያ ማረጋጋት ሚና እየተጫወተ ይገኛል። የማምረት ስራው በወቅታዊ ዝናብ ብቻ የተገደበ አይደለም። በክረምትና በበልግ ዝናብ ከሚመረተው ባለፈም የከርሰ ምድር ውኃን በመጠቀም በዓመት ሦስት ጊዜ የማምረት ስራ ይከናወናል።

ርዕሰ መምህሩ አያይዘውም፤ ትምህርት ቤቱ በከተማ ግብርና ስራ ላይ ትኩረት ከመስጠት ባለፈ ሠራተኞቹ ከባህላዊ አሠራር ወደ ዘመናዊ የአመራረት ዘዴ እንዲሸጋገሩ ከወረዳና ከክፍለ ከተማ ጋር በመተባበር ስልጠና ይሰጣል። ምርጥ ዘር በማቅረብና የተለያዩ የግብርና ተሞክሮዎችን በማስፋፋትም ተማሪዎች የተማሩትን ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲያስተላልፉ ይደረጋል። በዚህ መልኩ የትምህርት ቤቱ ግቢ ለማስተማሪያነት ብቻ የሚውል ቦታ ሳይሆን የምርት፣ የክህሎትና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማዕከል ማድረግ ተችሏል።

የከተማ ግብርና እንደ ከተማ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

የቱሪዝሙ ... ከገጽ 8 የዞረ

ተመልክቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማስፋፋት ዳይሬክተር አቶ ሳምሶን አይናቸው ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት መረጃ፣ መንግስት ባለፉት ዓመታት ለቱሪዝሙ ዘርፍ በሰጠው ትኩረት በአዲስ አበባ በርካታ የቱሪዝም መስህብና መዳረሻ ቦታዎች ተገንብተዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የከተማዋን ገፅታ የቀየሩ የኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶችም ተሰርተዋል። እነዚህም በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የቱሪስት ፍሰትና ገቢ በማሳደግ ረገድ የራሱ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከቱ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በፊት በከተማዋ ከቤቶች፣ ፋብሪካዎች፣ ንግድ ተቋማት የፍሳሽ ማስወገጃ የሚወጡ ፍሳሾችና ደረቅ ቆሻሻዎች ወደ ወንዞች ነበር የሚለቀቁት። በዚህ ምክንያትም ወንዞች በከፍተኛ ደረጃ ተበክለው ነበር፡፡ በውስጣቸው ያለው የብዝሃ ህይወት ሀብት ጠፍቶ፤ ለሰዎችም ጤና ስጋት ሆነው ነበር፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ወንዞችን ወደቀደመ ማንነታቸው ከመቀየር ባሻገር ነዋሪዎች ወደ ወንዝ ዳርቻዎች በመሄድ በንፁህ አካባቢ መዝናናትና ንፁህ አየር መውሰድ የሚችሉበትን እድል ፈጥሯል፡፡

“አዲስ አበባ ለረጅም ጊዜ የቱሪስቶች መሸጋገሪያ ሆና ቆይታለች” የሚሉት ዳይሬክተሩ አቶ ሳምሶን፣ የወንዝ ዳርቻና ሌሎች በከተማ የተከናወኑና በመከናወን ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ከተማዋን ከመሸጋገሪያነት ወደ መዳረሻነት ቀይረዋታል፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ከሌሎች የከተማዋ የቱሪዝም መስህብና መዳረሻዎች ጋር ተሳስሮ ተሰርቷል። ለምሳሌ ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ በተከናወነው የወንዝ ዳርቻ ወንዙ ብቻ ሳይሆን ከወንዙ ጋር አብረው አምስት የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ተሰርተዋል፡፡ ወንዙን ወደ ቀደመ ማንነቱ መመለስ፣ የወንዝ ዳርቻውን ቦታ ማልማት፣ የአረንጓዴ ሽፋንን ማሳደግ፣ የቱሪዝም መሰረተ ልማቶች (የሳይክል፣ የእግረኛ መንገዶች፣ መሮጫ ትራክ...) መስራት እና ለኢንተርፕራይዞች የስራ ዕድል የሚፈጠርባቸው ሱቆችን በማካተት ተከናውኗል፡፡

ዳይሬክተሩ አቶ ሳምሶን እንደገለፁት፣ ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ባለው የወንዝ ዳርቻም ስድስት ነባር እና አንድ አዲስ (አራዳ ፓርክ) ፓርኮች ከወንዝ ዳርቻ ልማቱ ጋር ተሳስረው እንዲለሙ ተደርጓል። እንጦጦ፣ የኢትዮ-ኮሪያ ዘማቾች መታሰቢያ ፓርክ፣ አራዳ፣ ወዳጅነት፣ አምባሳደር፣ ኢሬቻ፣ ፒኮክ ፓርኮች በወንዝ ዳርቻ ልማቱም አብረው ለምተዋል፡፡ በልማቱ ለቱሪስቶች የሥጦታ ዕቃዎችን የሚያቀርቡ፣ የሬስቶራንት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት፣ የቡና መሸጫዎች፣ ሰርቶ ማሳያዎች ለምሳሌ ወደ እንጦጦ አካባቢ በሽመና ስራ የተሰማሩ ወገኖች ሙያውን በተግባር ለቱሪስቱ የሚያሳዩበት ቦታዎች እንዲኖሩ ተደርጓል። ለጎብኚዎች አቅጣጫና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶች የማስቀመጥ፣ መፀዳጃ ቤቶች፣ ማረፊያዎች፣ ፋውንቴኖች፣ የእግረኛ መንገዶች እና ሌሎችም ተሰርተዋል። በተጨማሪም የአካባቢውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ ባህልና ወግ የሚያሳዩ እንዲሁም በኪነ ጥበብ ረገድም ለሀገር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ባለሙያዎች ሐውልት እንዲቆምላቸው ተደርጓል። ይህም የከተማዋን ገፅታ በመቀየርና የቱሪዝም ስበት ማዕከልነቷን በማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አቶ ሳምሶን ያስረዳሉ፡፡

የወንዝ ዳርቻዎች እንደ ቱሪዝም መስህብ ስፍራ እንዲጎበኙ ከማድረግ አኳያም ቢሮው አዳዲስ የቱሪዝም መስህብ ልማቶች ከተከናወኑ በኋላም በከተማዋ የሚገኙ አስጎብኚ ማህበራትና ባለሙያዎች በአካል እንዲጎበኙ በማድረግና በአዳራሽ ደግሞ በመስህቦቹ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም አስጎብኚዎች በሚያዘጋጁት የጉብኝት ፓኬጆች አካትተው እንዲያስጎበኙ እየተደረገ እንደሚገኝ አቶ ሳምሶን ጠቁመዋል፡፡

የአዲስ አበባን መልካም ገፅታና ታሪክ በመቀየር፣ አዲስ አበባ ከተወዳዳሪነት ወደ ተመራጭነት እንድትመጣ በማድረግ፣ የቱሪስቶችን ፍሰት በመጨመር፣ የስራ ዕድል በመፍጠር የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ እና ሌሎች የቱሪዝም መዳረሻ ልማቶች ሚና የጎላ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ከጉቲባ ወ/ሮ አዳነች አቢቤ በተለያዩ ጊዜያት እንደተናገሩት የወንዝ ዳርቻ ልማቱ አዲስ አበባን ለመኖር፣ ለመስራትና ለመዝናናት ምቹ፣ አረንጓዴና ውብ ከተማ እያደረጋት ይገኛል፡፡ ከተማዋን ወደ ቱሪስት መዳረሻነት እንድትቀየር አድርጓል፡፡

የቱሪዝም መምህርና ተመራማሪው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ቀደም ባሉት ዓመታት የአዲስ አበባ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች የቆሻሻ መጣያ በመሆናቸው በከፍተኛ ደረጃ ተበክለው፣ የተረሱና የከተማዋ መጥፎ የሆነ ገፅታ ማሳያ ነበሩ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ፣ ከተማዋን የማስዋብ ስራዎች ይህንን ገፅታ እየቀየሩት ነው፡፡

ከተማን ውብ፣ ፅዱና ማራኪ ማድረግ እንዲሁም ሰዎች የሚዝናኑባቸውን አደባባዮችና ፓርኮች የማዘመንና የማስፋፋት ስራዎች ከቱሪዝም እድገት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት እንዳላቸው ያነሱት የቱሪዝም ተመራማሪው፤ በወንዝ ዳርቻ ልማት ምቹና ደህንነታቸው የተጠበቀ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶች፣ ጎብኚዎች አረፍ የሚሉባቸው መቀመጫዎች፣ የተለያዩ አበቦች፣ ዕፅዋትና አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ዘመናዊ ካፌዎች፣ ሬስቶራንቶችና የተለያዩ የባህልና የመዝናኛ አገልግሎቶች ተካትተው መሰራታቸው የከተማዋን መስህብነት በከፍተኛ ደረጃ የሚጨምሩ ናቸው። ጎብኚዎች በእግራቸው እየተንቀሳቀሱ የከተማዋን ውበት እንዲመለከቱ፣ ነፋሻማ አየር እንዲወስዱ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በቀጥታ እንዲተዋወቁ፣ የከተማዋን ህይወትና ባህል ቅርብ ሆነው እንዲረዱ እድል ይፈጥራል። ይህም የቱሪስቶችን ፍሰት ከማሳደጉም በላይ በከተማዋ የሚኖራቸውን የቆይታ ጊዜ ያራዝማል።

የቱሪስቶችን ቆይታን የበለጠ ለማራዘም የተቀናጀ የቱሪዝም ጉብኝት ፓኬጅ ማዘጋጀት ወሳኝ እንደሆነ አያሌው(ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡ በከተማዋ የሚገኙ ታሪካዊና ሳይንሳዊ ሙዚየሞች፣ ዘመናዊና ተፈጥሯዊ ፓርኮች፣ የባህል ገበያዎችና የእደ-ጥበብ ማዕከላት፣ የወንዝ ዳርቻዎችና የኮሪደር ልማቶች በአንድ ላይ ተካትተው በፓኬጅ ሲዘጋጁ ጎብኚዎች ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ ያደርጋል፡፡

የጎብኚዎች የቆይታ ጊዜ እየተራዘመ ሲመጣ ከተማዋ ከዘርፉ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬና ገቢ በዚያው ልክ ያድጋል። ህብረተሰቡም ሰፊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ይሆናል። የአስጎብኚ ድርጅቶች፣ የሆቴልና የትራንስፖርት አቅራቢዎች፣ ሬስቶራንቶች፣ የባህልና የእደ-ጥበብ አልባሳት አምራቾችና ነጋዴዎች፣ በአካባቢው የሚገኙ ወጣቶችና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በጥቅሉ የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ከከተማዋ የኮሪደር ልማት እና ከሌሎች የከተማ ማዘመን እንቅስቃሴዎች ጋር ተዳምሮ የአዲስ አበባን የቱሪዝም እንቅስቃሴ በማነቃቃት፣ የከተማዋን ዓለም አቀፍ ገፅታ በመገንባት፣ ለነዋሪዎችና ጎብኚዎች ምቹ የሆነች ከተማ በመፍጠር ረገድ ቀላል የማይባል ሚና ይኖረዋል፡፡

ምናብና... ከገጽ 11 የዞረ

አሁን ላይ ትዕምኒት በቴክኖሎጂው ዓለም ውስጥ ያሉ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ድምፅ እንዲኖራቸው ለማስቻል ምርምሮችን ታደርጋለች። በቴክኖሎጂ ዘርፍ በተለይ በኤአይ ውስጥ ጥቁሮች በቂ ውክልና የላቸውም በሚል መነሻነት፣ ታዋቂውን “Black in AI” የተሰኘ ድርጅት መስርታለች፡፡ በአፍሪካ አገራት ውስጥ የሳይንስና የቴክኖሎጂ አቅም እንዲጎለብት “Distributed AI Research Institute (DAIR)” የተባለ ተቋም አቋቁማለች። ይህ ተቋም የኤአይ ምርምር ከማህበረሰባዊ እውነታዎች ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ሰፊ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።

የኮምፒዩተር ሳይንቲስቷና የኤአይ ተመራማሪ የሆነችው ትዕምኒት በቴክኖሎጂው ዓለም ከምታደርገው ታላቅ አስተዋጽኦ ባሻገር ጥልቅ የሆነ የሙዚቃ ፍቅር አላት። ሙዚቃ ለእሷ ከቀላል መዝናኛ በላይ ለአዕምሮ ማሰላሰል፣ የፈጠራ ስራዎችን ለመንደፍ እና ለአዳዲስ ሀሳቦች መነሻነት ትጠቀማለች፡፡

በአጠቃላይ ኪነ ጥበብና ሳይንስ በሰው ልጅ የእድገት ጉዞ ውስጥ ተቀናጅተው የሚጓዙ፣ አንዱ የሌላውን ጉድለት የሚሞላ የሁለትዮሽ የህይወት መስመር ናቸው። ኪነ ጥበብ ስሜትን በመቅረጽና ምናብን በማስፋት ለአዕምሮ ነጻነትንና ፈጠራን ሲሰጥ፣ ሳይንስ ደግሞ ያንን ምናባዊ ሃሳብ ገቢራዊ እንዲሆንና በሂሳብ ቀመሮች እንዲገለጥ ያደርገዋል። ስለዚህም እንደ ሊዮናርዶ ዳቪንቺ፣ አልበርት አንስታይን እና ትዕምኒት ገብሩ የመሳሰሉ ታላላቅ አእምሮዎች ህይወታቸው እንደሚያሳየው፣ ሳይንሳዊ ግኝቶች ኪነ ጥበባዊ እሴቶችና ስሜታዊ ብልህነት ጋር ሲተሳሰሩ ዓለምን የሚቀይሩ ታላላቅ ፈጠራዎች መፍጠር እንደሚችሉ ነው፡፡

የዕውቀት... ከገጽ 16 የዞረ

የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንደሰን አካሌ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ የከተማ ግብርና በትምህርት ቤት ብቻ የተገደበ እንቅስቃሴ አይደለም። በመዲናዋ በተለያዩ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በነዋሪዎች ዘንድ እየተስፋፋ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በከተማዋ እንደ አጠቃላይ የከተማ ግብርና ተጠቃሚዎች ቁጥር 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ደርሷል። በተቋማት ደረጃ ደግሞ 2 ሺ 777 የሚሆኑ የግልና የመንግስት ተቋማት የከተማ ግብርናን እየተገበሩ ናቸው፡፡ የትምህርት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ሌሎች አገልገሎት ሰጪ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሞዴልነት የሚጠቀሱ ትምህርት ቤቶች አሉ። በበጀት ዓመቱ በሩብ ዓመቱ ብቻ 42 አዳዲስ ተቋማት የከተማ ግብርናን መተግበር ጀምረዋል።

አቶ ወንደሰን አያይዘውም፤ በትምህርት ቤቶች የሚከናወነው የከተማ ግብርና የትምህርት ቤቶቹን ምድረ ግቢ አረንጓዴና ውብ ከማድረግ ባለፈ ለተማሪዎችና ለመምህራን የተሻለ የመማር ማስተማር ሁኔታ ለመፍጠር ያግዛል። ተማሪዎች የሚማሩትን በተግባር በመመልከት የበለጠ እንዲረዱ ያስችላቸዋል። ከዚህም በተጓዳኝ በአነስተኛ ደመወዝ ለሚሰሩ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰቦች በቀላል ዋጋ ምርት የማግኘት እድል ይፈጥራል። ከዚህም በላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የቀሰሙትን ዕውቀት ለወላጆቻቸውና ለጎረቤቶቻቸው በማስተላለፍ የከተማ ግብርናን በማህበረሰብ ደረጃ እንዲስፋፋ እገዛ ያደርጋል።

የከተማ ግብርና በስርዓተ ትምህርቱ (ካሪኩለም) ውስጥ መካተቱ ተማሪዎች በተግባር የሚያገኙትን እውቀት ወደፊት የሥራ ዕድል እንዲቀይሩ ያግዛል። ይህም ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ሥራ ፈላጊ ከመሆን ይልቅ ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሠረት ይጥላል።

ዳይሬክተሩ እንደሚያስረዱት፤ ይህ እንቅስቃሴ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ሳይወሰን በቴክኒክና ሙያ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም እየተተገበረ ይገኛል። ይህም በዘርፉ የሚገኘውን ዕውቀትና ክህሎት ወደ ሥራ ፈጠራ ለመቀየር ያለውን እድል ያሰፋል። በከተማ ውስጥ የሚገኙ ውስን ቦታዎችን በአግባቡ በመጠቀም ምግብን ከደጅ ማምረት የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም ከሚያግዙ አማራጮች አንዱ ነው። በራስ የሚመረት ምግብ የገበያ ጥገኝነትን ይቀንሳል፤ የተረፈውን በመሸጥ ተጨማሪ ገቢ ለማግኘትም ያስችላል።

ከዚህ አንጻር የከተማ ግብርና የምግብ ዋስትናን ከመደገፍ ባለፈ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማጠናከር፣ የስራ ባህልን ለማሳደግና የከተማውን ማህበረሰብ የራስ አቅም ለማነልበት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ህብረተሰቡ ይህንን በትምህርት ቤቶችም ሆነ በተለያዩ ተቋማት እየታየ ያለውን አበረታች የከተማ ግብርና በጎ ተሞክሮ በመውሰድ ከሸማችነት ወደ አምራችነት በመሸጋገር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የኑሮ ውድነትን መቋቋም ይኖርበታል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ መለያ ቁጥር ቦሌ/12/136/7/8/119524/00 ሴሪ ቁጥር - 1626049 ሰለሞን ክቤ አሊሾ ስም በተቋማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋብኞው በማናቸውም ምክንያት ይገፔዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፊኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 በቤት ቁጥር 621 በካርታ ቁጥር 06/15/13157/00 በአቶ በላይ ቦጋለ ስም በእጃቸው ላይ መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቀጥሮ ምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማናት አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በለሚ ኩራ ክ/ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በብሩክ ጌትነት ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/42/25/119061/00 ሴሪ ቁጥር 1616911 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ከንደሚኒየም ቤት አርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልያ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገፔዋለሁ፤ አስይገፔዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማናት አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ከላይ በርእሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 063 በእነ ፅጌ ከበደ አለሙ ስም የተመዘገበው የካዳስተር ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020900970 ሴሪ ቁጥር R 0107556 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 27/10/2018 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይገፔዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት

እነ/አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ወ/ሮ እልፍነሽ ሀሰን ሰኢድ በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000101002393 በሴሪ ቁጥር R 025357 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፊኬት/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገፔዋለሁ/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፊኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 20 ቀበሌ 52 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር -------- በካርታ ቁጥር 14/144/4098/9487/01 በአቶ/ወ/ሮ/እነ አዳነች አድማሱ እና ሁለት ልጆች ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይገፔዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገፔዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 19 ቀበሌ 58 በአዲሱ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር -------- በካርታ ቁጥር 15/01/28952/822813/823163/02 ለአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት/እነ ፋናዬ ወ/መስቀል ዘገየ በሴሪ ቁጥር 071130436 ተሰጥቷቸው የነበረው ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማናቸውም ምክንያት ይገፔዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገፔዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ጉዳዩ፡- <u>ለኦዲት ባለሙያ ጥሪ ስለማድረግ</u>

ልሔም የበጎ አድራጎት ማህበር ከሲቪል ማህበረሰብ ባለሥልጣን በመዝገብ ቁጥር 6730 ሕጋዊ ፍቃድ በማውጣት በጎዳና የወደቁ የዕለት ጉርስ የሚፈልጉ አቅመ ደካሞችን ችግር ለመፍታት በስድስት ኪሎ በይበልጥ በቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን አካባቢ የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡

ማህበሩ የ2018 ዓ.ም በጀት አመት የሂሳብ ስራ በውጭ ኦዲተር ለማስመርመር ስለሚፈልግ ይህ የጥሪ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለተከታታይ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ መጥታችሁ አዲት እንድታደርጉልን እንጠይቃለን፡፡

ልሄም በጎ አድራጎት ማኅበር

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እነደተሞከረው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር 07095/A በሴሪ ቁጥር 011702 በወ/ሮ ሙሉነሽ አብሴ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት ኦርጂናል ካርታ ኮፒ የጠፋባቸው ስለሆነ ካርታው የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማናት አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በአቶ ተረፈ አሰፋ አየለ ስም የተመዘገበ የኮንደሚንየም ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር ወ3/04-3-38-100-6145/00 ሴሪ ቁጥር 085411 የጠፋባቸው መሆኑን በ26/02/2019 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገፔዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮ/ቀ/ክ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ለ/ኩ3/7/1/7742/0042/8/00 ሴሪ ቁጥር 0239196 ቦታ ስፋት 90 ካ.ሜ በምንተስኖት ግዛቸው መንገሻ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ተደራጅቶ በመመሪያ መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

አመልካች አቶ ዮሃንስ ታደሰ የሙሉነሽ ፍጥረት ህጋዊ ሾሾ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙት በቀን 30/2/2019 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በካርታ ቁጥር ቦሌ/93/1/13/13646/00 የቦታው ስፋት በሰነድ 369 ሜ.ካ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልያ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገፔዋለሁ፤ አስይገፔዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 011 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር 008/87/1/12196 የተሰጠበት ቀን 18/09/2009 ሴሪ ቁጥር 077051 የሆነው በኢሃይ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 02/03/2019 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይገፔዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት

አመልካች ፀጋ ተሾመ በራሳቸው ስም የተመዘገበ በቀን 30/2/2019 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በካርታ ቁጥር ቦሌ/9/39/3/7/116142674 7/01 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ አርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልያ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገፔዋለሁ አስይገፔዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

ኪኢ.ኢ.ኤን. ሪል እስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 በይዞታ መለያ ቁጥር AA0006020045601 0605 ሴሪ ቁጥር C 257902 የሆነው የጋራ መኖሪያ ቤት በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋብኞው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገፔዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት







ጤናችንን የምንጠብቀው ህዳር አስራ ሁለት ቀን ቆሻሻን በማቃጠል አይደለም!

ቆሻሻን አደቃጥሉ!

» ከዓመት ዓመት ቆሻሻ ይፀዳል፤ ጤና ይጠበቃል! አካባቢ ይፀዳል፤ ከተማችን ትዋባለች።

» ቆሻሻን ማቃጠል ሀብትን ማቃጠል እንዴሆነ ያውቃሉ?

» ታዲያ ለምን ብለው ቆሻሻን ያቃጥላሉ? ለምን ብለው ተፈጥሮ ያዳለችንን ንፁህ አየር ይበክላሉ?

» ወርቅ የሆነውን ሀብት አመጽ አያጽርጉ !

የአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ!

ዓለምን ከአየር ንብረት አደጋ መታደጊያ መድረክ

በቶለሳ መብራቴ



የአየር ንብረት ለውጥ ድንበር የማይገድበው፣ ሀብታምና ደሃ ሀገር ሳይል የዓለምን ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ የምግብ ዋስትናና የተፈጥሮ ሀብት የሚፈታተን የዘመናችን ታላቅ ስጋት ነው። ይህንን እየከፋ የመጣ የዓለም ሙቀት መጨመር እና የአካባቢ መራቆት በጋራ ለመመከት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ስምምነት ፓርቲዎች ጉባዔ (COP) በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ እውን ሆነ።

ታሪካዊው የመጀመሪያው የኮፕ ጉባዔ (COP1) እ.ኤ.አ በ1995 በጀርመን በርሊን ከተማ ሲጀመር፣ ዋና ተልዕኮው በሳይንሳዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት መቀነስና ለተለዋዋጭ የአየር ንብረት የሚበጅ ዓለም አቀፍ ትብብር መፍጠር ነበር። ባለፉት ዓመታት ጉባዔው የዓለም መሪዎች በንጹሕ ኃይል፣ በደን ጥበቃ፣ በአየር ንብረት ፋይናንስና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ የሚደራደሩበት ቁልፍ መድረክ ሆኖ ዘልቋል። በተለይም በ2015 የተፈረመው ታሪካዊው የፓሪስ ስምምነት፣ የዓለም ሙቀት ጭማሪን ከ2 ዲግሪ ሴልሺየስ በታች ለማቆየትና ወደ 1 ነጥብ 5 ዲግሪ ሴልሺየስ ለመገደብ ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን የታሰረበት ወሳኝ ምዕራፍ ነው።

የኮፕ ጉባዔን የማስተናገድ ዕድል በአምስት የተባበሩት መንግሥታት የክልል ቡድኖች (አፍሪካ፣ እስያና ፓስፊክ፣ ምሥራቅ አውሮፓ፣ ላቲን አሜሪካና ካሪቢያን፣ እንዲሁም ምዕራብ አውሮፓ) መካከል በየዓመቱ እየተፈራረቀ ይሰጣል። አዘጋጅ ሀገር የሚመረጠው በክልሉ አባል ሀገራት ስምምነትና በጉባዔው ውሳኔ ሲሆን፣ የተመረጠው ሀገር የመሠረተ ልማት አቅም (ትላልቅ የስብሰባ አዳራሾችና ሆቴሎች)፣ አስተማማኝ የጸጥታና ደህንነት ዋስትና፣ የፋይናንስ አቅም፣ የሎጂስቲክስና የትራንስፖርት ዝግጁነት በኮፕ ሴክሬታሪያት ተገምግሞ በጉባዔው የመጨረሻ ውሳኔ ይጸድቃል።

እስካሁን 30 ሀገራት ጉባዔውን ያስተናገዱ ሲሆን፣ የ31ኛው ጉባዔ (COP31) አዘጋጅነት ግን ልዩ ታሪክ አስመዝግቧል። ቱርክዬ እና አውስትራሊያ ጉባዔውን ለማዘጋጀት ባደረጉት የረጅም ጊዜ ፉክክር ምክንያት በ2025 በብራዚል (COP30) ውሳኔ ሳያገኝ ቆይቶ ነበር። በመጨረሻም ሁለቱ ሀገራት በደረሱበት የሥራ ክፍፍል ስምምነት መሠረት፣ ቱርክዬ የጉባዔውን አዘጋጅነትና ፕሬዝዳንትነት ስትይዝ፣ አውስትራሊያ ደግሞ የድርድር አመራርነቱን እንድትወስድ ተወሰነ።

በዚሁ መሠረት፣ COP31 በቱርክዬ አንታሊያ ከተማ እየተካሄደ ይገኛል። በጉባዔው ላይ ቱርክዬ በአስተናጋጅነት ስትመራ፣ አውስትራሊያዊው ክሪስ ቦወን የድርድሩን ሂደት በመምራት ላይ ናቸው።

ዛሬ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰማ ባለበት ወቅት፣ ኮፕ ሀገራት የኢኮኖሚ ልዩነታቸውን ወደ ጎን በመተው የጋራ ህልውናቸውን የሚታደጉበት የመጨረሻ ተስፋ ነው። የዘመናችን ትልቁ ፈተናም በወረቀት ላይ የሰፈሩ ስምምነቶችንና ቃል ኪዳኖችን ወደ መሬት አውርዶ በተግባር ማሳየት ነው።

ምንጭ፡- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ስምምነት (UNFCCC) የአሰራር ደንብና መመሪያዎች

የአትሌቲክሱ ተስፋዎች

በሳህሉ ብርሃኑ

አሁን ላይ በአዋቂዎች መድረክ የምናውቃቸው ታላላቅ አትሌቶች ዋነኛው መነሻቸው የዓለም ወጣቶች ኦሎምፒክ ነው። እ.ኤ.አ በ2010 በሲንጋፖር መካሄድ የጀመረው የዓለም ወጣቶች ኦሎምፒክ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ሀገራት በስፖርቱ ዓለም ያላቸውን ብቃት ማጎልበቻና አዳጊዎችን የማፍሪያ መንገድ አድርገው ተጠቅመውበታል። መሠረታዊ ዓላማውም አዳጊ አትሌቶች ከዓለም አቀፍ መድረክ ጋር እንዲተዋወቁ፣ የኦሎምፒክ መንፈስን እንዲለማመዱ እና የስኬት መሰረታቸውን እንዲጥሉ ማስቻል ነው።

አራተኛው የወጣቶች ኦሎምፒክ በአፍሪካ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የማከናወን ኃላፊነቱን በተቀበለችው ምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር ሴኔጋል በዳካር ከተማ ከጥቅምት 21 እስከ ህዳር 4 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ ሲከናወን ቆይቷል። ከ206 ሀገራት የተውጣጡ ከ2 ሺህ 700 በላይ አትሌቶች በተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች ለሀገር ክብርና ለሜዳልያ ሲፋለሙ ስለመቆየታቸው የዓለም ኦሎምፒክ ኮሚቴ መረጃ ያሳያል። ኢትዮጵያም በዚህ መድረክ በአትሌቲክስ፣ በውሃ ዋና፣ በቴኳንዶ፣ በውሹና በብስክሌት ስፖርቶች ተሳትፋለች።

ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተውጣጡ ወጣት አትሌቶች በዳካር ታድመው የውድድሩን ድባብ ያደመቁት ሲሆን፣ አዘጋጇ ሀገር ሴኔጋልም በተደራጀ አቀባበል በማስተናገድ የአፍሪካን የማዘጋጀት አቅም በተግባር አሳይታለች። በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት የዓለም አቀፉ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዝዳንት ክርስቲ ኮቨንትሪ ውድድሩ በአፍሪካ ምድር የሚካሄድ የመጀመሪያው የኦሎምፒክ ኩነት መሆኑን ጠቅሰው፣ “ይህ ለሴኔጋል፣ ለአፍሪካ እና ለመላው የኦሎምፒክ ቤተሰብ ታሪካዊ አጋጣሚ ነው” ብለዋል።

የአፍሪካ የጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ዋሂድ አሾዲ፣ በበኩላቸው የዳካር 2026 አደረጃጀት ስኬታማነት “አፍሪካ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ትልልቅ የስፖርት ውድድሮችን የማስተናገድ ሙሉ አቅም እንዳላት ያረጋገጠ ነው” ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ለአህጉሪቱ ስፖርት ታሪካዊ ምዕራፍ የከፈተው ይህ ውድድር የእስካሁን ሂደት በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች፣ በተለይም በአትሌቲክስ፣ በውሃ ዋና እና በሌሎችም መድረኮች የወደፊቱን የዓለም ስፖርት የሚረከቡ አዳዲስ ተሰጥኦዎች ብቃታቸውን አስመስክረዋል። በዚህ ታሪካዊ የዳካር የወጣቶች ኦሎምፒክ መድረክ ላይም፣ የኢትዮጵያ ወጣት አትሌቶች የሀገራቸውን ገናና የአትሌቲክስ ታሪክ በአዲስ ትውልድ እያደሱና የአሸናፊነት ባህሉን በደማቁ እያስቀጠሉ ይገኛሉ። አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩን ሰንደቅ ዓላማ በኩራት ያውለበለቡት እነዚህ ተስፈኛ ሯጮች፣ በተለይ በረጅምና መካከለኛ ርቀት ውድድሮች ላይ ባሳዩት ድንቅ ፍጥነት፣ የታክቲክ ብስለትና ያልተበገረ ጽናት የተመልካቹን ቀልብ ገዝተዋል። የትናንቶቹን ጀግኖች ፈለግ በመከተል በአፍሪካ ምድር ላይ ያስመዘገቡት አበረታች ውጤት፣ ለኢትዮጵያ ስፖርት ቤተሰብ ተስፋን አጭሯል።

በወጣቶች ኦሎምፒክ ጨዋታዎች ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋን የወርቅ ሜዳሊያ በአትሌት ጁነዲን አብዶ አማካኝነት አስመዝግባለች። በወንዶች 2 ሺህ ሜትር መሰናክል ሩጫ የተወዳደረው አትሌት ጁነዲን አብዶ ርቀቱን በ5:29:30 በማጠናቀቅ አንደኛ በመውጣት ለሀገሩ የወርቅ ሜዳሊያ አምጥቷል።

በተመሳሳይ ኢትዮጵያ ሌላ የብር ሜዳሊያ ማግኘት ችላለች። በሴቶች 3 ሺህ ሜትር ፍፃሜ በኦሪገን በተካሄደው የዓለም ከ20 ዓመት በታች ሻምፒዮና አሸናፊ የነበረችው አትሌት ዮርዳኖስ ፅጋብ ሌላ ድል ለኢትዮጵያ አስመዝግባለች። አትሌት ዮርዳኖስ በወጣቶች ኦሎምፒክ ከባድ ፉክክር በማድረግ ርቀቱን በ9:15:71 በማጠናቀቅ 2ኛ በመውጣት ለኢትዮጵያ የብር ሜዳሊያ አስገኝታለች።

የ2 ሺህ ሜትር መሰናክል የፍጻሜ ውድድር አትሌት ፃድቃን መኮንን 6:32:15 በመግባት 2ኛ ደረጃ በመያዝ የብር ሜዳሊያ ባለቤት ሆናለች። በውድድሩ የኬንያዋ አትሌት ኮስጊ አንደኛ በመውጣት የወርቅ ሜዳሊያውን ስታሸንፍ፣ ፃድቃን መኮንን የብር ሜዳሊያውን አግኝታለች። በሴቶች 800 ሜትር የፍፃሜ ውድድር አትሌት ነፃነት ሰለሞን ድንቅ ብቃቷን በማሳየት ለኢትዮጵያ ሶስተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ አስመዝግባለች።



ፎቶ፦ ከገፀድር

በዳካር ከተማ ሲከናወን በቆየው የወጣቶች ኦሎምፒክ ውድድር ላይ ተሳትፈው ውጤታማ ከሆኑ አትሌቶች መካከል ጥቂቶቹ

18 አትሌቶችን በአምስት የስፖርት ዓይነቶች ያሳተፈችው ኢትዮጵያ 5 ወርቅ፣ 3 ብር እና 1 ነሃስ በአጠቃላይ 9 ሜዳልያዎችን በማግኘት አንደኛ ደረጃን ይዛ አጠናቅቃለች

በወንዶች 1 ሺህ 500 ሜትር የፍፃሜ ውድድር የተሳተፈው አትሌት ዋቢ ወጂራ ርቀቱን በ3:58:73 በማጠናቀቅ አንደኛ በመውጣት ለሀገሩ ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ማምጣት ችሏል። የ3 ሺህ ሜትር የፍጻሜ ውድድር አትሌት ጎይቶም መኮንን 8:08:24 በሆነ ሰዓት በመግባት ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ለኢትዮጵያ የብር ሜዳሊያ ማምጣት ችሏል።

የሴቶች 1 ሺህ 500 ሜትር የፍጻሜ ውድድር አትሌት ኤልሳቤጥ አማረ ድል አድርጋለች። አትሌቷ ርቀቱን ለማጠናቀቅ 4:28:02 ሰዓት ወስዶባታል። አትሌት ዮሚፍ አበበ እንደዚሁ በወንዶች 800 ሜትር በአሸናፊነት አጠናቋል።

18 አትሌቶችን በአምስት የስፖርት ዓይነቶች ያሳተፈችው ኢትዮጵያ 5 ወርቅ፣ 3 ብር እና 1 ነሃስ በአጠቃላይ 9 ሜዳልያዎችን በማግኘት አንደኛ ደረጃን ይዛ አጠናቅቃለች። በዳካር የተመዘገበው በዚህ ድል፣ ተተኪና አዳጊ ወጣቶች፣ የቀድሞ ጀግኖች አትሌቶችን ዓርአያ በመከተል ዳግም ታሪክ የሠሩበት ውድድር መሆኑም ተነግሯል።

የበርካታ ሀገራት ወጣት ብስክሌተኞች እየተሳተፉበት በሚገኘው በዚህ ውድድር በሴቶች ኢትዮጵያ በማህደር ደስታ ተወክላለች። 59 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር በሸፈነው የሴቶች የጎዳና ላይ ብስክሌት ውድድር ማህደር 24ተኛ ሆና አጠናቅቃለች። ማህደር ከባድ ሙቀት በነበረው ቀን ላይ ኪሎ ሜትሩን ለማጠናቀቅ 1 ሰዓት ከ35 ደቂቃ ከ41 ሰከንድ ወስዶባታል። የሴቶች የጎዳና ብስክሌት ውድድር ሩሲያዊቷ አንጀሊና ኖቮሎድስካያ በ1 ሰዓት ከ31 ደቂቃ ከ19 ሰከንድ አጠናቅቃ የወርቅ ሜዳሊያ ስታሸንፍ፣ አውስትራሊያዊቷ ኤልሲ አፕስ የብር እንዲሁም የቼክ ሪፐብሊኳ ሊንዳ ሲትኮቫ የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤት ሆነዋል።

በዳካር የዓለም ወጣቶች ኦሎምፒክ በወርልድ ቴኳንዶ ውድድር ኢትዮጵያን በ48 ኪሎ ግራም ዘርፍ በመወከል የተወዳደረው ወጣት አትሌት ሲፈን ታዬ፣ የዳካርን ከፍተኛ የሙቀት ጫና በመቋቋም የነበረውን አቅም ሁሉ አውጥቶ ተወዳድሯል። ምንም እንኳን አትሌቱ የዓለም አቀፍ ውድድር ልምድ ማነስና የውድድሩ ውጤት እንደጠበቀው ባይሳካለትም፣ በሜዳ ላይ ያሳየው ነጥብ የማስቆጠር ችሎታ እና ጥረት ለወደፊቱ ትልቅ ተስፋ ያለው አትሌት መሆኑን አሳይቷል።

ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፈችበት የውሹ ስፖርት ወጣቱ ተወዳዳሪ ናትናኤል ሀነስ ሀገሩን የሜዳልያ ዝርዝር ውስጥ አስገብቷል። ናትናኤል በቻንቻን የውድድር ዘርፍ ሦስተኛ በመውጣት በኦሎምፒክ መድረክ በውሹ ስፖርት የመጀመሪያውን ሜዳልያ ለኢትዮጵያ አስመዝግቧል። ይህ ውጤት ኢትዮጵያ ከአትሌቲክስ ውጭ ሌላ የሜዳሊያ ተስፋ እንዳላት አሳይቷል።

ኢትዮጵያ እስካሁን በተካሄደው የወጣቶች ኦሎምፒክ ውድድሮች 30 ሜዳሊያዎችን ሰብስባለች። 12 ወርቅ፣ 11 ብር እና 7 የነሐስ ሜዳሊያዎችን ባለቤት ሆናለች። የዓለም የወጣቶች ኦሎምፒክ ጨዋታዎች ለኢትዮጵያ ስፖርት ትልቅ አበርክቶ ያደረጉ መድረኮች መሆናቸው እሙን ነው። በእነዚህ ውድድሮች ላይ ታሪካቸውን የጀመሩት እንደ መሐመድ አማን፣ ዮሚፍ ቀጂልቻ፣ በሪሁ አረጋዊ፣ መቅደስ አበበ፣ ሂሩት መሸሻና መለሰ ንብረት ያሉ አትሌቶች ከዓመታት በኋላ በየዓለም ሻምፒዮና እና በዋናው የኦሎምፒክ መድረክ ላይ ለሀገራቸው ትልልቅ ድሎችን ማስመዝገብ ችለዋል።